ሰንበተ ክርስቲያን ክብርት ልጅት ናት
መንፈስ ቅዱስ ለሰው የተሰጠባት
ጌታ ጉብኝቷቸው በቅዱስ መንፈሱ
ሐዋርያት ፀኑ ከብልየት ታደሱ
ምሥጢር ለመተርጉም በአውቀት ጉለመሱ
ሃይማኖታቸውን በግልጽ መሰከሩ
የአይሁድን ግልምጫ ሞትንም አልፈሩ
ለዜተክርስቲያን የጴጥሮስ ስብከት
ሦስት ሺህ ነፍሳትን አተረፈላት
ተመለሱ ብሎ ጴጥሮስ ሲመክራቸው
ሊገሥጻቸውም በኩሉ ሥራቸው
ከአይሁድ መካከል የበዛቱጥራቸው

አዝነው ተጸጸቱ ስለፀደፋቸው
በክርስቶስ እምነው በሰሙም ተጠምቀው
የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለው
ከዓለም ክፉ ሥራ ከክፋት ርቀው
በፍቅር በአንድነት መከራን ታግሠው
በጎ እየሠሩ ቢጎውን ተናግረው
ወንጌልን በአንደበት በሥራም መሰከረው
ለአምላክ ታምነው ኖሩ በመላ ዕድሜያቸው
ለምእመናን ሁሉ በጉ አብነት ሆነው።

ግንቦት 19 ኤስድሮስ ሰማዕት

ሀገሩ አንጸኪያ ነው :: አባቱ በድላእን እናቱ ሶፍያ ይባላሉ። እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰውን የሚያከብሩ ደጋጉች ነበሩ። በድላእን የንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ሊቀሐራ ነበረ። ዲዮቅልጥያስ በነገሠ በ20 ዓመት ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ እያለ ምእመናንን ይፈኝቸው ጀመረ። በድላእን ፈጣሪዬን ክጀ ለጣኦት ስግጀስ አልኖርም ብሎ ሚስቱንና ሁለት ልጆቹን ይዞ ከአድባራት ባንዱ ተቀመጠ። ዲዮቅልጥያኖስ አስፈልጎ አምጥቶ በሰይፍ አስመታው ኤስድሮስ በዚህ ጊዜ የ12 ዓመት ልጅ ነበረ። ይህስ ምንም አያውቅም ብሎ ከእናትና ከእጎቱ ጋር አጋዘው።

አሥራ ስምንት ዓመት ሲሞላው በሌላ ስፍራ ያለ ዐላዊ ኢራኀራኀኑ ልብከ ወኢመከርከኩ ትተመየጥ እምሃይማኖትከ አልተመለስክምን አለው ፈጣሪውን የከዳ ለጣኦት የሰገደ ይመለስ እንጂ እኔማ ፈጣሪዬን አውቄ ሃይማኖቴን ጠብቄ የምኖር ነኝ አለው። ከግንድ አሰቅሎ ሥጋውን በአስዋጠብርት አስተፈተፈው እናቱ አንተ ርጉም አንተ ጎሱም እያለች ደሙን እየታፈነች እረጨችበት። እጎቱም አፎምያ ትባላለች በደንጊያ ፊት ፊቱን ትጠብሰው ጀመረች። ሰይፍ ጀግሬው ሁለቱንም በሰይፍ መታቸው። እሱንም ጎኑን አስቀድዶ በእሳት አቃጥሉ ለሰማይ አዕዋፍ ለምድር አራዊት ራት ይሁን ብሎ ከዱር አስጣለው። ጌታ ከሞት አንሥቶ ከንጉሥ ፊት አቀረበው ከሠራዊቱ 800 አመነ በአመላኩ ለኤስድሮስ እያሉ አንገታቸውን ለስለት ሰውነታቸውን ለእሳት ሰጥተው በሰማዕትነት አርፈዋል።

አሱንም ከብረት አልጋ አስተኝቶ ከበታቹ እሳት አስነደደበት አሁንም ከሞተ በኃላ ተነሥቶ መሠከረ ከዚህም በኋላ የወፍጮ ደንጊያ በአንገቱ አሳስሮ ከባሕር አስጣለው፣ ደንጊያው ሠጠመ አርሱ ወጣ።

በመጨረሻ ሥቃዩ ይጽናበት ብሎ ግንድ ላይ በችንካር አስቸንክሮ ተወው። ጌታ በስምህ የተማጸነውን ምሬልህለሁ አንተ ከገባህበት መካነ ዕረፍት አስገባልህለሁ ብሎ ተስፋውን ነግሮት ከ 17 ዓመት ተጋድሉ በኋላ በዚህ ዕለት ዐርፏል።

ፉ ከታሪኩ አንጻር መዋዕለ ሕይወቱ ከ292- 329 ዓ.ም መሆኑ ነው።

ሰማዕቱ ኤስድሮስ ላዕከ ቃል ፍጹም
የመልካም ዛፍ ፍሬ ጣፋጭ ነው መልካም
የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን
ለዓለም ሲመሰክር ሲያስተምር እምነትን
በምቾት አይደለም ሳይቀምስ መከራን
እንደ ሐዋርያት ሠጥቶ እንጂ ነፍሱን

አንገቱን ለስለት ለችንካር እጁን
ኤስድሮስ ለአምላኩ በአሕዛብ ፊት
እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀሰማዕታት
እስከ ሞት ድረስ ነው የታመነለት
የሰማዩን መንግሥት የክብርም መውረሻ
በርሱ መታመን ነው እስከመጨረሻ

ማቴ 40 22፤ 2413

ግንቦት 21 ደብረ ምጥማቅ

ከሠላሳ ሶስቱ የእመቤታችን በዓላት አንዱ ነው። ደብረ ምጥማቅ በምኔተ ገምኑዲ አቅራቢያ የምትገኝ ቦታ ናት። እመቤታችን በስደት ሳለች ጌታ በዚህ ቦታ በስምሽ ወላይ ቤተክርስቲያን ይታነጻል ስሙንም ደብረ ምጥማቅ ይሉታል ብሎ ነግሯት ነበር። ይኸውም አልቀረ። በዚሁ ቦታ በእመቤታችን ስም ቤተክርስቲያን ታንጸ ስሙ ደብረ ምጥማቅ ተብሏል።

በዚህም ዕለት እመቤታችን ከወሐይ ሰባት እጅ አብርታ ከጉልላቱ ላይ በመንበረ ብርሃን ተቀምጣ መላእክት ሊቃነ መላእክት ከበው ሲያመሰግኗት፣ ነቢያት ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት እጅ ሲነ ሣት ታይታለች። እስከ አምስት ቀንም ምእመናኑን አረማውያኑን አንድ ወገን አድርጋ ስትባርክ ሰንብታለች። ከዚህ በኋላ ምእመናንም አረማውያንም በየዓመቱ እነሀን አምስት ዕለተት በደብረ ምጥማቅ ተሰብስበው የሚያከብሩ ሆነዋል።

ግንቦት 24 ሀ. ዕንባቆም

ዕንባቆም ማለት ጠቢብ ለባዊ ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ነው ወአብሰለ ተብሏለ ከመ ይሰድ ምሳሐ ለእሰ የአጽዱ ይላል ንፍቀ ቀቅሉ ለአሜጀች ምላ ይዞ ሲሄድ ቅዱስ ሚካኤል ሰድሎቱ ዘንተ ምሳሐ ለዳንኤል ዘሰሉ ውስተ ግበበ ባቢሉን ባቢሉን በጉድጋድ ለተጣለ ለዳንኤል

ውሰድለት አለው። ጌንኤል ወዴት አለ ባቢሎንንም አላውቅም አለ ወነሥኦ በአሐቲ ሥዕርተ ድኅዱ ይላል አንዲት ጠጉሩን ይዞ አድርሶት ሳይከፍት ገብቶ ሣግቦት ሳይከፍት ወጣ፣ መልእኩ እንዳመጣው መልሶታል ተረ. ዳን

ከዚህ በኋላ እስራኤልን ሲያስተምር ቆይቷል የጌታም ሰው መሆኑ ተገልጸለት እግዚአብሔርስ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእም አህጉረ ይሁዳ እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ከይሁዳም ሀገሮች ብሉ ትንቢት ተናግሯል።

➤ መዋዕለ ትንቢቱ ከ 609 -606 ዓ.ዓ

ሊ. በአተ ግብጽ

ጌታ ተወልዶ 2 ዓመት ሲሆነው ሰብአ ሰገል እጅ ሊነሡ እጅ መንሻ ሊሰጡ "አይቴ ሀሉ ዘተወልደ ንጉሠ አይሁድ እያሉ ቢመጡ ሄሮዶስ መንግሥቱን የሚነጥቀው መስሎት" ሊገድለው አስቦ ሕፃናቱን ሰብስቡ ብሎ ባዘዘበት ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ለዮሴፍ "ንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወሑር ብሔረ ግብጽ" አለው። ማቴ 2:13 እመቤታችን ደንግጣ ልዋል ልደር ሰኰል ልትቆን ልጇን አዝላ ዮሴፍ ሰሎሜን አስከትላ ሽሽት ጀምራ በዚህ ዕለት ምድረ ግብጽ ገብታለች።

ሄሮድስ ያጨናነቃ ደርሰው ወንዙን ተሻግረው ካለፉ በኋላ ጌታ በእግሩ ድኅዲሐ ይንኩል አያለ ሲሄድ ከአንዱ ደንጊያ ላይ አሠረ እግሩ ተቀረጸ። እናቱ ሰሎሜ በዚህ ቦታ በስሟ ወቢይ ቤተክርስቲያን ይታነፃል ደብረ ምጥማቅ ይባላል። ብሏታል። ገጸመ አስቴጥስንም ከሩቅ አሳይቶ በዚያ ዐለት ላይ እንደመላእክተ ሰማይ በንጽሕና የሚያገለግሉኝ ወጻጽቼ ይኖሩበታል ብሏታል።

በግብጽም ወደ ምስራቅ ሲደርሱ የዮሴፍን በትር ከሁለት ሰብሮ ከመሬት ተክሎ ባጠጣው ጥዑም ውኃ አፍልቆ አለምልሞ ጥዑም መዓዛ ያላቸው ዕፀው አድርጎ በለሳን /በለ ሰን/ ይባላሉ፣ ለማየ ጥምቀት መቀደሻ ይሆናል። ብሏታል። እሰሙናይን ከሚባል ቦታም ሲደርሱ እንጨቶችና ተራሮች ሰገዱላት። "ምዕረ ትትፈሣሕ ሶበ ተንዘን ለሕጻን ወላዲቱ፣ ርእያ ዘገሃረ ተአምረ ውስተደወለ ግብጽ አመበአቱ፣ እንፈርዐ አድባር ወሰገዱ ሎቱ" እንዲል ደራሲ።

➤ የእመቤታችን መዋዕለ ስደት ከ 02 - 05 ዓ.ም ድረስ ነው ሙሉ ታሪኩን በዚህ መጽሐፍ ከፍል 1 ከገጽ 38 - 41 ተመልከት።

ግንቦት 25 ቅድስት ሰሎሜ

ሰሎሜ ማለት ሰላማዊት ማለት ነው። ለእመቤታችን የአክስት ልጅ ናት ማኅት አያቷ ነው፣ ማርያምን ሶፍያንና ሐናን ወልዷል ማርያም ሰሎሜን፣ ሶፍያ ኤልሳቤጥን ሐና እመቤታችንን ወልዳዋል። ነገረ ማርያ በንክ እመቤታችን የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ሦስት እኅቶቿን አዋልጇታት አላት። ብትመጣ ብፋሀ ሐዘን ታቅፋ አገኝታት ሕማሙ ምጽ ሳይለማሽ በሴቶች የሚደርሰው ሳይደርስብሽ እንደምን ወለድሽው? አለቻት። በማያመረመር ጥበቡ በድንግልና ፀንሺ በድንግልና እንድወልደው አደረገኝ አለቻት። ካሳየሁ አላምንም ብላ ልትዳስሳት እጇን ዘረጋች፣ በእሳት እንደተለበለበ ማንድ ሆኖ ቀረ። የጌታዬ እናቴ እመቤቴ በእውነት ትንቢት የተነገረለትን ሱባኤ የቆጠረለትን አዳኝ እንደወለድሽ አምኛለሁና ይቅር በይኝ ብላ አለቀሰች እኔንማ ምን አድርገሽኛል? ይለቁንስ የማይመረመር ግብሩን ልመርምር ብለሻልና እርሱን ይቅር በለኝ በይው አለቻት። እያለቀሰች ሰውነቱን ብትዳስሰው ተፈውሶላታል። አመስግናዋለች።

ከዚህ በኋላ እንጪት ሰብራ ውኃ ቀድታ እመቤታችንን እያገለገለች ኖራለች። በስደቱም ጊዜ ሕፃኑን አዝላ ከርሷ ጋር ተሰዳለች። "ነበ ሐደበት በማይ አልባሊሁ ወአባሉ፡ለሕፃነ ድንግል ገቡ ሰሎሜ ዘተነገሠ" እንዳለ ደራሲ።

ጌታም በመዋዕለ ስብከቱ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ቆጥሯታል። በስቅለቱ ጊዜ ከእመቤታችን ጋር ከመስቀሉ ሥር ሆና ታለቅስ ነበር። ዮሐ 19:25 በተነሣም ጊዜ በሌሊት ወደመቃብሩ ከሄዱ ሴቶች አንዷ ነበረች። ከዕርገት በኋላ ከሐዋርያት ሳትለይ ሐዋርያትን በተልእኮ ስታገለግላቸው ኖራ በዚህ ዕለት ዐርፋለች።

ሰላም ለለሎሜ ክብርት መብዕዕት
የጌታ እገልጋይ ሐዋርያዊት
ጌታ አምላክ ክርስቶስ አንቺን ለክብር መርጠሽ
በክንድሽ ታቀፍሽው አዘልሽው በጀርባሽ
ድንግል ማርያምን የአምላክን እናት
ሊያዩአት ተመኝተው አበው ሳያዩአት
በትንሳት ሆነሽ ያገለገልሻት
ታድለሽ ነው እኮ ተመርጠሽ በእውነት
ዙነዘኔ ጊዜ አዝነሽ ከርሷ ጋራ
ሲጨንቃት ተጨንቀሽ ተቀበልሽ መከራ
ድንግል በልጇ ሞት ስታለቅስ በምር
አብረሽ ተገኝተሻል በመስቀሉ ሥር
ፍቅሯ አገብርሽ የልጇም ፍቅር

ዮሐ 19 25

ግንቦት 26 ቶማስ ሐዋርያ

ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው። ቀዳሚ ስሙ ዲዲሞስ ነው ዲዲሞስ ማለት ጨለማ ማለት ነው። ቁጥሩ ከ12 ሐዋርያት ነው።ማቴ 10:3 ዮሐ 20 :24 ሐዋ 1:13.

ሊቃ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ያየው በ8ኛው ቀን እሁድ ሲሆን ያመነውንም በጠር የተወጋ ጐኑን ደሰ ነው።___ገጽ ተመልከት የእመቤታችንንም ትንሣኤ ሰርገድን አስቃድሞ ያየ እርሱ ነው___ገጽ ተመልከት

ሀገረ ስብከቱ ሕንደኬ ነው። ለምክንያት ይሁነኝ ብሎ በ30 ብር ተሸጠ ከመስፍነ ብሔሩ ከሉክዮስ ቤት እያገለገለ ይኖር ነበር። ምን ምን መሥራት ትችላለህ? አለው። ሕንፃ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ እችላለሁ አለው እንኪያስ ሠርተህ ቆየኝ ብሎ ብዙ ወርቅና ብር ሠጥቶት አሕዛብ ምኩሀን ናቸውና እንዲህ ያለ ጠቢብ አገኘሁ ለማለት ወደ ንጉሥ ሄደ። እሱም ሕንጻ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ ከዚህ የበለጠ አለን ብሎ ለነዳያን መጸወተው። ከዚያውም ዘንድ አስተምሮ አሳምኗቸዋል። የሉክዮስም ሚስት አርሶንዋ ከነልጆቿ ከነአገልጋዩቿ አምና ተጠምቃለች።

ሉክዮስ ከሄደበት ሲመለስ ያነጽከው ሕንጻ የቀረጽከው ሐውልት ወዬት አለ? አለው በወርቅና በብርህ ያነጽኳቸው ሕንጻዎች እኒህ ናቸው ብሎ ያመኑቱን ደኃፆቹን አሳየው ይህ ክፋ ባሪያ ተጫወተብኝ ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ቆዳውን አስገፍፎ ስልቻ አሰፍቶ በአሸዋ መልቶ አሸክሞ ገበያ ለገበያ ሲያዞረው ሚስቱ አርሶንዋ አይታ በድንጋጤ ወድቃ ሞተች። ሚስቴ የሞተች ባንተ ምክንያት አይደለምን ካዳንካት እኔም በአምላክህ አምናለሁ አለው። ጌታ ቁስሉን እንደ ውኃ አቀዝቅዞለት ካለችበት ሄዶ ስልቻውን ቢያስነካት ተነሥታለች በዚህም ሉክዮስ አምኖ ተጠምቋል።

ከዚህ በኋላ ስልቻውን ተሸክሞ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ሙት እያነሣ ደውይ እየፈወሰ አሕዛብን አሳምኖ አጠመቀ። ቀንጦፍያ ሲደርስ አንድ ሽማግሌ ሰባት ልጆቹን ገድለውበት ሲያዝን አግኝቶ ስልቻውን እያስነካ ሰባቱን አስነሥቶለታል። በኢናስም የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት አይተው ከንጉሱ ሚስት ከንግሥቲቱ ጀምሮ እስከ ተራ ገባር ድረስ ያሉት ሁሉ አምነው ተጠመቁ። ኋላ ግን ካህናተ ጣኦቱ ጥቅም የሚቀርባቸው ቢሆን በተንኮል ከንጉሥና ከመኳንንቱ አጣልተው በዚህ ዕለት አንገቱን በሰይፍ አስመትተውታል።

➢ ሰማዕትነት የተቀበለው በ 72 ዓ.ም ነው

ንሁድ ክብር ሰው ነው ተማስ የኛ አቡን
በእጁ የዳሰሰ የአምላኩን ጉን
ዘመዱ ወጌ ሲሆን አምላያው

እንደምን በሰው ላይ ይጨክናል ሰው?
አምላክ ክርስቶስን ቢሰብክላቸው
አቤት ክፉታቸው መጨከናቸው
ስልቻ አደረጉት ቆዳውን ገፈው
የቆሰለው ሥጋው በጨው ታጥቦ ታሽቶ

የቆዳው ስልቻም በአሸዋ ተሞልቶ
ተሸክሞ ሲዞር በመከራው ፀንቶ
ክብሩን መሰከረ ስልቻውን ነክቶ

የሞተው ተነሥቶ ጌባጣውም ቀንቶ
ስትወልድ በምጿ አዝና አልቅሳ ሴት
ከወለደች ኋላ ደስ እንደሚላት
ጻድቅም ስለጽድቅ የሚሞተው ሞት
የዘላለም ደስታን ያስገኛል ሕይወት

ዮሐ 16 21

ምዕራፍ 4

ሰኔ 9 ሳሙኤል ነቢይ

ሳሙኤል ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው። 1ሳሙ 1:20 አንድም ካህን ተአማኒ ማለት ነው። 1ሳሙ 2:35 ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው፣ አባቱ ሕልቃና እናቱ ሐና ይባላሉ የተወለደው የአርማቴም ዕጻ በሆነች በመሴፋ ሲሆን የብፅዓት ልጅ ነው። ጡት ሲተው እናቱ አፋ እህል ሳይለምድ ሆዱ ዘመድ ሳወድ መሰዳ ለቤተእግዚአብሔር ሠጥታዋለች።

ሊቀካህናቱ ዔሊ ከዘናቱ አፍኒን ፊንሐስ ይባላሉ። አፊኒን ፊንሐስ ጽዩአን ምግባር ነበሩ ጌታ ዔሊን ልጆችህን ሥራ ቅጻ አለው። እነሱ ተመክረው የማይመለሱ፣ ዔሊም ከእግዚአብሔር ይልቅ ለልጆቹ አድልቶ ከሹመታቸው ልሻራቸው ከመዓርጋቸው ላዋርዳቸው የማይል ቢሆን ጌታ አስቀድሞ ለሳሙኤል በራዕይ አስታውቆ ቁጣውን በሞተ እስራኤል ጀምሮ በኤዋ ጽዮን፣ በሞተ አፍኒን ፊንሐስ ጀምሮ በሞተ ዔሊ ፈጽሞ ሳሙኤልን ሊቀካህናት አድርጉ ሾመው።

ከህንት ከምስፍና አንድ አድርጉ ይዞ 40 ዘመን አስተዳድሯቸው አረጀ። ኢዩ ኤል አብያ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት። ካህናት አድርጉ ሾማቸው። ደኃ የሚበድሉ ፍርድ የሚያጓድሉ ቢሆን እስራኤል "እንተሰ ልህቀ ከሙ ኢትመግበነ ወደቂቅከኒ ኢሖሩ በፍናትከ" እንተ እንዳታስተዳድረን አረጀህ ሽመግልህ፣ ልጆችህም አሠርህን አልተከተሉም በዚያውም ላይ በኢያቢስ ዘገለዓድ ባሉ 2 ነገድ ተኩል ወንድሞቻችን ናያስ አምናዊ ቀኝ ቀኝ ዓይናችሁን ገብሩልኝ ይላልና ቅን ፍርድ የሚፈርድልን ከጠላት የሚታደገን ንጉሥ አንግሥልን አሉት ጌታ ከሙሴ ጀምሮ እስከእሁን ድረስ ካህናትን መሳፍንትን አስነሣ እንጂ እንደ አሕዛብ ንጉሥ አንግሦላችኋለን ተው አይሆንም አላቸው ጌታ "ስምየሙ ቃሉሙ ዘይቤሉከ -የሚሉህን ስማቸው" አለው :: ሳኦል ወልደቂስን ቀብቶ አንግሦላቸዋል። ለእርሱም እንዲዝ ሥርዓት ሠርቶባቸዋል። ኋላም ሳኦል ቢበድል የዕሴይ ልጅ ዳዊትን ቀብቶ አንግሦላቸዋል። ዳዊትን ከቀባ በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ በዚህ ዕለት ዐርፏል።

➢ የከረው ከ በ1100 ዓ.ዓ ገደማ ነው።

ሰኔ 11 ገላውዴዎስ ሰማዕት

ገላውዴዎስ ማለት ዕንቈጻዘቦን ማለት ነው:: ሀገሩ አንጾኪያ ነው:: አባቱ አብጥልማዎስ የንጉሥ ኑማርያናስ ወንድም ነው:: እንደ ዮሴፍ አሰራኤላዊ መልከቀና እንደ ዮፍታሔ እንደ ጌዴዎን ኃያለኛ ነበረ:: የሀገሩም ሰዎች ከመውደዳቸው የተነሣ ስዕሉን ሰለው ከእደዛሬይ አቁመው ያደንቁለት ነበር::

ንጉሥ ዲዮቅልጥያናስ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ እያለ ምእመናንን ሲፈጅ እርሱ ከቅዱስ ፊቅጦር ጋር ለአንብቦ መጻሕፍት ይተጋ ነበር:: ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና በአምላለ አረጋዊ መጥቶ ልጆቼ ይህ ንጉሥ ምሕረት የሌለው ጨካኝ እንደሆነ አታውቁምን አሁንም ቢሰማ ይጣላቹሀልና መስላችሁ እደሩ አላቸው:: በነገሩ ጠላትነቱን አውቀው አ አቡሃ ለሐሰት ረሀቅ እምኔነ ወግድልን አሉት አርአያውን ለውጠ በአምላለ ገብር ጸሊም ሆኖ ባማችሁኝ አግኙኝ ብሏቸው ሄደ ንጉሥን ገላውዴዎስና ፊቅጦር ሳሉ መንግሥትህ ይጸና መስሉሃልን አለው:: ካሉበት አሰጠ ርቶ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣያት ስገዱ አላቸው አይሆንም ይህን አናደርግም አሉት ከዚያ እንዳይቀጣቸው ቤተሰቦቻቸውን ፈርቶ ፊቅጦርን ወደ እስክንድርያ ሰደደው እርሱንም ወደ አንጺናው ላከው::

የአንጺናው መስዩን አርያናስ ምነው ወንድሜ ንጉሥ የወደደውን ወደህ የጠላውን ጠልተህ በግዛትህ በሹመትህ ተደላድለህ ትኖርምን አለው:: አንሰ ኢመጻዕኩ ኀቤከ ከመታስሕተኒ በቃልከ ወዳንተ የመጣሁት በሐሰት ቃልህ ልታስተኝ ነውን? አለው:: ለግስፈራራትም ቢሉ ተቆጥቶም ነው ቢሉ የያዘውን ጦር ቢጥልበት ጉኑን ወግቶት በሰማዕትነት ዐርፏል::

➤ ሰማዕትነት የተቀበለው በ304 ዓ.ም አካባቢ ነው::

ቅዱስ ገላውዴዎስ የአንጺናያ መርቅ
ሰማዕተ ክርስቶስ ሐዋርያ ጽድቅ
ለይጣን ሸማግሌ መስሎ ሊያስተው
ጸሎቱን እንዲተው ሊከለክለው
ወግድልኛ ብሎ በእምነት ድል ነሣው
ሊቀጡ ሲወስዱት አሥረው እጃቸን
ሽንጣላውን ሰምቶ ቁጣ ዛቻውን
ላይታለልለት ላይፈራው ሹመን
ወዲህ የመጣሁት አይደለም ልሞኝ
በሐሰተኛ ቃልህ እንድታስተኝ
ይልቅ እንካ እንጉቴን በቢይፍህ ቅጣኝ
እኔ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ
ብሎ አስመቶኖ ሰጠው አንገቱን
ወደ ፈጣሪው ዘንድ ናፍቆ መሄድን
ከንስጥ ኑር ይልቅ ሬኖና ከሚበን
የሚሻል ነውና ከአምላክ ጋር መሆን

ሰኔ 12 በዓለ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ.መ

ሀ. ዕረፍታ ለቅድስት አርሞያ

ሀገሯ ኪልቅያ ነው:: ባለቤቷ አስተራኒቆስ ይባላል፣ መስፍን ኪልቅያ ነበረ፣ ታሞ ሞቶ ከሀብቷ ከንብረቷ እየሰጠች እየመጸወተች በጾም በጸሎት ተወስና ትኖር ነበር:: ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ደግ መነኩሴ መስሎ አጋንንትን መነኮሳይያት አስመስሎ መጥቶ ከደጅ ሆኖ አስጠራት:: ከቤት ገብታችሁ በቅዱስ ሚካኤል ስዕል ፊት ጸልዩልኝ አለቻቸው እኛማ በነግህ ጸልየናል፣ እንደው አንቺ ግን ይህ ሁሉ ጾም ጸሎት ምን ያደርግልሻል? ሲበዛ ያለ ጊዜ እንደሚገድል አታውቂምን ሀብትሽን ሰጥተሽ መጪረስሽስ ስለምንድን ነው? በዚያው ላይ አንቺ ስትደክሚ የሚደግፍሽ ስታረጂ የሚጦርሽ ልጅ የለሽም፣ ሁለተኛ ማግባት ኃጢአት መስሉሻልን? እነ አብርሃም እነ ዳዊት ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች ወልደው የለምን? አሁንም ቤት ሠሪ ጉመን ዘሪ ልጅ ያስፈልግሻልና ባል አግቢ፣ እሺ በይኝ አላት አ አባ እስኬማከ ሠናይ ወቃልከሰ እኩይ አባ ቆብህ መልካም ነበረ ንግግርህ ግን ክፉ ነው አትጹሚ አትጸልዪ ያልከኝ ጌታ ምጽዋተ አበድር እመሰዋዕት ብሉ የለምን፣ ሁለተኛ ባል አግቢ ማለትንስ ከምን አገኘኸው አርጋብ እንኳ ባሉቻቸው ከሞቱባቸው ከሌላ ወንድ አይቀርቡም ታዲያ ጥንቱን በንጽሕና ሊኖር የተፈጠረ ሰው ሁለተኛ አላገባም ቢል ዕዳ ፍዳ ሊሆንበት ነውን? ብላ ባሏ ታሞ ሳለ ያሠራላትን ስዕለ ሚካኤል አውጥታ ብታሳየው ሰኔ 12 ቀን መጥቼ ከተመካሽበት ከዚህ ገብሱስ ስዕል ጋር አጠፋሻለሁ ብሏት እንደተቢያ ፀኖ ጠፋ::

ሰኔ 12 ቀን በነግህ ብርሃናዊ መልአክ መስሉ መጥቶ ጾም ጸሎትሽ ስግደት ምጽዋትሽ ዐርጉልሻል፣ ያሰሡት ሚካኤል በዚያ ዕለት ቅድመ እግዚአብሔር ይቆማልና መጥቼ አጠፋሻለሁ አንላለሽ አውቄ ላድንሽ መጥቻለሁና ስገጂለኝ አላት አንተ ማነህ? አለችው

ሊቀመላእክት ሚካኤል ነኝ አላት:: የንጉሥ መልእክተኛ ያለግኑተም ይሄዳልን? በትረ መስቀልህ ወዴት አለ? አለችው:: መስቀል አሊዞ መሳል ልግድ ነው እንጂ እኛስ አንይዝም አላት ቆየኝ ስዕሉን ላምጣልህ ብላ ዘውር ስትል አርአያውን ለውጠ ደብረ ጽልመት መስሉ አነቃት ቅዱስ ሚካኤል እንደ ዓይን ጥቅሻ ፈጥኖ ደርሶ ቀጥቶ አምሉ ገዝቶ እመቀ እመቅ ጥሉታል:: እሷንም ብፅዕት ሆይ ጸም ጸሉትሽ ሰጊድ ምጽዋትሽ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶልሻል ዕረፍትሽ ዛሬ ነው ብሏት ዐረገ::

ወደ ቤተክርስቲያን ሂዳ ሥጋውን ደሙን ተቀብላ ጻጻሱን ካህናቱን ወደ ቤት ጠርታ ተመለሰች ጳጳሱን በወርቅ ካህናቱን እንደመዓረጋቸው በብር በናስ መንበር አስቀምጣ አብልታ አጠጥታ ወርቅ ብሯን ለቤተክርስቲያን መሥሪያና ለድሆች ምጽዋት ያደርገው ዘንድ ለጳጳሱ ሠጥታ ዐርፋለች:: ሰዕሉም ከእቅፏ ወጥቶ በሮ በሮ ያላንዳች መስቀያ በቤተመቅደሱ በር ተሰቅሎ ተገኝቷል:: ኋላም አብሮ አፍርቶ በአበባው በፍሬው ሕሙማንን የሚፈውስ ሆኗል::

ቅድስት አፎምያ በእምነቷ ጸንታ
በጸም በትሩፋት ሰይጣንን ድል ነሥታ
ንጉት ንባች በክብር አክሊል ተቀዳጅታ
አውነት በመሰለች የሐሰት ትምህርት
መምህር ሳይሆን መስሉ ሰውን ከሚያስት
ከሞት ሐዋርያ ከጽድቅ ጠላት
ነቅተን እንጠብቅ ጸንተን በእምነት

እርሱ መቼም ቢሆን ጀምሮ ከጉንት
የከሀዲት መፍለቂያ የሐሰት አባት
ሊመኝ የሚኖር ነው የሰውን መጥፋት
ከምግባር ልውጥ ከእምነታችን
በጉ እያስመሰለ ክፉ ከፋውን
እኛን የርሱ ባሮች እንዳያደርገን
እስኪ እናፍርስበት የሰይጣን ምክሩን

ዮሐ 8:44 ኤፌ 6:11 ያዕ 4:8

ለ. ዘተፈነወ ኀበ ባሕራን

ሀገሩ እስክንድርያ ነው በዘመነ በጥሊሞስ ልጁ አክሉብጥራ በግብጽ ፹፭ ፱ሚባል ኮከብ ስም ቤተ ጣያት አሠርታ ሕዝቡ በየዓመቱ መሥዋዕት እየሠው ተረፈ መሥዋዕቱን እየተመገቡ እየዘፈኑ እያጨበጨቡ ያከብሩ ነበር:: ሊቀ ጳጳሳት አባ፣ እስክንድሮስ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ «አብያተ ጣያታት ይተዐጽዋ አብያተክርስቲያናት ይትራኀዋ» ብሎ ካወጀ በኋላ አፍርሶ ከቦታው ላይ ቤተክርስቲያን ሠርቶ ታቦተ ሚካኤልን አግብቶ የጣያቱን በዓል

ተው ይህን አነብሩ ብሎ በየዓመቱ በዚህ ቀን በዓል እንዲሆን ሥርዓት ሠራላቸው::

ይህንንም በዓል ከሚያከብሩ ምእመናንን አንዱ የዚህ የባሕራን አባት ነበር:: ተፀንሶ ሳለ ሞተ በተወለደ ጊዜ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ከቤቷ ገብተው ሕፃኑን ባርከው ይህ ሕፃን የዚህን ባለጸጋ ሀብት ይወርሳል ሲሏት ባለጸጋው ጎረቤቷ ሰማ:: ነገሩን ከልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ኖሮ ሕፃኑ አሥር ዓመት ሲሆነው እናቱ ቀጻ የምታለብሰው ቆርሳ የምታጉርሰው አጥታ ስትቸገር ለርሷ ሃያ ወቄት ሠጥቶ ሕፃኑን ላሳድገው ብሎ ከቤቱ ወሰደው:: ወዲያውም በሦስን ከቶ ከባሕር ጣለው ማዕበል እየገፋ ወስዶ ከወደቡ አደረሰው:: አንድ በግ ጠባቂ አግኝቶ ወርቅ መስሉት ከቤቱ ወስዶ ቢከፍተው መልካም ብላቴና ሆኖ አገኘ:: ልጅ ይሻ ነበርና ደስ አለው ከበላው እያበላ ከጠጣው እየጠጣ አሳደገው::

ከብዙ ዓመታት በኋላ ያ ባለጸጋ ለንግድ ሲሄድ መሸተበት ከነርሱ ቤት አደረ:: ባሕራን ባሕራን እያለ ሲጠራው ሰምቶ ባሕራን ምን ማለቱ ነው? አለው ከባሕር የተገኘ ማለት ነው አለው:: መቼ አገኘኸው አለው፣ ጊዜውን ጠቅሶ ሲነግረው ለካስ አልሞተምና አለ:: ሲነጋ ከቤቱ የረሳሁት አለና የድካሙን ዋጋ ላንተ እከፍላለሁ ልጅህን ልላከው? አለው እሺ አለ:: «እንደደረሰ ግደሉት» ብሎ ጽፎ አትሞ ምልክት ነግሮ ሰንቁን አሲዞ ወሰአሞ በጉሕሉት ከመ ይሁዳ ይላል እንደይሁዳ በሽንገላ ሰሞ ሰደደው::

ዘጠኝ ቀን ተጉዞ የአንድ ቀን ጎዳና ሲቀረው ቅዱስ ሚካኤል በአምሳለ ሊቀሐራ በፈረስ ተቀምጦ መላእክትን እንደ ሠራዊት አስከትሎ ከመንገድ ተገናኘው:: አንተ ጉበዝ ወዴት ትሄዳለህ? አለው እንዲህ ካለ ቦታ መልእክት ላደርስ ተልኬ እሄዳለሁ አለው:: እስኪ መልእክቱን አሳየኝ አለው ጌታዬ ለማንም አታሳይ ብሎኛል አለ:: ያም ባይሆን እንደተጠቀለለ አሳየኝ አለው:: አሳየው ወመልአክሰ ነፍሀ ውእተ ክርታስ ወደምሰሰ ኩሎ ዘጽሑፍ ውስተ ውእቱ ክርታስ ይላል እፍ ቢልበት የሞቱን ትእዛዝ አጥፍቶ የሕይወት ትእዛዝ ጽፎበታል:: ያን ይዞ ሂደ ለቤቱ ሹም ሰጠው ቢገልጸው ልጁን ዳሩለት ሀብት ንብረቴን አውርሱት ባሮቼ ይገዙለት የሚል አነበበ:: በጌታው ማኅተም ታትሟልና እንዲሁ አደረገለት::

ባለጸጋው ክንግድ ሲመለስ የዘፈን የጨዋታ ድምጽ ሰምቶ ብላቴናውን አግኝቶ ይህ ሁሉ ዘፈን ጨዋታ ምን ተገኝቷል? አለው። የላከኸው ሰው ልጅህን አግብቶ ሀብትህን ወርሶ ይኸው አርባ ቀን ሙሉ ደክሩናል አለው። ደንገጦ ከፈረሱ ወድቆ ሞቷል። ባሕራንም ይህ ሁሉ በቅዱስ ሚካኤል ረዳኢነት የተደረገለት መሆኑን በራዕይ ተረድቶ እምኖ መጎረገ ቅስና ተቀብሎ ቤተክርስቲያን አሳንጾ ሲያገለግለው ኖሯል።

የማይ ባሕራን የሌለው ተንኮል
በሠሩን ታሸጉ ከክሕር ሲሳል
ውጦ እንዳያስቀረው ሞገድ ማዕበል
ጠብቆ አወጣው ቅዱስ ሚካኤል
ቅንጣት እንኳ ክፋት በደል ላይኖረው
ሞት ታክቶት ሲሄድ ወደሚገድለው
መልአኩ ሚካኤል ከሞት ታደገው

ጠላቱን አጥፍቶ ንብረቱን መለሰ
መልአኩ ሚካኤል በእምነት ለጠራው
የደጋ ደጋፊ ረዳቱ ነው
ከችግር ከሥቃይ የሚታደገው።
አደራ ሚካኤል ቅዱስ ጎብኝኝ
ደካማ ነፍና ሥል አትበለኝ
በኃጢን በሞንተቱ የሚደርስልኝ
ለኔ ካንተ ሌላ ምን ዘመድ አለኝ

ለ. ቅዱስ ላሊበላ/ ከ1180 - 1207 ዓ.ም/

ላሊበላ ማለት ንህብ አእመረ ጸጋሁ ማለት ነው። በተወለዱ ጊዜ ቤቱ በንብ ተከቦ ነበርና ሀገሩ ርሃ ነው አባቱ ጃን ሥዩም ይባላል። ትውልዱ ከዛግዌ ነገሥት ነው። ያማረ የተዋበ መልክ መልካም ነበረና ያለፈ ያገደመው የመጣ የወረደው ሁሉ ይህንንስ ያንግሠው ይሉ ነበር። ንጉሡ ሐርብይ /ሐርቤ/ /ገብረማርያም/ ይህን ሲሰማ ታናሽ ወንድሙ ቢሆንም ንጉሥ በመንግሥቱ ቢገዙት አይወድምና እንግዲህማ መንግሥቴን ሊነጥቀኝ አይደ ለምን ብሎ ይመቀኘው ጀመረ። ይልቁንም ግብሯ የከፋ ክፉ እጎት ነበረችው። ሆዱን በጥብጠ አንጀቱን ቆራርጠ ይግደለው ብላ መርዝ በጽዋ ሞልታ ላከችበት። ተልኮ ያመጣው ዲያቆን ቀምሼ አሰጣለሁ ብሎ ቢጌኔጭለት ጠምቧ ብሎ ሞቷል። የሚንከባከበውም ውሻው ዲያቆኑ የተፋውን ልሶ ሞተ እርሱም ይህ ሁሉ የሆነ በኔ ምክንያት ነው። ወዳጄ ሞቶ እኔ እቀራለሁን ብሎ የተረፈውን ጨለጠው ቅዱስ ገብርኤል ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ከጌታ ፊት አደረሰው። የመላእክትን ምስጋና ሰምቶ ከነዚህስ ጋር ብኖር በወደድሁ ነበር አለ። በግብር አምላካዊ የተሠሩ ሥራው የሆኑ በዓታትን አሳይቶ እንዲህ ያሉ ስሜ የሚቀደስባቸውን ማደሪያዎቼን ብታሠራ ክብርህ ከክብራቸው ምስጋናህ ከምስጋናቸው አንድ ይሆናል አለው።

ከዚህ በኋላ ከሠታቱን ንቡዓቱን ሁሉ ሲያሳየው ቆይቶ በሶስተኛው ቀን ወደ ሥጋው መለሰው ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው አፈፍ ብሎ ተነሣ።

ሙቀት ሳይለይህ አይሆንም ብለን እንጂ ገንዘን ልንቀብርህ ነበር፣ ወዴት ቆይተህ መጣህ? አሉት። እስመ ፍቅር ከመሞት ጽንዕት / / ፍቅር /እንደ/ እስከ ሞት የጸናች እንደሆነች አታውቁምን? የወዳጄ ፍቅር አገብሮኝ ከደረሰበት ደርሼ መጣሁ አላቸው። የበለጠ የሚጠሉት የሚቃወሙት ሆነዋል።

ወንድሜ ጥፋቴን እኅቴ ሞቴን ከተመኙልኝ ከእንግዲህ ከዚህ ምን ያስቀምጠኛል? ብሎ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖርን መርጦ በረሀ ገብቶ በዓት ሠርቶ ተቀመጠ። እንዲህ ሆኖ ሲኖር የታዘዘ መልአክ ነገ በዚህ ጊዜ እንዲህ ያለች ብላቴና ትመጣለችና እንዲህ በላት አለው ከሴት ርቄ ንጽሕ ጠብቄ እኖራለሁ እንጂ ይህንንስ አላደርገውም አለ፣ የፈጣሪህን ፈቃድ መተላለፍ ይቻልህልን? አለው እሺ አለ።

በማግሥቱ ባለው ጊዜ መስቀል ክብራ እንጨት እየለቃቀመች ካጠገቡ ደረሰች። መልአኩ እንዲህ ብሎ ስላንቺ ነገረኝ አላት። ሄዳ ለአባቷ ነገረች። ጥሪው አላት ጠርታ አመጣችው የመልኩን ቀናነት የቃሉን ጥውምነት አይቶ ለዚህስ ሊድሩለት ይገባል ብሎ ድሮለታል።

ከዚህ በኋላ እንደ አብርሃም እንደ ሳራ ተዋደው ለበጉ ምግባር ተግተው የሚኖሩ ቢሆኑ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ሰማዕተ ሐሰት አስነስቶ ለባል የታጨቸውን ሴት ግድ ብሎ አገባት ብሎ ከንጉሥ አስከሰሰው። ንጉሡ አስጠርቶ አርባ አስገረፈው። ከዚት ሲገባ መስቀል ክብራ ወንድሜ ንጉሥ በሰላም ነው ያስጠራህ? አለችው፣ እኔማ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖር ይሻለኛል ብዬ በረሀ ወድቄ አልነበረምን እንግዲህም ከዚያው እኖራለሁ እንጂ ከሰው ጋር አልሆንም፣ ከወደደሽ ተከተይኝ አላት ተከተለችው በረሀ ገብተው በዓት ሠርተው ተቀመጡ። ንጉሥ ሠራዊቱን ልኮ ያስፈልገው ጀመር። ጠባቂ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ኢየሩሳሌም ሂደህ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነሥተህ ትመለሳለህ አለው፣ ይህችስ እኅቴ እንደምን ትሆናለች አለ። ለርሷስ ሚካኤል አለላት ብሎ በአምሳለ ወሬዛ ሆኖ እየመራ

ወሰደው መስቀል ክብራንም ቅዱስ ሚካኤል በአምላለ ወሬዛ ሠናይ አርአያሁ ሆኖ ከሴቶች ገጻም ወስዶ አደራ ሰጣት::

ላሊበላም ቅዱስ ገብርኤልን እየተከተለ ' ሲሄድ ደክሞት አረፍ ካለበት በከንፍህ ነቅተህ ሰማየ ሰማያት እንዳደረስከኝ በከንፍህ ነጥቀህ ኢየሩሳሌም አታደርሰኝምን አለው:: ክብር የክብር ክብር እንድታገኝበት ብዬ እንጂ ነው ብሎ በከንፉ ነጥቆ አደረሰው:: ቅዱሳት መካናትን አይቶ እጅ ነሥቶ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ሲደሰት ጌታ በብሩህ ደመና ተገልጾ ክብርህ ወንጌልን ለመስበክ ዓለምን ከዞሩ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ የተካከለ ይሁን፣ በተስፋህ የጸናውን ቢከዳንህ የተማጸነውን ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም አድንልሀለሁ፣ መቃብርህን እጅ የነሣ ጎልጎታ መቃብሬን እጅ እንደነሣ ይሆንለታል፣ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለታል:: ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ መስቀል ክብራ ካለችበት አደረሰው::

በዚያ ሌሊት ጌታ ንጉሡን መንግሥትህን ለወንድምህ ሰጥተህ ብልየት ጎልፈት የሌለበትን ሰማያዊ መንግሥት ፈልግ አለው:: መንግሥቱን ለላሊበላ ለቆ በረሀ ወድቆ ከፍጹምነት ደርሶ ዓርፏል::

እሱም መንግሥቱን ከያዘ በኋላ በየሀገሩ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠርቷል:: በከተማውም ላይ 11 አቢያተ ክርስቲያናት ከቋጥኝ አስፈልፍሉ አሠርቷል:: ሊሠራም ፈቃደ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማጠየቅ አንድ ክንድ ያህል ተቀርጾ ያደረው በማግሥቱ 2 ክንድ ያህል ሆኖ ይገኝ ነበር:: አብያተ ክርስቲያናቱም

1. ቤተ አማኑኤል
2. ቤተ መድኃኔዓለም
3. ቤተ ማርያም
4. ቤተ ሚካኤል
5. ቤተ ገብርኤል
6. ቤተ መስቀል
7. ቤተ ጎልጎታ
8. ቤተ ጊዮርጊስ
9. ቤተ መርቆሬዎስ
10. ቤተ ሊባኖስና
11. ቤተ ደናግል ናቸው::

እንዲህ አብያተ ክርስቲያናት ሲሠራ አጥቶ እስከ መቸገር ደርሶ ገንዘቡን ለድኃ ሲመጸውት ለጸሎት ሲተጋ ኖሮ በዚህ ዕለት በክብር ዐርፏል::እልመክኑን የሚባል ልጅ የነበረው ቢሆንም መንግሥቱን የወረሰው ግን የወንድሙ ልጅ ነአኩቶ ለአብ ነው::

ቅዱስ ላሊበላ ካህን ወንኑሥ
ለኢትዮጵያ ክብር ነው ሞገስ
ከፋዎች ቢሆኑ ወገናቹ በምድር
የማይመሰሉ የማይኑ ዘክውር
ውሉና አጻሩ ሆነ ከአራዊት ጋር
ባለግወቃቸው ሰዎች ቢጠሉት
መላእክት ወዳጆች ጓደኞች ሆኑት
ጥበብ ግስ ተዋልን ፈጣሪ ሠጥቶት

ጽድቁ ድንት ቢሆን ሥራውም የሚገርም
ስሙን ስታዘክር ትናራለች ዓለም::
እርሱ ቅቤ ግሩን ሥጋ እየበላ
ደኃ ተሬ አጥቶ በረሀብ ሲቆላ
አልቻለው ብሎ አደቶ ግለት ቾላ
መጽውቶ ጨረሰው ሀብቱን በጠቅላላ
ለድኃ መራራት ግዘን ለምስኪን
የሚያሠጥ ነውና በቀኝ መቆምን::

ሴራ 4. 1ግቱ 251 40 ያዕ 2.16

ሰኔ 17 አባ ገሪማ ዘመደራ

ቀዳሚ ስማቸው ይስሐት ነው አባታቸው ሶርንያስ ንጉሠ ሮም ነበር:: ከልጅነታቸው ጀምረው መንፈሳዊ ትምህርት ሲማሩ በዲቁና ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ አድገዋል፣ ኋላም የአባታቸውን መንግሥት ወርሰው ለዓት ዓመት ገዝተዋል::

ከዚህ በኋላ አባ አንጠሌዎን ዘሰማዕት ምድራዊ መንግሥት ያልፍ ይጠፋ የለምን? የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ትወርስ ዘንድ ፈጥነህ ወደእኔ ና ብለው ላኩባቸው ቅዱስ ገብርኤል ወዲያውኑ ነጥቆ አክሱም አድርሷቸው ተገናኙ መጎርገ ምንኩስና ተተብለው በጸም በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ጀመር ጽማቸውም ሥጋቸው አልቆ አጥንታቸው እስኪቆጠር ድረስ ነበር:: ሲጸልዩም ሰውነታቸው ገሌ መቆም እስኪያቅታቸው ድረስ አብዝተው ይሰግዱ ነበር::

አንድ ቀን መቋጐናቸውን ተቀብለው ከመንድሞች ጋራ ወደ መንገድ ሲሄዱ ቤተክርስቲያን አግኝተው እጅ ሲነሱ ካህናቱ እየተቻኮሉ መጥተው ቅዳሴ ሊታጎልብን ነውና ከእናንተ የሚቻለው አንድ ሰው ይርዳን አሏቸው ሌሎቹ መቅጐናቸውን ተመገቡ ነበርና አንችልም አሉ፣ እሳቸው ጠቅልለው የያዟት መቋጐናቸውን ከቅጽሩ አስቀምጠው ገብተው ቀድሰውላቸዋል:: እኒያም ፀልተው የቀደሱ መስሏቸው ለአባ አንጠሌዎን ነገሩ:: እርሳቸውም ሲመጡ መነኰሳቱን አድርጎትም ከሆነ እንዳያፍር ጥቂት እልፍ ፀሉ አሏቸው:: አባ ገሪማ ይህን አውቀው ጎድማስ ሰብአ ዕፀውኒ መአዛን ይሰስሉ ለነ እንጨቶችና ደንጊያዎችም ይወገዱልን እንጂ አሉ:: በዙርያቸው የነበሩ እንጨቶችና ደንጊያዎች ሶስት ምዕራፍ ያህል ሽሽተዋል:: «እምገጸ ዕብዩ ሠናይ ወእምነ ግሩም ታሉ፣ አዕባን ተግሀሉ መዕፀው ለሰሉ» እንዲል አርኬ:: አባ አንጠሌዎን ያዩት የሰሙት ሁሉ ደንቋቸው ግሩም ግሩም ገሪማ ገሪምከኒ አ ወልድየ ይስሐቅ ግሩም ድንት ልጄ ይስሐቅ አስገሪምከኝ /አስደስትከኝ/ አሉ ገሪማ የተባሉት ከዚህ በኋላ መነኮሳቱም አጥፍተናል ብለው ይቅርታ ጠይቀዋል::

ከዚህ በኋላ መደራ ገብተው በዓት ሠርተው 23 ዓመት በትኅርምት ኑረዋል:: ጌታም ልዩ ሀብት ገጺረ

ተአምራት ሠጥቷቸዋል። በነግህ ሰንዴ ዘርተው ዕለቴን ለመሥዋዕት አድርሰዋል። ከመሥዋዕትነት የተረፈውንም በጠፍጣሷ ደንጊያ ቢወቅጡት 77 ቁና ዱቄት ሆኖላቸዋል። በጎቱም ደንጊያ ላይም ወይን ተክለው አብቅለዋል። አንድ ቀንም መጽሐፍ ሲጽፉ ውለው የጀመሩትን ሳይፈጽሙ ፀሐይ ልትገባ ስታቆለቁል ጸልየው የጀመሩትን እስኪፈጽሙ ድረስ ባለችበት እንድትቆይ አድርገዋል። የሚጽፉበትም ብዕር ከእጃቸው ቢወድቅ ወዲያው አብቦ አፍርቶ ተገኝቷል።

ከዚህም የበዙ ተአምራትን ሲያደርጉ ኑረው በዚህ ዕለት በሠረገላ ብርሃን ተሠውረዋል። ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ480 ዓ.ም ነው።

የሚያየውን ዓለም ባላየው ለውጠ
ሰላገለገለው ጌታን በተመለጠ
ሕያው ሆኖ አለ በምሲጋና አጊጠ
ከተጉበጉበው ከአፋራሹ ወጥቶ
በትሩርምት ናረ ከሞሻ ተከቶ
ዛሬች ቃሉን ሰምተው የተናገረውን
ተነቃቅለው ሂዱ ለቀው ቦታቸውን

ደንጊያዎችም ቃሉን አክብሩለት
ደሙ ቢላቸው ራቁ ሸሹለት
ክብሩ እንዲገለጥ የአባ ገሪማ
አብዛ ተገኝች ብፁሩ ለምልማ
እንደ አባት ገሪማ የወንጌል መምህር
ሁሉን ትቶ ያደረ ለጌታው በምድር
ስለእንድ ፈንታ ያገኛል አሥር

ማቴ 19፡20

ሰኔ 20 ሕንጸተ ቤታ ለእግዝእትነ

እመቤታችን ባረገች በ4 ዓመት ጳውሎስና በርናባስ ፊልጵስዩስ ገብተው አስተማሩ፡ ሕዝቡም አምነው ተጠመቁ እንግዲህ ወደ ቤተ ጣዖት አትሒዱ አሏቸው የለመድነውን ከክለከላችሁንማ መካን ጸሎት ስጡን አሏቸው። እንዲህ ብንላቸው እንዲህ አሉን ብለው ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ላኩ አልቦ ዘትገብሩ ወኢምንተኒ ዘእንበለ ትእዛዙ ወምክሩ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለጌታችን ፈቃድ አንዳች ልታደርጉ አይገባም እናንተም ጸልዩ እኛም እንጸልያለን ብለው ላኩባቸው። ሱባዔ ሰጪሪሱ በዚህ ዕለት ጌታ በሩቅም በቅርብም ያሉ ደቀመዛሙርቱን በደመና ጠቅሶ ፊልጵስዩስ ሰበሰባቸው። ዮሐንስ ጌታዬ ለምን ሰበሰብከን ብሎ ጠየቀ ጌታም በእናቴ ስም ጽንፍ እስከ ጽንፍ አብያተ ክርስቲያናት

እንዲታነጹ ፈቃዴ ነውና ሕንጻ ቤተክርስቲያን ላሳያችሁ ሥርዓት ላስተምራችሁ ነው አለው።

ይህንን ብሎ ወደ ምስራቅ ወሰዳቸው ተራርቀው የነበሩ 3 ደንጊያዎች ነበሩ፡ በተአምራት አቀራርቦ ቁመቱን ወርዱን መጥኖ ሠጣቸው ወአዕገኒ ይለመልሙ በእዴሆሙ ይላል እሳት እንዳየው ሰም ከእጃቸው እየለመለሙ /እየተሳቡ/ ቁመቱን 24 ወርዱን 12 ክንድ አድርገው ሠርተውታል። ወይእዜኒ አንትሙኒ ከመዝ ግበሩ እንግዲህ እናንተም እንዲህ አድርጋችሁ ሥሩ ብሏቸው ዐረገ።

በማኅሥቱ እመቤታችንን መንበር ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጉ ቀድሶ አቁርቧቸዋል። ዳግመኛም ወአርአሶ ለጴጥሮስ ይላል ጴጥሮስን እጁን ሚሮ ፖትርያርክነ አድርጎ ሾሞታል። በዚህም ጊዜ ሰማያውያን መላእክት ምድራውያን ሐዋርያት አንድ ሆነው አመሰግነዋል። «በሠ

ላስ አዕባን ገጸ ሥላሴሁ ለአምሮ፡ ሐኒጸ ቤትኪ ድንግል ድኅረ ፈጸመ ሣርሮ፣ አመ ወረደ ለበዓል ምስሌኪ በእኅብሮ፡ እንዘ ይብላ ቃለ ለዘምሮ ልዑል ቀደሰ ማኅደሮ፡ ደናግል ለጽጌኪ ዘበጣ ከበሮ» እንዲል አርኬ፣

➢ ታሪኩ የተፈጸመው በ53 ዓ.ም ነው

ለ. ኤልሳዕ ነቢይ /ከ852 – 798 ዓ.ዓ/

ኤልሳዕ ማለት ዐቃቤ ሀገር ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ይላኮር ነው፡ አባቱ ዮሳፍጥ ይባላል 1ኛ ነገ 19፡16

መምህሩ ኤልያስ ከርሱ የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ካንተ ላልወሰድ የምት ሻውን ለምን ብሎት ባንተ ያደረ መንፈስ እግዚአብሔር በኔ እጽፍ ድርብ ይሁን ብሎ ለምኖ አድሮበታል። ይህም ሊታወቅ ኤልያስ አንድ ሙት ቢያስነሣ እርሱ 2 ሙታን አስነሥቷል ኤልያስ 1 ጊዜ ዮርዳኖስን ከፍሎ ቢሻገር እርሱ 2 ጊዜ ከፍሎ ተሻግሯል።

መምህሩን ሸኝቶ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሲመለስ ኢያርኮ ከከተማ ገብቶ ሠናይ ንብረታ ለባቲ ሀገር በዚህች ቦታ መኖር መልካም ነው አለ። ሊቀበሉት የመጡ ደቂቀ ነቢያት ወማየ ብሔራብ እኩይ ውኃቱ ውኃው ግን ወላድ የሚያመነን መካን የሚገድል ክፉ መራራ

ነው አሉት። በአዲስ ሽክላ ጪው አምጡልኝ አላቸው። አመጡለት ከምንጭ ላይ አድርጎ ከመዝ ይቪ እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል ፈመሰከም ለዝንቱ ማይ ከመ አልቦ ዘይመክን እምኔሁ ወዘይመውት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከርሱ የሚመክን የሚሞትም እንዳይኖር ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ ይላል ብሎ ቢጸልይበት ምሬቱ ጠፍቶ ጣፋጭ ሆኗል ምሳሌነቱን ከዘመነ ስብከት ታሪክ ተመልከት።

ከዚያ አልፎ ቤቴል ሲደርስ ሕፃናት ዕርግ በራህ ውጣ መላጣ እያሉ ዘለቱበት 2 ድባት አስነስቶ 42ቱን አስፈጃቸው 2 ነገ 21-25

ፀቀርሚሉስ ላለ አንዲት ሴት መጥታ ነቢየ እግዚአብሔር ባሌ ፪ሞት ባለ ዕዳ ልጄን ሊነጥቁኝ ነው ብላ ይረዳት ዘንድ ተማፀነችው ከቤትሽ ምን አለ? አላት ጥርኝ ዘይት አለችኝ አለችው። ከጎልንጀሮችሽ ማድጋ ተውሰሽ ሙዪው አላት። ሶስት አራት ማድጋ ተውሳ ጠብ ጠብ ብታደርጋቸው በዘይት ተሞልተው ተገኙ። ይህን ሽጠሽ ዕዳሽን ክፈዪ የቀረውን ተመገቢ ብሏታል። 2 ነገ

ፀፍኖተ ሱናም በሚያልፍም ጊዜ በእንግድነት የምትቀበለው አንዲት ሱናማዊት ነበረች፣ ማረፊያ ሰገነት ሠርታለታለች። አንድ ቀን ደቀመዝሙሩ ግያዝን ምንእናድርግላት? አለው። እርሱም ልጅ ስለሌላት ታዝን ይሆናል አለ። አስጠርቶ የዛሬ ዓመት እንደዛሬ ሕፃን ትታቀፊያለሽ አላት እንዳላትም በዓመቱ ወንድ ልጅ ወለደች። ሕፃኑ ባደገ ጊዜ አባቱን ተከትሎ መስክ ወጥቶ ሳለ ድንገት ሞተ። ሂዳ በውኑ ትወልጂያለሽ ብትለኝ እንጂ እኔ ለምኜ ነበርን? ብላ አለቀሰችበት ቢሄድ ከአልጋው ተኝቶ አገኘው፡ እጁን ከእጄ እግሩን ከእግሩ ገጥሞ እየወደቀ እየተነሣ ሲጸልይ በሰባተኛው ተነሥቶለታል። 2 ነገ 4:25-37

ከዚህ ፀኋላ ዘመነ ሪሀብ ሆነ ደቂቀ ነቢያት ወደርሱ ተሰበሰቡ። ደቀመዝሙሩ ግያዝን ቅጠል ለቅመህ ቀቅለህ ስጣቸው አለው። እርሱም ሳይመርዋ ያገኘውን ሁሉ ቀቅሎ ሠጣቸው። ቀምሰው ፪ሞራቸው ሕምዝ ባቲ ለልሕኩተ ነቢይ መርዝ አለበት አሉ። በልንይ ዴቁቅ አላትንህ ስጣቸው አለው፣ አላትና ቢሰጣቸው ምሬቱ ጠፍቶአቸው ጣፍጧቸው ተመግበውታል 2 ነገ ምዕ 4 ምሳሌነቱን ከዘመነ ስብከት እይ።

በጊዜው የነበረ የሶርያ ሊቀሠራዊት ንዕማን በፈረሰ በሠረገላ ሆኖ ሠራዊት አስከትሎ ወደርሱ መጣ ስለምን ቢሉ ሰውነቱ በለምጽ ነዶ ነበርና ሚስቱ ሲገባ ሲወጣ እያየቸው ታዝን ነበር ከእስራኤል የተማረከች አገልጋይ ነበረቻት በሀገራችን ደውይ የሚፈውሱ ሙት የሚያነሱ ነቢያት አሉ ከነርሱ ዘንድ ቢሄድ ይድን ነበር ብላ መከረቻት። ነገሬቸው እርሱም ንጉሡ ወልዴ አዴር አፈውሶ ለንዕማን ቁልዔየ ወዳጂ ንዕማንን እንዲፈወስ አድርገው ብሎ ለእስራኤሉ ንጉሥ ጽፎለት ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ንጉሡም መልእክቱን አንብቦ አሁን በምን ልጣላው ብሎ ነው እንጂ እኔ መግደል ግዳን የምችል አምላክ ነኝን? አለ ኤልሳዕ ይህ ተገልጸለት ወደኔ ላክው ብሎ ልኮበት በዚህ ምክንያት መጥቷል። ገና ከደጅ ቆሞ ሳለ ፀዮርዳኖስ ውኃ 7 ጊዜ ተጠመቅ አለው ነቢይ ሲባል ፀታሉ ተናንሮ በእጁ ዳሰ የሚፈውስ መስሎኝ እንጂ ውኃማ በሀገሬስ መች አጣሁ ብሎ ተቆጥቶ መለስ ሲል ነቢየ እግዚአብሔር የተናገረው አይቀርምና ያለህን አድርግ አሉት ሄዶ 7 ጊዜ ተጠምቆ ድኗል።

ፀሚሄድም ጊዜ 10 መክሊት ብር 6 ሺህ ወቄት ወርቅ 10 እጀ ጠባብ ይዞ ይህን ተቀበለኝ አለው እሞሾሉ ለጸጋ እግዚአብሔር ፀወርቅ ወፀብሩር የእግዚአብሔርን ስጦታ ፀወርቅ ፀብር አሸጠዋለሁ ብሎ እንቢ አለ። እንኪያስ ምን ሳድርግልህ አለው። በእግዚአብሔር እመን ለሱም ብቻ ስገድ አለው። ለዚህማ ጌታዬ ከቤተ ጣዖት ሲገባ እኔን አስከትሎ ሲሰግድ ትከሻዬን ተደግፎ ነው ከፈቀድክልኝ ግን አፈር ጭኜ ወስጂ መደብ አሠርቼ እሱ ለጣዖቱ ሲሰግድ እኔ ስመ እግዚአብሔር ጠርቼ ልሰገድ አለው። ይሁን አለው ጭኖ ወሰዶ መደብ አሠርቶ ስመ እግዚአብሔር እየጠራ የሚሰግድ ሆኗል።

ግያዝ ወርቅ ብር አልቀበልም ሲል አይቶ ነበርና ሲሄድ ከወደ ኋላ ተከትሎ ነቢየ እግዚአብሔር እንግዶች መጥተውበት ወርቅ ብር ላክልኝ ብሏል አለው። አይሆንም ቢለኝ እንጂ ሁሉንስ ውሰድ ብዬ አልነበረምን ብሎ 2 መክሊት ብር 2 እጀ ጠባብ ሠጠው። ሲመለስ ከወዴት መጣህ አለው እዚሁ ነበርኩ አለ። ንዕማን ሊቀበልህ ከሠረገላው ሲወርድ ልቤ ካንተ ጋራ አልሄደምን ከእግዚአብሔር ጸጋ ይልቅ ወርቅ ብር ሽተህልና የርሱ ለምጽ ባንተና በቤተሰቦችህ ይሁን አለው በለምጽ ተመቶ እንደ በረዶ ነጥቶ ወጥቷል። 2 ነገ ምዕ 5

ደቂቀ ነቢያት ቦታ ጠበበን በዮርዳኖስ ቤት ሠርተን እንኑር አሉት እሺ ይሁን አላቸው። በዮርዳኖስ ዳርቻ እንጨት ሲቆርጡ አንዱ ምሣሩ ከባሕሩ ገባበት የተበደርኩት ምሣር ገባ ብሎ አዘነ ኤልሳዕ ቅርፊት ልጦ በገባበት በኩል ቢጥል የማይዘቅጠው ቅርፊት ዘቅጦ የሚዘቅጠው ምሣር ተንሳፈፈ ያውልህ ብሎት እጁን ዘርግቶ ወስዶታል።

ከዚህ በኋላ ወልደ አዴር ንጉሠ ሶርያ እስራኤልን ሊጣላ ምሽግ መሽጉ ተቀመጠ። ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ በዚህ ሂድ በዚህ አትሂድ ብሎ ላከበት ያም የማይሆንለት ቢሆን ምሥጢር የሚያወጣ አለን? አለ። የምታስበውን የምትናገረውን እያወቀ የሚነግረው ነቢዩ ኤልሳዕ ነው አሉት ይዛችሁ አምጡልኝ ብሎ ሠራዊቱን ሰደደ። ግያዝ በፈረስና በሠረገላ ሆነው ከበዋቸው ቢያይ ደነገጠ ኤልሳዕ ከኛ ጋር ያሉት ይበዛሉ አለው ቢወጣ በእነርሱ ወገን መላእክት በሠረገላ እሳት ሆነው ታዩት። ኤልሳዕ ይህ ሕዝብ ዕውር ይሁን ብሎ ወደ ጌታ አመለከተ። ሁላቸውም ታወሩ። ሄደ ወዴት ትሄዳላችሁ ማንንስ ትፈልጋላችሁ? አላቸው። የምንሄደው ዶይታን የምንፈልገው ኤልሳዕን ነው አሉት። እንኪያስ መንገድ ስታቹህል ብሎ እየመራ ሰማርያ አድርሶ ዓይኖቻቸው የሚያዩ ይሁኑ ብሎ ጸለየ፡ አዩ። የእስራኤል ንጉሥ አባቴ ልግደላቸውን? አለው። የሚበሉት የሚጠጡትን ስጣቸው እንጂ ክፉ አታድርግባቸው አለው። ኢትማኦ ለእኩይ በእኩይ የምትል ሕገ ወንጌል እንድትሠራ አውቆ ጠላቶቹን አብልቶ አጠጥቶ ሸኝቷቸዋል። እነዚያም ጠላቱን አግኝቶ አብልቶ አጠጥቶ የሚሸኝ አለን ብለው እያደነቁ ወደሀገራቸው ተመልሰው ብዙ ዘመን ሳይጣሉ ኖረዋል።

ኤልሳዕም እንዲህ ባለ ግብር 50 ዘመን አስተምሮ በዕላፊ ዐርቈል ካረፈም በኋላ እስራኤል በሞአውያን የተገደለ የአንድ ሰው በድን መስደው ከመቃብሩ ቢያኖሩት ተነሥቷል።
2 ነገ 13:20

ሰኔ 21 ቅዳሴ ቤታ ለእግዝእትነ

በሰኔ 20 ቀን የተተረከውን ከገጽ _____ ተመልከት

ሰኔ 23 ሰሎሞን ንጉሥ /ከ983 - 931 ዓ.ዓ/

ሰሎሞን ማለት መሰተሳልም ማለት ነው። አባቱ ዳዊት እስራኤልን 40 ዘመን ገዝቶ አረጀ፣ አዶንያስ ወልደ አጊት /የዳዊት ልጅ ነው/ አባቴ ዳዊት አረጀ አቤሴሎምም ሞተ ወንድሜ ሰሎሞን እንዳይነግሥ ሕፃን ነው የአባቴ መንግሥት ለኔ ይገባል ብሎ ከኢዮአብ ጋር ሰሙ ለኔ መብቱ ላንተ ይሁን ብሎ መክሮ ቅብዐ መንግሥት የሚቀባው አብያታርን ይዞ በኬልቅ ዘዘኤልቅ በዓል አድርጎ ነገ ሥሡ አለ።

ነቢዩ ናታን የአዶንያስ መንግሥት እንደማይጸና አውቆ የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን /የአርዮ ሚስት የነበረች ኋላ ዳዊት ያገባት እስራኤላዊት/ ኢሰማዕኪኑ ከመ ነግሠ አዶንያስ ወልደ አጊት: አዶንያስ እንደነገሠ አልሰማሽምን አሁንም ሂደሽ ንጉሥን ተሐሰውኑ ቃልከ እግዚአየ ከመ ሰሎሞን ወልድየ ይነግሥ እምድኅሬየ በዲው እኔም መጥቼ ነገርሽን አጸናልሻለሁ አላት ሄዳ ጌታዩ ከኔ በኋላ ልጂ ሰሎሞን ይነግሣል ያልከው ቃልህ ታበለን? አለችው። ወዲያውም ናታን መጣ እሷ ወደ እልፍኝ ገባች። ምነው ደገኛ ልጅህ አዶናያስ ሲነግሥ ሳትጠራኝ ቀረህ አለው ነገራቸው አንድ አንደሆነ አውቆ ቤርሳቤህን አስጠርቶ ሕያው እግዚአብሔርን ከኔ በኋላ ልጂ ሰሎሞን ይነግሣል አለችው። ዕለቱንም ነቢዩ ናታንን ነሀሪ ሳደቅን ብንያስ ወልዳ ዮዳሄን ኬልቲ ፈልቲ የሚባሉ ሬሾፍሮችን ጠርቶ በበቅሎዬ አስቀምጣችሁ ግዮን ወደሚባል መናፈሻ ወስዳችሁ ቀብታችሁ አንግሡት አላቸው ወስደው ቀብተው አንገሡት ሕዝቡም ሕየው ወልደ ኑጋሚ ሺህ ዓመት ያንግሥህ እያሉ በዕልልታ በሆታ ተቀበሉት።

የአብያታር ልጅ አኪማሆስ አባቱን ከነገር ሊያድን ወደ እነ አዶንያስ ሄዶ የሆነውን ነገራቸው ወአዝዙ ይሠረቁ ጽውዓኒሁ ለአዶንያስ ይላል ታዳሚዎቹ አንድ አንድ እያሉ ከደብተው ከሰሎሞን ገብተዋል። አዶንያስ ኢዮአብና አብያታር ግን አቅርንቱ ምሥዋዕ ይዘው ተማጽኑ ሰሎሞን ለጊዜው ምንም አላላቸውም።

ሰሎሞን ወደ ቤተመንግሥት ሲደርስ ዳዊት ከዙፋኑ አስቀምጦ እጁን በራሱ ሥር እግዚአ ኩንኒከ ዘበ ለንጉሥ አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፡ ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ ብሎ ጸለየለት፣

እርሱንም ኩንን በጽድቅ ሕዝብህን በእውነት ግዛ /ምራ/ ብሎ መከረው፤ ሕዝቡንም የ12 ዓመት ሕፃን ሾመብን እንዳይሉ ወይ ወርድ ከመ ጤል ውስተ ፀምር - ጠል ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ ነገሩ ምክሩ ከሰው ልቡና ይስማማልና ብሎ መክሯቸዋል:: 1 ነገ ምዕ 1 መዝ 71-1

ከዚህ በኋላ ዳዊት ዐረፈ እርሱም «ልጄ ሰው ሁን» /1ነገ/ ያለውን የአባቱን ቃል እያሰበ ደኃ እንዳይበድል ፍርድ እንዳያጓድል እየተጠነቀቀ መንግሥቱን ይመራ ጀመር:: በገባኦን መሥዋዕት የሠዋ ዕለት ጌታ ምን ትሻለህ?ሲለው፤ እሱም ጌታ ሆይ ድኃ እንዳልበድል ፍርድ እንዳላጓድል ጥበብንና ማስተዋልን ሰጠኝ ቢለው እውነት እልሀለሁ ካንተ በፊት የነበሩ ያላገኙትን ካንተም በኋላ የሚነሡ የማያገኙትን ጥበብ ሠጥቼሀለሁ ያልለመንከኝ ሀብትንም የሚመስልህ የሌለ አድርጌ ሠጥቼሀለሁ:: እንደ አባትህ እንደ ዳዊት በፍጹም ልብህ ከኔ ጋር ብትሆን እኔም ካንተ ጋራ እሆናለሁ፤ ሲሊው ራዕይ አየ:: እንዲያውም ድንቅ ጥበብንና ማስተዋልን አግኝቷል 1 ነገ 3 4:15

አንድ ቀን ንጉሥ ፍረድልን ብለው ሁለት ሴቶች ቀረቡ ምን ሆናቹኃል አላቸው አንዲቷ ንጉሥ ፍርድ ልብስ ሁለታችን ካንድ ቤት እንኖራለን፣ እኔ በወለድሁ በ3ኛ ቀን እርሷም ወለደች፣ እንትልፍ ሲይዛት ሕፃኑን ተጭና ገደለችው፤ እኔም ተኝቼ ሳለሁ ልጄን ወስዳ የሷን ልጅ ከጎኔ አስተኛችው ልጄን አስመልሰልኝ አለችው ሁለተኛይቱም ዋሽታለች የሞተው የርሷ ነው ይህ ልጄ ነው አለች:: እርሱም የሞተውማ እንድ ጊዜ ሞቷል ይህን ያለውን ከፍላችሁ ሀቡ መንፈቀ ለዛቲ ወመንፈቀ ለእንታኅቲ እኩ ሊታውን ለዚህች እኩሊታውን ደግሞ ለዚያች ስጡ ብሎ አዘዘ ያች አልወለደችውምና እሺ ብላ እጅ ነሳች ይህችንዋ ግን ልጄስ ከሚሞት እሷ ትውሰደው አለች:: የዚያች ልጅ እንዳልሆነ አውቆ ለዚህች ሰጥቷታል: አስራኤልም ጥበቡን አድንቀዋል:: 1ነገ 3:16- 28

አባቱ ዳዊት ቤተ መቅደስ ልሥራ ባለ ጊዜ አኮ አንተ ዘትነድቅ ሊተ ቤተ አላ ወልድከ ዘወጽአ እምሐቋከ ውእቱ ይነድቅ ሊተ ቤተ በስምየ ከአብራክህ የተከፈለ ልጅህ በስሜ ቤት ይሠራልኛል ብሎት ነበርና /2 ሳሙ 2:12/ ሰሎሞን ጌታ ጥበቡን ገልጦለት ከጢሮስ ዝግባና ጽድ እያስመጣ ቤተመቅደስ ሠርቷል::

በ586 ዓ.ዓ ስልምናስር ያፈረሰው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ነው

ቤተመንግሥቱንም አብሮ በ20 ዓመት ውስጥ ሠርቷል:: 2 ዜና 9:1

መንግሥቱን አጽንቶ ግዛቱን አስፋፍቶ የዳዊት ከተማ ጽዮንን አድሶ አስፍቶ ሲኖር በ4ቱ መዓዘናት ያሉ ነገሥታት ጥበቡን ለማየት እየመጡ ይጠይቁት እጅ መንሻም ይሰጡት ነበር:: ከነዚህም አንዷ የሀገራችን ንግሥት የነበረች ማክዳ ነበረች:: ታምሪን የተባለ ኢትዮጵያዊ ጥበቡን ነግሯት ልታየው ወደደች

ከብረ ነገሥት ገጽ 12

ለንግድበሚሄድ ጊዜ እኔ ወደርሱ እሄዳለሁና መንገድ እንድትመራኝ በቶሎ ተመለስ ብላ ለሰሎሞን የሚሰጥ ለርሱም የሚሆን ብዙ ወርቅና ብር ሰጠችው:: እርሱም ኢየሩሳሌም ደርሶ መልእክቱን አድርሶ በቶሎ ተመለሰ በሀገራችን ብቻ ያለ ሽቱ የገዘየን ጥርስ ዕንቁ፣ ወርቅና ብር ይዛ 500 ደናግል አስከትላ ሄደች:: ከእግሯ ላይ እንደ በግ እንደ ፍየል ዘርዛራ ሰኩና ነበረባት ስትገባ ከደጁ ወድቆ የነበረ ግንድ ቢነክው ተቀርፎ ወድቆላታል:: ገባሬ ተአምርነቱን ተረድተው እሱ በ 1 ብር እርሷም በ 1 ብር ለብጠው ከዚተመዛግብት ተቀመጠ

ከርሱ ዘንጋ የተገኙ 28 ነገሥታት በ1 በ1 ብር ለብጥውት እደሁድ 30 ውን ብር ለያዶዳ ሠጥተው በግንዱ ጌታን ሰቅለውታል::

ወደሀገሯም እስክትመለስ ድረስ የሰባ እያረደ የጠራ እያወረደ ባማረ ቦታ አስተምሳታል::

አንድ ቀን ግብር አግብቶ ካዳራሽ ተገኝቶ በቀኙ አስቀመጣት መኳንንት መሳፍንቱ ወይዛዝርቱ እንዳያዩአት መንጠላዕተ መጽሐት ጋረደላት እርሷ ግን ታያቸዋልች ምግቧን ከርሱ ጋራ ጀልታ የአሳላፊዎቹን ሥርዓት የምግቡን ዓይነት ሌላውንም ጥበቡን ሁሉ አደነቀች ብዙም እንቆቅልሹን አምጥታ ጠየቀችው መአልቦ ዘኢፈከረ ላቲ ውተሠወረ እምኔሁ ይላል ላይመልሳት ተሠውሮት የቀረ የለም ሁሉን መለሰላት ጥበብህን ነግረውኝ መጥቼ በዓይኔ እስክይ ድረስ አላመንሁም ነበር: አሁን ግን ከሰማሁት እጄሩ የሚሆን ጥበብህን አየሁ አንተን በእስራኤል

ዙፋን ያስቀመጠ አምላክህ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ብላ አመሰገነች::

ግብር ሲመለስ ወደ ማረፊያዬ ሄጀ እንዳርፍ አሰናብተኝ አለችው:: ዛሬማ ከዚህ እደሪ እንጂ ለምን ትሄጃለሽ? አላት ድንግል ስለሆንኩ በዚህ ለማደር እፈራለሁ ድንግልናዬንም ክልጠበቅሁ አባቴ ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ይፈርሳል አለች:: ለለምን? አላት ጥንቱን የሀገራችን ሰዎች ንጉሥ ነው እያሉ 400 ዘመን ለዘንዶ ሲገብሩ ይኖሩ ነበር የእኔ አባት አንጋቦስ ዘንዶውን ገድሎ ነገሠ:: በፍጻሜ ዘመኑ ሕዝቡን አረጀሁኝ ከኔ በኋላ ልጆቼን እንድታነግሡልኝ ቃል ግቡልኝ አላቸው እነርሱም ወንድ ልጅህ ወንድም ባይኖር ወንድ ሳታውቅ ሴት ልጅህን እናነግሥልሀለን አሉት እሱም ሲሞት እኔን አነገሱኝ አለችው:: እንዲህስ ከሆነ ተላልፈ አልነካሽም አላት:: ማልልኝ አለችው አንቺም ከሀብቴ ከንብረቴ እንዳትነኪብኝ ማይልኝ አላት ጥበበኛ ስትሆን እንዲህ ያለ ተራ ነገር ትናገራለህን ወርቅ ብር በሀገሬ ሞልቷል ወዳንተ መምጣቴ ጥበብህን ላይ እንጂ ወርቅ ብር ፈልጌ ነውን?አለችው: ግድየለም ማይልኝ አላት ማለችለት: እሱም አስቀድሞ መሐላ ላያፈርስ ማለ:: ደንገጡሯን ይዛ ተኛች::

ጥቂት ተኝታ ውኃ ጠማት ውኃ ጠማኝ ከዙሰዙስቱ ቀድተሽ አምጪልኝ አለቻት ሰሎሞን ሲያንቀላፋ ዓይኑን ይገለግል ሲኝቃ ዓይኑን ይከድናል:: ዓይኑን ገልጾ ብታየው ንጉሥ ያየኛል አለቻት ሁለተኛ ጠምቶኛል አምጪልኝ አለቻት አይሆንም ያያል አለቻት:: ሶስተኛ አዙንስ አያይም አምጪልኝ አለች ሰሎሞን ከእንቅልፋ ነቅቶ ዓይኑን ከድኖ ነበር:: የተኛ መስሏት ቀድታ ሰጠቻት ስትጠጣ እጇን ይዞ ምነው መሐላሽን አፈረስሽ? አላት ውኃ ቢጠጡ መሐላ ይፈርሳልን አለችው ምድር በውኃ ላይ ጸንታለች አትነክልት አዝርዕት ዕፀዋት በውኃ ይበቅላሉ ያብባሉ ደንግሞም እንጂ ውኃ ቢጠጡት ያረካል ቢታጠቡበት ያንጻል: ታዲያ ከዚህ የበለጠ ምን ሀብት አለ? አላት በዚህ ተረታች አብረው አደሩ::

በምትሄድ ጊዜ እንሻለሁና በወለድሁ ጊዜ ሴት ወይም ወንድ መሆኑን እንዳስታውቅህ ምልክት ስጠኝ አችው ወንድ የወለድሽ እንደሆነ ይህን ላኪልኝ ብሎ የወርቅ ቀለበት ሴት ከሆነችም ይህን ላኪልኝ ብሎ የብር ቀለት ሠጣት:: ይህንንም ምክንያት አድርገሽ ለእግዚአብሔር ሰገጂ ብሎ ከታቦተ ጽዮን ሀብት ፣ መንፈሳ ሰጣት

ይህን ይዛ በክብር በመሳረግ ወደ ሀገሯ ተመለሰች:: ስትሄድም ዓምደ ብርሀን ተከትሏት ሲሄድ አይቶ ክብር ወደ ኢትዮጵያ ሄደ ብሏል::

መዋዕለ ጽንሷ ሲፈጸም ወንድ ልጅ ወለደች:: ስሙንም ዕብነሐኪም አለችው የብልህ ልጅ ማለት ነው:: የምስራቹንም የወርቁን ቀለበት ላከችለት:: ወንድ ልጅ አገኘሁ ብሎ ደስ አለው አይታችሁት ኑ ብሎም ባለሟሎቹን ብዙ ወርቅና ብር አሲዞ ላከ::

ዕብነ ሐኪም 19 ዓመት ሲሆነው አባቱን ሊያይ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ሰሎሞን መኳንንት መሳፍንቱን ልጄን ተቀበሉ ብሎ ልብስ መንግሥቱን፣ ዘውዱንና የሚቀመጥበትን ሠረገላ አሲዞ ላከ ልብስ መንግሥቱን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ በሠረገላው ሆኖ ሲገባ መልኩ አባቱን ይመስል ነበርና ንጉሥ ወዴት ሄዶ ነበር? አሉ ሲደርስም ምኒልክ እንደምን ዋልህ እንደምን አለህ ብሎ ሳመው ከዚህ በኋላ ስሙ ምኒልክ ተብሏል:: ምን ያምር ማለት ነው::

ከዚህ በኋላ ምኒልክ ሲወጣ ሰሎሞን እየመሰላቸው ተከትለውት ይወጣሉ ሲገባ ይገባሉ:: ይህ የሚያስቸግራቸው ቢሆን ለሁለት ጌታ መገዛት አይቻለንምና አንግሠህ ወደናቱ ሀገር ላከው አሉት:: እኔን የበኩር ልጅህን ላክ ካላችሁኝ እናንተም ወንድም ሆነ ሴት የበኩር የበኩር ልጆቻችሁን ከልጄ ጋራ ትልካላችሁ አላቸው እሺ ይሁን አሉ:: ሊቀ ካህናቱ ሳዶቅ ልጁ አዛርያስን ሠጠ:: ሌሎቹም እንዲሁ የበኩር ልጆቻቸውን ሠጡ:: የካህናቱ ልጆች ሂዱ ካላችሁን ምክንያት አድርገን ለእግዚአብሔር እንሰግድበት ዘንድ ከታቦተ ጽዮን ሀብት አንዱን ስጡን አሉ:: የታቦተ ጽዮን የውሰጠኛው ልብስ ይሰጣችሁ አላቸው:: እነርሱ ግን ከታቦተ ጽዮን መለየት አልወደዱምና አንድ አንድ ወቄት ወርቅ አዋጥተው በታቦተ ጽዮን ልክ ታቦት ቀርጸው በወርቅ ለብጠው በታቦት ጽዮን ቦታ አኑረው ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሄዱ::

ከተማውን ለቀው ሲወጡ ኢየሩሳሌም ተናወጠች:: ሰሎሞን ሳዶቅን አስጠርቶ ይህ ልጅ በተነጸነሰባት ሌሊት ፀሐይ ከምድር ወርዳ በኢየሩሳሌም ጥቂት ስታበራ አይቻለሁ አሁንም ሂደህ ታቦተ ጽዮን መኖሯን ተመልከት አለው:: ቢገባ ልጆቻቸው የሠሯትን እንጂ ታቦተ ጽዮንን አጣት ደነገጠ ሄዶ የለችም ወስደዋታል አለው:: እንደ ነፋስ በሚበር ሠረገላ ሆኖ ተከተላቸው በ3 ቀን የሄዱትን በ1 ቀን ተጉዞ ዜናቸውን ቢጠይቅ ከኛ በሠለስት ተነሡ

ሊጸልዩም መረኖቻቸው ፈርሶባቸው በንጋር ያህል መራት ልተው ይታዩ ነበር ይሆን ጊዜም የገ ቀን ጎዳና ተጉዘው ይሆናል አሉት፣ እያዘነ ተመለሰ። እኒያም ብንነገረው መልሶ ለአባቱ ይሰውናል ብለው ፈርተው አልነገሩትም ነበር። የምንገርህ አለ ለአባትህ መልስህ እንዳትሰጠን ቃል ግባልን ብለው ቃል ካስገቡ በኋላ በጪተመቅደስ የነበሩ የሕግና የጥበብ መጻሕፍትንና ታቦተ ጽዮንን ይዘን መጥተናል አሉት። ፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ ቢሆን ነው ብሉ እጅግ ደስ አለው።

ሲደርሱም እናቱ 40 ቀን የሰነ እያረደች የጠራ እያመረደች ታላቅ አቀባበል አድርጋለታለች ታቦተ ጽዮንንም ቤተመቅደስ አሠርታ አስቀምጣለች ለክህናቱም ርስት ጉልት ሰጥታቸዋለች። ክብ ነገ

ሰሉሞን የጌታ ጎብዕ ስም የተቀረጸበት ግርማ ሞገሱ ትእምርተ መንግሥቱ የሆነ ቀለበት ነበረው አንድ ቀን ከዙፋኑ አስቀምጦት ሳለ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ከንዙፋኑ ጠቅሎ ወስዶ ኮባሕር ጣለው ሰሉሞን ሊገባ ሲል ዙፋን ጠባቂው አትግባም ብሉ ከለከለው። ኧረ ሰሉሞን ነኝ ቢለው ሰይጣን በምትሐት እሱን መስሎ በዙፋኑ ተቀምጦ ነበርና ሰሉሞን በዙፋኑ ተቀምጦ ሰሉሞን ነኝ ትላለህን? ብሉ ገፍቶ አስወጣው እርሱም ወጥቶ በከተማው 2 ሳምንት ያህል እየለመነ ሰነበተ አንድ ቀን ሰይጣን እየተከታተለ የሰውን ልብ እያጸናበት የሚመጸውተው አጥቶ ከባሕር ሄዶ ዓሣ አጥማጆችን ለመነ። አንዱ ይህ ዘብዛባ ብሉ የሞተ ዓሣ ጣለለት ሆዱን ቢቀደው ቀለበቱን አገኘ ግርማ ሞገሱ ትእምርተ መንግሥቱ ነውና በዚያ የነበሩት ንጉሥን ከዚህ ምን አመጣው እያሉ ከበው እጅበው ከቤተመንግሥቱ አደረሱት። ሰይጣኑ ወጥቼ እሄዳለሁ ሲል እንግዲህማ ወዴት ትሄዳለህ ብሉ ምድር አስቆፍሮ ቀበረው እንዳይወጣም መርበብተ ሰሉሞን የሚባል ስመ አምላክ አትሞበታል። ከዚህም ያደረሰው አንድ ቀን የራበው ችግረኛ ሲለምን ምን ሆኖ ነው ቢል ርቦት ብለውት በሞጊዝት አድጎ ኋላም ፀመንግሥት ሆኖ ረሀብን አያውቅምና ረሀብ ደግሞ ምንድር ነው? ብሉ ነበርና እንዲቀምሰው ነው።

ኋላ ግን መፍቀሬ አንስት ሆነ 700 ሚስቶች 300 ቅምጦች አስቀምጦ አረማውያት የሆኑት ለሣያት እንዲሠዋ ልቡን አዘንብሉት ንጉሥ በመንግሥቱ ሲገበብት እንደግይወድ ጌታም በእምላክነቱ ቢገበብት አይወድምና መንግሥትህን ከልጅህ እጅ ከ12 እቀዳለሁ።

ለባሪያዬ ለዳዊት ስለግልኩት መሐላ ግን አንዱ እጅ ለልጅህና ለቤቱ ይሆናል አለው 1 ነገሥ.16.

በፍጻሜ ዘመኑ ንስሓ ገብቶ ይቅርታ ለመነ ጌታም ንስሓውን ተቀብሉ ኃጢአቱን ፋቀለት መርገም ያልወደቀባት ንጽሕት ዘር ከአዳም ባሕርይ ተከፍላ በሴት አካል ተቀርጻለች፣ ከሴት ሲወርድ ሲዋረድ በኖኅ በሴም ከሴምም ሲወርድ ሲዋረድ በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ፡ ከያዕቆብም ሲወርድ ሲዋረድ በዳዊት ከዳዊትም ባንተ ካንተም በሮብዓም አካል ተቀርጻለች ከርሷ አምላክ ይወለዳል እርሱም በሞቱ ዓለሙን ያድናል ብሉ የዓለምን የድኅነት ተስፋ ሊላውንም እስከ ምጽአት ድረስ የሚሆነውን ሁሉ ገልጸለታል። ጥበባቱን ምሳሌያቱን ተግሣጻቱን በመጽሐፍ ጽፎ /አጽፎ/ ቢተወለደ በ52 በነገሠ በ40 ዓመቱ ዐርፏል።

ሰኔ 24 ሙሴ ጸሊም

አባት እናቱ ፀሐይን ያመልኩ ነበር፡ ኃጢአት በሠራ ጊዜ ተው አምላካችን ፀሐይ ይጣላህል ይሉታል። ፀሐይማ አምላክ ቢሆን እስከዛሬም ባቃጠለኝ ነበር ይላቸዋል። አንድ ቀን ፀሐይና ጨረቃን የሚያፈራርቀውን እውነኛውን አምላክ ባውቀው በወደድሁ አለ። መንፈስ ቅዱስ አነሳስቶ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ወሰደው ካህን ለተልዕኮ ሲገባ አይቶት ሊፈጀን የመጣ ነው ብሉ ፈራው። እርሱ ሄዶ አምላክ ማን አንደሆነ አስተምረኝ አለው ከመምህር ኤስድሮስ አገናኘው። አስተምረው አጥምቀው ለመዓርገ ምንኩስና አበቁት።

አርባ ዘመን ከሰው ተለይቶ በዓቱን ዘግቶ ከኖረ በኋላ በ500 መነኮሳት ላይ አበምኔትነት ተሾመ። ቀን ቀን ሲያስተምር ይውላል፣ ሌሊት ሌሊት ከበረሀ ወርዶ እንጨት ሰብሮ ውኃ ቀድቶ ለየመነኮሳቱ በየደጃፋቸው ያኖርላቸዋል። እርሱ መሆኑን አያውቁም ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና አንድ ሌሊት እንጨት ሰብሮ ውኃ ቀድቶ ሲመለስ። በደንጊያ መሀል አገዳውን መታው እርሱ ግን ጻብዕ መሆኑን ተረድቶ የበለጠ እንዲህ ባለ ትሩፋት የሚጋደል ሆኗል።

በዓል ቦሚያደርጉ ጊዜ አባታችን መዓርገ ቅስና ተቀብለህ ናዘን ብለው ወደ ሊቀጳጳስ ይዘውት ሄዱ ሊቀጳጳሳቱ እንዲህ

ያለውን ጠቋራ ታመጡብኛላችሁን አለ። ሠናየ ገብሩ ብከ አ ጸሊም ዘኀሱም ገጽከ መልክህ የከፋ አንተ ጠቋራ ደግ አደረጉብህ እያለ ራሱን እየገሰሠጸ ወጣ። እመቤታችን ለሊቀጳጳሳቱ ተገልጻ መልኩ ቢጠቁር ልቡ ይነጻ የለምን ብላ ገሠፀችው ደግ አላደረግሁም ብሎ አስጠርቶ ሾመው። ይህም የእመቤታችን ቃል ኪዳኗ ዘማዊውን እንደ ድንግል ንጥኡን ጻድቅ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል «ይትባረክ ጽጌኪ ማርያም ለልበየ ፍቅርኪ ዘከፈሉ፣ወአያር ኀቀ እምኔየ ለኪዳንኪ ሣህሉ፣ ትምህርተ ኪዳንኪ ይሁብ ለዘማውያን ተደንግሉ» እንዳለ ደራሲ። የንስሓንም በቁጴት ይገልፃል ንስሓሰ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመዘኢአበሰ» እንዲል።

ከዚህ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ 7ቱን አስከትሎ ወደ አባ መቃርስ ሄዶ ሳለ በርበር ገዳሙን ሊያቃጥሉ እነርሱንም ሊገድሉ መጡ። ከናንተ የፈራ ይሸሽ አለ። አባታችን አንተስ አትሸሽምን አሉት ሞት ፈርቼ ሰማዕትነት ጠልቼ እሸሻለሁን አለ። ወዲያው በርበር ደረሱ በጎልማሳነቱ ጊዜ ደም አፍስሶ ነበርና ኢይነጽሕ ደም ዘእንበለዳም፣ደም ያለ ደም አይነጻምና የኔም ደም ይፍሰስ ብሎ አንገቱን ለሰይፍ ሰጠቶ በሰማዕትነት ዐርፏል። ከደቀመዛሙርቱም 6ቱ እሱን ተከትለው አንተገታቸውን ለሰይፍ እየሰጡ ሞቱ። አንዱ ግን ፈርቶ ከጥሻ ተደብቆ ነበር፣ መልአኩ ስምንት አክሊላት አምጥቶ 7ቱን ለሰባቱ ሲያቀዳጃቸው አንዱ ከእጁ ሲቀር አይቶ ከተደበቀበት ወጥቶ በሰማዕትነት ሞቶ ተቀዳጅቷል።

➢ የነበረው በ 4ኛው ም.ዓ ድ/ልክ ነው።

የጸም ጓደኛዋ የጸሎት ወዳጅ
የዋህ አባ ሙሴ በረሱ ፈራጅ
በንስሓ ታጥቦ ነጽቶ ከበረድ
በጽድቅ ጎዳና ሲሄድ ሲራመድ
ሰይጣን ተመቅኝቶ ሊያጠፋው ሲወድ
እንውን ሊረዳ ቢወጣ ቢወርድ
ሞገስን አገኘ በፈጣሪው ዘንድ

ሙሴ በጎ ሰው ነው እውነተኛ ምስመናን
ለእምነቱ ቀንቶ ያፈሰሰ ደሙን
ጻድቅ ሆኖ ሳለ ፍጹም የከበረ
ሁሌ በደለኛ ሰው ነኝ ይል ነበረ
ምን በጎ ብንሠራ ከበደል ርቀን
ከቶ አይጽነንም ልንል ጻድቃን ነን
በሥራችን ሁሉ ፍጹም ሰላልሆን

ሰኔ 25 ይሁዳ ሐዋርያ /ረድዕ/

ይሁዳ ማለት ታማኝ ማለት ነው። ቁጥሩ ከ 7ቱ አርድዕት ነው የጌታ አሳዳጊ የዮሴፍ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነው። ማቴ 13:55 ይሁዳ 1:1

ጌታ «ሑሩ ወመህሩ ውስተ ኩሉ አሕዛፌ ምድር» ማቴ 28:19 ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን ለዓለም እንዲሰብኩ ያዘዛቸውን አስቦ ሐዋርያትን መስሎ ሐዋርያትን አክሎ ዞሮ በማስተማር ብዙዎችን ከይሁዲነት ወደ ክርስቲያንነት ከአረማዊነት ወደ ምዕመንነት መልሷል።

በቁ፻ሜ ዘመኑ ዐላውያን አልተው ተመቅኝተው ከዘመነ ቤቲ ጥለውት ሳለ ያስተማራቸው ምእመናን ክሃይማኖት እንዳይፋለሱ በኃጢአት እንዳይረክሱ ተጋድሏዊ መልእክት ጽፎ ልኮላቸዋል። በመጨረሻም በችንካር ተቸንክሮ በመሰቀል ተሰቅሎ ሀርቷል።

ሰኔ 26 አያሱ ወልደ ኑዌ

ኢያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው አባቱ ነዌ የባላል። መምህሩ ሙሴ በምድረ ሞአብ ካረፈ በኋላ ጌታ ባንተ አድራ ሕዝቤ እስራኤልን ለወጻጀቼ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ማልሁላቸው ምድር አገባቸዋለሁና በርታ ጽና ከባሪያዬ ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁ ካንተ ጋር እሆናለሁ አለው። እርሱም ጠንክሮ ሕዝቡን ይመራ ያስተዳድር ጀመር።

ካሌብንና ሰልሞንን ኢያሪኮን ሰልሉ ብሎ ላካቸው። ደጋ ደጋውን ሲሰልሉ ሰንብተው አያሪኮ ደረሱ የኢያሪኮ ንጉሥ እስራኤል ከግብጽ መውጣታቸውን ሰምቶ ሰባት የብረት ቅጽር ቀጽሮ ይኖር ነበር። የሀገሩም ሰዎች ጠርጥረዋቸው ሊጣሏቸው መጡ። ሪፀብ/ ራኬብ/ ከምትባል ዘማ ቤት ገብተው ሠውሪን አሏት ከሰኘት አውጥታ በቀርከሃ ጠቅልላ አቆመቻቸው ተከታትለው መጥተው የእስራኤል ሰላዮች ከቤትሽ ገብተዋል አውጪ አሏት። መጣትማ ገብተው ነበር። ቁራሽ ቀምሰው ውኃ ተጉነጭተው ከናንተ ጥቂት ቀደም ብለው ወጥተው ሄዱ አለቻቸው። መጣቢታቸውን ሰላልካደች መውጣታቸውን አምነውላት ተመልሰዋል። ገብታ ትብውዩ ሀገሪን ወትቀትሉ ነገሥታቲን ሀገራችን ትገዛላችሁ ነገሥታቱን ትገድላላችሁ ይሀም ሊታወቅ ኃያላኑ ይሸበራሉ ለ50 ለ60 የሚከፈተውም የብረት በር በገዛ እጁ ሊከፈት ሲዘጋ ያድራል ነገር ግን ወገኖቼ ተድላ ደስታ ሲያደርጉ

እኔ አላደረግሁምና አብራችሁ እንዳታጠፋኝ ታል ገዙልኝ አለቻቸው። ቤተሰብሽን በቤትሽ ሰብስበሽ ከመስኩትሽ ሐር አንጠ ልጥለሽ ቆዪን ብለዋት ሄደው ያጋጣግቸውን ሁሉ ለኢያሱ ነገሩት።

ኢያሱ ታቦተ ጽዮንን አሲዞ ዮርዳኖስን ከፍሉ ተሻገሩ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ መና ከደመና እየወረደላቸው ውኃ ከጭንጫ እየፈለቀላቸው ይመገቡ ነበር። በኋላ ግን መናው ቀርቶ የከነዓንን ፍሬ የሚመገቡ ሆነዋል።

ኢያሪኮ ቅጽሯ ሰፊ አምባዋ ጽኑ ነውና 6 ቀን እየዞረ ከደረሰበት ሲሰፍር ሰንብቶ በሰባተኛው ቀን ኃያላኑን በግራ በቅኝ አሰልፎ ካህናቱን አልባሰ ተክህኖ አልብሶ ማዕጠንታተ ብርት አሲዞ ታቦተ ጽዮንን በመሀል አድርጎ እሱም ከመሀል ሆኖ የነጋሪት ድምጽ ሰትሰሙ አውኩ ደንፋ ብሏቸው ነበርና ቢደነፋ የኢያሪኮአጽርአንደ ከሞር በአራት ወገን ፈርሳል። ረዐብንና ቤተሰቧን አስቀርቶ ሕዝቡን አጥፍቶ ሀገሪቱን ይዟል።

እስካሁን ያገኘውን ለራሳችን ስናደርግ መጥተናል ከንግዲህ የምናገኘው ለእግዚአብሔር ይሁን ብሎ እስራኤል ያገኙትን ሁሉ ለቤተ እግዚአብሔር ሠጡ። ከጋይ ሰዎች ጋር ሲዋጉ ባንድ ጊዜ 36 እስራኤላውያን ተመቱ። ኢያሱ ወደ ጌታ ፀያመለክት ያልከውን ያስቀረ አለ አለው። ዕጣ ቢያጣጥል በአካን ወልደ ዛራ ወደቀ ከደበቀው ወርቅና ብር ጋር በደንጊያ ተወገር ደንጊያ ተከምሮበት ሞቷል። ከዚህ በኋላ ጌታ ጋይን አሳልፎ ሠጥቶታል።

ጋይን አልፈው ገባያን ሲደርሱ 5 አሞራውያን ነገሥት ተባበሩት የቀረቡትን እርሱ በሰይፋ መታቸው የራቁትንም ጌታ በመብረቅ ፈጃቸው። ካሰበው ሳይደርስ ፀሐይ ልትገባበት ቢሆን ለትቁም ፀሐይ በገባያን ወወርጎኒ በፈለገ ኤሉን ፀሐይ በገባያን ትቁም ጨረቃም በኤሉን ወንዝ ብሎ ጸልዮ ካሰበው እስኪደርስ ድረስ ፀሐይን ካለችበት አቁሚታል። ኢያ 10:12

በፍነሚ ዘመኑ እስራኤልን ሰብስቦ የሞአብን አምላክ ታመልኩ ወይስ እግዚአብሔርን አላቸው እግዚአብሔርን እንጂ የሞአብን አምላክ አናመልክም አሉት ምን ምስክር ይሁንባችሁ አላቸው፡ አንተ ያልከው ይሁን አሉ ሦስት ገጻት ያሏት ደንጊያ /ሐውልት/ ወስዶ በሴሎ በደብተራ አሪት አጠገብ ተክሰ የወጣ የወረደው ያሰፈ ያገደመው ሁሉ ኢያሱ ከእስራኤል ጋር የተማማለባት ሐውልት እያለ የሚያያት ሆኗል። እንዲህ ሆኖ ኖሮ በተወለደ 110 ዓመቱ ዐርፏል።

➢ የኖረው በ1500 – በ1400 ዓ.ዓ ገደማ ነው።

ሰኔ 27 ያዕቆብ ዘሥሩግ /ከ 366 – 438 ዓ.ም/

ያዕቆብ ማለት አጋዚ አዕታኢ ማለት ነው። አባቱ የሰርያ ሊቀካህናት ነበር። በተመለደ በ3 ዓመቱ እናቱ ወደ ቤተክርስቲያን ይዛው ሄደች። ልዑካን ሥጋውን ደሙን አተብለው ሲመለሱ ከእናቱ ጭን ወርዶ ድንኩል ድንኩል እያለ ቤተመቅደስ ገባ። ሊቀጳጳሱ ጸጋ እግዚአብሔር እንደጠራው ከፍጹምነት እንደሚደርስ አውቆ ደሙን /ተረፋን/ በጽዋው 3 ጊዜ ጋተው ወዲያው ምሥ ጢር ተገልጸለት ሥጋህን ደምህን የሰጠሽኝ እያለ አመሰገኗል። አያይዞም «አንበ እፈርሀ ሠለስተ ግብራተ ወይእቲ ጸአተ ነፍስ እምሥጋ፣ ወተራክቦ ምስለ እግዚአብሔር ወጸአተ ፍትሕ ላዕሌየ – ሶስት ነገሮችን እፈራለሁ እኒህም የነፍሴ ከሥጋዬ መለየት፣ ከእግዚአብሔር ጋራ መገናኘትና ፍርድ መሰማት ናቸው1» እያለ ያለቅስ ጀመረ። ካህናቱም ምእመናኑም ጌታ እንጂ በዚህ ሕፃን አድሮ ወቀሰን ብለው አልቅሰዋል።

በ7 ዓመቱ ብሐይ ሐጺስ አጠና፣ በ12 ዓመቱ ድረሰት መድረስ ጀመረ 5 ያህል ጳጳሳት መጥተው ከፊታቸው ቆሞ ድርሰት እንዲደርስላቸው ጠየቁት። ትሕትና ልግዱ ነውና ከእናንተ ፊት ቆሜ እንኳ ድርሰት መድረስ ያጠናሁትንም አዘኖዬ መናገር አይቻለኝም አላቸው እንኪያስ ይሆን .ተርጉመህ ንገረን ብለው የአራቱን እንሰሳ ስዕል አሳዩት። ታሪኩን አምልቶ ምሥጢሩን አስፋፍቶ ተርጉሞላቸዋል። ከዚህም በኋላ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል ብዙ ድርሳናት ደርሷል።

በኤፍራጥስና በጤግሮስ መካከል በምትገኘው በሥሩግም ኤጲስቆጶስነት ተሹሞ ላለ ለጌታ ሁሉት ባሕርያት አሉት 'በሚል የልዮን ትምህርተ ክህደ ከልቁዶን ጉባዔ

> 0451 ዓ.ም የተደረገ የእኛ ቤተክርስቲያን የማትተበለውና ጉባኤ ካሰባት ተብሎ የሚጠራ ነው። የጴጥ. ታሪክ በግሉም መድረክ ገጽ

636 ኤጲስ ቆጶሳት የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት ዲዮስቆሮስን አውግዘው በለዩት ጊዜ መናፍቃን በመሠለጠናቸው ዲዮስቆሮስም እውነተኛዋን ሃይማኖት ይዞ ሳለ በመለደጹ እነኑ ልዮንም ይተባበረኛል ብሎ ምስለኔ ብሎ ላከበት። እርሱ ግን በኤጥሮስ መንበር ተቀምጫለሁ ብለህልና ከከህደትህ ተመልስህ ንስሓ ገብተህ አንድ ባሕርይ በሚል ሃይማኖት ኤጥሮስን ብትመስለው አኔም እመስልሀለሁ፣ ይህ ካልሆነ ግን አንተ ዲያብሎስ ነህ ተከታዮችህም ኢጋንንት ናቸው ብሎ ነቅፎታል።
እንዲህ ሆኖ ኖሮ በተወለደ በ72 በተኛመ በ10 ዓመቱ በ438 ዓ.ም ዐርፏል።

ብለይና ሐጺስ የተጸፈበት
መዝገብ ነው ሰሊጻ ያፅቀብ በእውነት
ሞትና መቆምን በእግዚአብሔር ፊት
ጌታ ሊፈርድብኝ ፍርዱንም መስማት
ነፍሴን አስጨንቋት እኒህ ሰባት ግብራት
እያለ ሊያለቅስ በፅንባ ሊርስ ፊቱ

ገና በሰላት ዓመት በሕፃንነቱ
እዝነው አለቀሱ ሕዝቡ ካህናቱ
ከክሉት ርቀን በጎ እየሠራን
የዓለም ተድላ ደስታ ሳይታልለን
እንዘን ወንድሞች ስለነፍሳችን
የምንሞትብትን ቀኗን አስበን

ሲራ 28: 6፤3 መቃ 6:1

ሰኔ 30 ልደቱ ለዮሐንስ መጥምቅ

የተፀነሰው በቅዱስ ገብርኤል ብስራት መስከረም 26 ቀን ነው። በ6ኛው ወር እመቤታችን መልአኩ ኤልሳቤጥን እንተ እም እዝግድኪ ይዕቲኒ ጸንሰት ወረከበት ወልደ በልሀቃቲሃ ወብርስእቲሃ ብሏት ነበርና ኤልሳቤጥን ልትጠይቃት መጣች ኤልሳቤጥ የሰላምታዋን ድምጽ ስትሰማ እንፈርዐፀ እሳል በውስተ ከርሣ ይላል ጽንሱ በማኅፀኗ ሰግዷል። ኤልሳቤጥም መንፈስቅዱስ መልቶባት ቡርክት አንቲ እምአንስት ከሴቶች ተለይተሽ የተባረከሽ ነሽ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ የማኅፀንሽም ፍፌ ቡሩክ ነው፣ ወምንትኑ አነ ከመትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚየ – የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ የሰላምታሽን ድምጽ ስሰማ ጽንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሳልና ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምነበ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ተልከው የነገሩሽን ቃል እንዲሆን የምታምኚ ንዕድ ክብርት ነሽ ብላ አመሰግናታለች። እመቤታችንም ከርሳ ተቀብላ ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ብላለች 3 ወርም ከርሳ ጋር ቆይታለች።

እመቤታችን ወደ ቤቷ ከተመለሰች በኋላ ብዙም ሳትቆይ በዚህ ዕለት ኤልሳቤጥ ወለደች በሰምንተኛው ቀን ሊገዝሩት መጥተው ስሙን ማን እንበለው አሉ፤ ዮሐንስ ይባል አለች። አልቦ እምአዝግድ ኪ ዘከማሁ ስሙ – ከዘመዶችሽ በዚህ ስም የተጠራ የለም። እንደምን ይሆናል ብለው ዘካርያስን ማን ቢባል ትወዳለህ አሉት ብዕርና ክርታስ ሰጡት። ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ ብሎ 10ሩን ፊደላት ጽፎ እንደበቱ ተፈትቶለት ተግናሯል። ወዲያውም «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘተሣህለነ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ» ብሎ ጌታን አመሰገኗል፤ ሕፃኑንም ወእንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ እስመ ተሐውር ቅድመ እግዚአብሔር ከመትጺሕ ፍኖቶ - አንተም ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ትጠርግ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና ብሎ ትንቢት ተናግሮለታል። ሉቃ 1:39 – 79

➤ ይህ የተፈጸመው 5500ው ዘመን ሊፈጸም መንፈቅ ሲቀረው /በ1ዓ.ዓ አጋማሽ/ ነው።

ምዕራፍ 5

ሐምሌ 2 ታዴዎስ ሐዋርያ

ቀጸሚ ስሙ ልብድዮስ ነው፣ ወልብድዮስ ዘተሰምየ ታዴዎስ እንዲል ልብድዮስም ማለት ልብድ ሠሪ ዓሣ አሥጋሪ ማለት ነው፤ ልበድዮስም ይለዋል ካህነ አምላክ ማለት ነው። ታዴዎስ ማለት ዘርዕ ወማዕረር ማለት ነው አራትን በዘር ወንጌል ን በመከር መስሉ አስተምሯልና በነግህም ስንዴ ዘርቶ ለመሥዋዕት አድርሷልና። ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ከትዱስ ጴጥሮስ ጋር ለስብከት ወደ አፍራትያ ሲሄዱ አንድ ዝሬ ዘር ሲዘራ አገኙ ራበን አብላን ጠማን አጠጣን አሉት ቀደም ብላችሁ ቢሆን ነበር እንጂ አሁንማ ስንቁን ጨርሻለሁ፣ እንዳላመጣላችሁም ቤቷ ሩቅ ነው አላቸው እንዳለህ ብለን ነው እንጂ ብለው መለስ መለስ ሲሉ ደግ አላደረግሁም ብሎ ቆዩኝ ሳምጣላችሁ ብሏቸው ጥማዱን ፈቶ በሬዎቹን አሰማርቶ አገልግሉን መንቀሉን አንጠልሉ ወደ መንደር ሄደ። ታዴዎስ እየዘራ እርሱ እያረሰ ሁት ሶስት ጥማድ የሚያወጣውን ዘሩን አበርክተው ዘርተው ቆዩት ምግባቸውን ይዞ ሲመጣ ዘሩ ተዘርቶ አሽቶ አፍርቶ በሬዎቹም ለምለም ሣር ሲነጩ ጥሩ ውኃ ሲጎነጩ አገኘ። አግልክት ከሰማይ ወርደው ወደኔ መጥተዋል ብሎ እያደነቀ ያመጣውን መግቧቸው ጌቶቹ ወደ ቤት እንሂድ አላቸው። እንመጣለን ቀድመህ ሂድ አሉት። በሬዎቹን እየነዳ እሸቱን እየበላ ሲሄድ ጊዜው የዘር እሸቱን ከወዴት አገኘኸው? አሉት የሆነውን ሁሉ ነገራቸው ሰይጣን ከሐዋርያት ፊት ፊት እየሄደ በአሕዛብ ልብ እያደረ ትምህርታቸውን እንዳይቀበሉ እንዲያውም በእሳት ተኩሰው በደንጊያ ወግረው እንዲገድሏቸው ይመክር ነበር። እኒህንም በነፋሱ ቅናት አነሣሣቸው። የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ነን የሚሉት መሠሪያን ይሆናሉ ካሉበት አድርሰን አሉት። ይመጣላችኃል ከዜሁ ቆዩአቸው አሉ። እኩሌቶቹ እነሱ ሙት የሚያነሱ ድውይ የሚፈውሱ ናቸውና ተው አይሆንልንም ያጠፋናል አሉ ሌሎች ግን በምክንያት እናቸንፋቸዋለን ብለው አንዲት ዘማ በገንዘብ ገዝተው ራቁቷን ከከተማው በር አቆሙ እነርሱም ከዚያ ሲደርሱ ዕርቃኗን ጥላ ቢያዩአት ክፍታቸውን አውቀው በነፋስ አውታር ሲቅዘው እግዚኦ እግዚኦ አስብለዋታል። አይሆንልንም ብለው የነበሩት አይሆንልንም ተው ስንል እንቢ ብላችሁ እኛንም ልታስጠፉን ነው ብለው ይሸበሩ ይታወኩ ጀመሩ።

ከሞተ ኃጢአት የምትድኑበትን ልናመለክታችሁ እንጂ ልናጠፋችሁ አልመጣንም ብለው አስተምረው አሳምነዋቸዋል። ሴቲቱም ፍዳዋን ጨርሳ ወርዳለች ኋላም በተልዕኮ ስታገለግለው ኖራለች።

ቅዱስ ጴጥሮስ ከተመለሰም በኋላ በየሀገሩ እየዞረ በማስተማሩ ብዙዎችን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ከክህደት ወደ ሃይማኖት መልሷል። የሚመቀኘው አንድ መሠርይ ነበር። አስተምሮ ያሳመነውን አንድ ባለጸጋ በክርስቶስ ማመንህ ምን አገኛለሁ ብለህ ነው? አለው ገነት መንግሥተ ሰማያት እገባለሁ ብዬ ነዋ አለው። ክርስቶስማ ባለጸጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል» ማቴ 19:24 እያለ እንዴት ትገባለህ አለው? እርሱም ነገሩ ደንቆት ታዲያስን ባገኘው ጊዜ አባቴ እንዲህ ብለህ አስተምረህልን? አለው አዎን አለ። እንኪያስ አድርገህ አሳየኝ አለው። ያስተማረው አንጥረኛ ወዳጅ ነበረው። መርፌ ስደድልኝ ብሎ ላከበት። እርሱም ነገሩን አውቋልና ቀዳዳውን አስፍቶ ላከለት የመርፌ ቀዳዳ ምን ቢሰፋ ግመል ያሳልፋልን እንደነበረው አድርገህ ላከልኝ ብሎ መለሰው። እንደነበረው አድርጎ ሰደደለት መርፌውን አቁም ግመሏን ያሳልፋልን 3 ጊዜ አመላለሶ አሳይቷቸዋል። «ለትውልደ ትውልድ ጎሪት እስከ ተአምሩ ተጽሕፈ፣ ሰቀለ ብእሲተ በነፋስ ዘትዜሙ ዘልፈ፣ በስቁረቶ መርፍዕ ካዕበ – ገመለ አጎለፈ» እንዲል አርኪ። እንዲህ ባለ ሲያስተምር ቆይቶ በመጨረሻ በደንጊያ ተወግሮ ሞቷል።

ሐምሌ 3	ቅዱስ ቄርሎስ ሊቀ ጳ /ከ375 – 444 ዓ.ም/

ቄርሎስ ማለት ማጎቶት ማለት ነው። ሀገሩ እስክንድርያ ነው ሊቀጳጳሳት ቴዎፍሎስ አጎቱ ነውና እያስተማረ አሳድጎታል፤ እርሱም መንፈስ ቅዱስ መርጦታልና ወሰበ ይስምዖ ለቀለም ያጸንዖ በአሐዱ ጊዜ ወይመስል ከመዘቀዳሚ ተምህረ /ድርቁር/ ይላል ቀድሞ የተማረው እኪ መስል ድረስ የነገሩትን ቀለም ባንድ ጊዜ ይይዝ ነበር። እንዲህ አድርጎ በ5 ዓመት ብሉይ ሐዲስ አጥንታል። ከዚህ በኋላ ከአባ ሰራብዮን ሥርዓተ ምንኩስና ተምሮ አንባቢነት ሾመው ኋላም እርሱ ሲሞት ንጽሕናውን ተረድተው። በመንበረ

ማርቆስ 24ኛ ሊቀጳጳሳት አድርገው ሾመውታል። ተሹሞም ሳለ ብዙ ድርሳናት። ደርሷል ብዙ ተግሣጻት ጽፏል ቅጴሌም ደርሷል።

በዘመኑም የቁስጥንያ ሊቀጳጳስ ንስጥሮስ «ሕሰው ኬ ትስመይ ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክ ወእማኒ ትሰመይ ወላዲተ ሰብእ» በማለት የጌታን የአምላክነት የእመቤታችንን እመ አምላክነት ነቅፎ ተነሣ። ንጉሡ ቴዎድስዮስ ዘይንዕስ በኤፌሶን ጉባዔ ይሁን ብሎ አወጀ። 200 ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው በርሱ አፈ ጉባዔነት ተከራክረው አውግዘው ለይተውታል። /በ431 ዓ.ም/

ንስጥሮስ ከተወገዘ በኋላ ሳዕላይ ግብጽ ይኖር ነበር። የወንድም ፍቅር አገብሮት ካለበት ድረስ ሂዶ ወንድሜ የሚጎዳ መስሎህ ከሆነ እኔ ልጎዳልህ ጌታን አምላክ ወልደ አምላክ እመቤቴንም ወላዲተ አምላክ በል አለው እኔስ ግብፄ ተስማምቶኛል ይህን አልልም አለው። እመቤቴን ላዋርድ እኔንም አልታዘዝ እንዳልክ ላንተም አንደበትህ አይታዘዝልህ ብሎ ረገመው ወሞት እንዘ ይነብህ ከመ ከልብ ይላል ምላሱ ተጎልጉሎ ወጥቶ ከደረቱ ተንጠልጥሎ እንደውሻ ህዝ ህዝ እያለ ደምና መግል እየተፋ ሞቷል።

እሱም እንዲህ ባለ ግብር ኑሮ ለሊቀጳጳስነት በተመረጠ በ43 ዓመቱ በዚህ ዕለት ዐርፏል።

ለሊቀጳጳሳት ቅዱስ ቄርሎስ
እስኪ እንደፀቱ ስለምታ ታድርስ
መንፈስ ቅዱስ መርጦት ይሕንጎቱ
ይተረጎም ነበር ምሥጢር ይሕንደፀቱ
አዝማች ዚረጉሙ ስለደንገል ብሉ
የመርደት ሞት ሞተ ንስጥሮስ ነውሉ

ምላሱ እንደጡት ወጥቶ ተንጠልጥሎ
መቀረድን ሽቶ መጣል በሲኦል
አልመከር ያለ አሁንም ሞልቷል
ኃጢአት ሠርቼ ነፍሴ እንዳትጉዳ
አምላኬ እንዳስብህ በሠርክ በማለዳ
ታልሀን ጸፍልኝ በልቤ ሰሌዳ

ሐምሌ 5 ጴጥሮስ ወጳውሎስ

ሀ.	ቅ. ጴጥሮስ

ጴጥሮስ ማለት ኩኩሴ ሃይማኖት ማለት ነው አንተ ኮኾኑ ወላይ ዛቲ ኩኩሓ አሐንጸ ለቤተክርስቲያንየ እንዲል ማቴ 16:18 በዕብራይስጥ ኬፋ ይለዋል። ቀዳሚ ስሙ ስምዖን ነው፤ ትውልዱም

ከነገደ ሮቤል ነው። አባቱ ዮና ይባላል። የተወለደው በገሊላ አውራጃ በቤተ ሳይዳ ነው። ጸርቴዋ የምትባል ሚስት ነበረችው የሚተዳደረው ዓሣ በማጥመድ ነበር። ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር ዓሣ ከሚያጠምድበት ተጠርቶ ሐዋርያ ሆኗል። ማቴ 4:19

የዋህ፣ ፈጣን ቁጡ ነበር። የዋህነቱ ጌታ በባሕር ላይ ሲሄድ አይቶ ጌታ ሆይ አንተስ ከሆንክ ወዳንተ እንድመጣ አስናብተኝ ብሎ በባሕር ላይ ሊሄድ በመሞከሩ ማር 6: 45፣ ፈጣንነቱ ጌታ ደቀመዛሙርቱን በቂሣርያ ሰዎች ማን ይሉኛል ብሎ ጠ ይቋቸው ሙሴ ነው፣ ኤልያስ ነው ይሉሀል ባሉትና እርሱም መልሶ አንትሙስ መነ ትብሉኒ - እኛን ተስ ማን ትሉኛላችሁ ብሎ በጠ የቃቸው ጊዜ ጴጥሮስ ፈጥኖ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ አግዚአብሔር ሕያው የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ ብሎ በመመለሱ ማቴ 16:16 ቁጡነቱም አይሁድ ጌታን በያዙት ጊዜ ተቆጥቶ የሣልኮስን ጆሮ በሰይፍ በመቁረጡ ዮሐ 18:10 ታውቋል።

ጌታ «ይቀልል ይጎልፍ ገመል እንተ ስቁረተ መርፍዕ እምባዕል ይባዕ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ባለጸጋ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ገመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ብሎ ሲያስተምር ጴጥሮስ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ዋጋችን ምንድር ነው? ብሎ ጠይቆ ነበር። ጌታም አማን አብለክሙ አንትሙ እለተለውክሙኒ አመዳግም ልደት አመይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ዲበ መንበረ ስብሐቲሁ አንትሙኒ ትነብሩ ዲበ ዐሠርቱ ወክሌዔቱ መናብርት ወትኩንኑ ዐሠርተ ወክልዔተ ሕዝበ እስራኤል ብሎ ከወንድሞቹ ከሐዋርያት ጋር የሚያገኘውን ክብር ነግሯቸዋል። ማቴ 19:27 – 28።

ከለያልይ ባንዱም ኢትነውሙኑ - ጌታዬ እትተኛምን አለው የዕንቁ ጽዋ ውኃ መልቶ ሰጠው፣ ላይጠማው እንቅልፍ ያዘው። ጽዋው ከእጁ ወድቆ ተሰበረ ቢነቃ ጽዋው ተደቁሶ ውኃው ፈሶ አገኘ ደነገጠ። እኔም ይህን ዓለም የያዝሁት በመሀል እጄ ነው፣ መተኛት ማንቀላፋት ቢኖርብኝ ዓለሙ እንዲህ ተደቁሶ በጠፋ ነበር አለው እንደምን አድርገህ ትይዘዋለህ አለው? ዓለምን በመሀል እጁ ይዞ እሱን ከመሀል አድርጎ አይቴ ሀሉክ ኦ ስምዖን ወዴት አለህ? አለው፣ ኢየአምር እንዳኢ እንኛ ያለሁበትን አላውቀውም ብሎታል።

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ከሁሉ አስቀድሞ ቢክተለውም በሕማሙ ጊዜ ከሁሉ አስቀድሞ ክዶት ነበር። ጓላ ግን በንስሓ የሚመለስ ሁኗል። ማቴ 26:69 – 75 ጌታ ከማረጉም አስቀድሞ «ረዐይኪ አባግዕየ፣ ረዐይኪ መሐስዕየ፣ ረዐይኪ አባግዕትየ – በጎቼን ጠቦቶቼን ጠብቅ ብሎ በፍጹምነት በማዕከላዊነትና በወጣኒነት ያሉትን ሁሉ እንደ አባት ሆኖ እንዲንከባከባቸው አደራ ሠጥቶታል። ዮሐ 20: 15 – 17 ካረገም በጓላ በ10ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የሚያውቀው ጸንቶለት የማያውቀው ተገልጸለት ባንድ ቀን ስብከት 3000 ሕዝብ አሳምኗል። ሐዋ 2:41

ከጊዜያት ባንዱ ከዮሐንስ ጋር ለጸሎት ወደ ምኩራብ ሲገቡ እግሩ ልምሾ ሆኖ የተወለደ አንድ ሰው ስመ እግዚአብሔር ጠ ራባቸው። ወርቅሰ ወብሩር አልብየ እምዘብየሰ እሁበከ – ወርቅና ብር የለኝም ያለኝን ግን አሰጥሀለሁ። ናሁ በስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ ተንሥእ ወሑር - በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥእ ተመላለስ አለው ድኖ ተነሥቷል። ሐዋ 3:1 – 8

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በጓላ መጺናቸው ኢየሩሳሌምን 1 ዓመት በጎብረት ካስተማሩ በጓላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማድረስ ዓለምን ዕጻ በዕጻ በተከፋፈሉ ጊዜ ርእሰ ሐዋርያት ነውና ሮምን ደርበው ሠጥተውታል። እርሱ ግን ለሁሉ አባት ነውና ሐዋርያትን ሁሉ ከሀገረ ስብከታቸው አድርሰ

ሐዋርያተ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በጓላ መጺናቸው ኢየሩሳሌምን 1 ዓመት በጎብረት ካስተማሩ በጓላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማድረስ ዓለምን ዕጻ በዕጻ በተከፋፈሉ ጊዜ ርእሰ ሐዋርያት ነውና ሮምን ደርበው ሠጥተውታል። እርሱ ግን ለሁሉ አባት ነውና ሐዋርያትን ሁሉ ከሀገረ ስብከታቸው አድርሰ አለማምዶ ይመለስ ነበር። በሮም 25 ዓመት አስተምሯል፣ ከዚህ በፊት ግን በሰማርያ፣ በልዳ፣ በኢዮጴ አንጾኪያ፣ በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያና በቢታንያ አስተምሯል። በኢዮጴ ስምዖን ሰፋዬ አሣዕንን ሊቀ ሐራ ቆርነሊዎስን አስተምሯል ጣቢታን ከሞተ አስነሥቷል ሐዋ 9:36 – 42 በልዳም ኤንያ የተባለ የ 8 ዓመት የአልጋ ቁራኛ ፈውሷል። ሐዋ 9:32 – 34

በሰማርያም ሲያስተምር ሲሞን የሚባል መሠርይ ብዙ ወርቅና ብር አምጥቶ እኔም እጁን በሠጌነቡበት ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ ተአምር እንዲደረግ አድርጉልኝ አለ። «ወርቅከሰ ወብሩርከ ይኩንከ ለከ ለሕርትምና ይመስለከኑ ዘበወርቅ ትሣዖጠ ለጸጋ እግዚአብሔር - ጸጋ እግዚአብሔርን በወርቅ ትገዛለህን ወርቅና ብርህ ለጥፋትህ ይሁንልህ አልብከ ክፍል ውስተዝ ነገር – በዚህ ነገር ከኛ ጋራ እድል ፈንታ ተርታ የለህም በጽኑ ከህደት

ተይዘህ አይህለሁና አለው። ያም የማይሆንለት ቢሆን አንጾኪያ ወርዶ ያስት ጀመረ። ደቀመዛሙርትህን አሳተ ብለው ነገሩት። ዮሐንስን አስከትሉ ወረደ። መከራከር የማይቻለው ቢሆን ወደ ሮም ሄደ። ተከተሉት ሕዝቡን ለማሳት ለመሥዋዕት የቀረበውን በሬ በጆሮው ቢያንሾካሽክበት ከሁለት ተከፈለ ቅዱስ ጴጥሮስ ጠርተህ አምጣው ብሉ ቢባርከው አፈፍ ብሉ ተነሥቶ እያዳፋ አምጥቶታል። ያም በበኩሉ በምትሐት አጋንንትን ስቦ አንተን ቅስና አንተን ዲቁና ሹሜያቹሀለሁ ብሉ ለማረግ ሞከረ ጥቂት ከፍ ካለ በኋላ ጴጥሮስ ቢያማትብበት አጋንንት ጥለውት ሸሹ፣ እሱም ወድቆ ደቆ ቀርቷል። ኋላም ተከታዮቹ ትንሣኤ ሙታን የለም ጌታ ነፍስ አልነሳም ምትሐት፣ ሕድረት እያሉ ቢያውኩ 11 ዱን ሐዋርያት 72 አርድዕት ቅዱስ ጳውሎስንና የዕቆብ እኅው እግዚእን በኢየሩሳሌም ሰብስቦ / በ50 ዓ.ም/ በያዕቆብ ሊቀመንበርነት 43ቱን አናቅጸ ዲድያስቅልያ እንዲወስኑ አድርጓል። ከዚህም ሌላ ያስተማራቸው ምእመናን ከሃይማኖት ከምግባር እንዳይወጡ 2 መልእክቶችን ጽፎላቸዋል። የመጀመሪያውን በ54 ዓ.ም በባቢሎን 2ኛውን በ60 ዓ.ም በሮም ጽፎታል።

ንጉሡ ኔሮን ቄሣር መምለኪ ጣዖት ነበረ። በሃይማኖት ምክንያት አስሮት ነበር። አካይያ ዘምቶ ጠላቱን ድል ነሥቶ ሲመለስ ለጣዖት ስገድ ቢለው አልሰግድም አለ። በችንካር ተቸንክሮ በመስቀል ተሰቅሎ ይሙት ብሉ ፈርደበት ከዚያ በፊት አሕዛብ ሊጣሉት ሲነሱ ወደ ጌታ ሲያመለክት እሳት ከሰማይ ወርዳ ታጠፋለት ነበር አሁንም እሳት ከሰማይ ወርዳ ትብላቸው ብሉ ወደ ጌታ ቢያመለክት ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ታየው ሰቀሉከኑ ዳግመ በሮም ዳግመኛ በሮም ሰቀሉህን? አለ አንተ ብትፈራ እንጂ ነዋ አለው። ፈቃድህስ ከሆነ ብሉ እንደ ጌታዬ አቁማችሁ ሳይሆን ቁልቁል ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ አላቸው በራሱ ዘቅዝቀው ሰቅለውታል። ሥጋውንም ደቀመዝሙሩ መርቄሎስ ከመስቀሉ አውርዶ በወተት በወይን አጥቦ ሽቱ ቀብቶ በነጭ ሐር ገንዞ እንዳይፈርስ በሜር በተመላ ሣጥን አድርጎ ቀብሮታል።

መዋዕለ ስብከቱ 50 ዓመት ነው /ገድ ሐዋ ፡ ዜና ሐዋ/

ለ. ቅዱስ ጳውሎስ

ጳውሎስ ግለት ንዋይ ጎሩይ ግለት ነው «ንዋየ ጎሩየ ረሰይክም» እንዲል ሐዋ 9:15 አንድም ብርሃን ግለት ነው ኢጳውሎስ ግለት ብርሃን እንደሆነ ዘጻ 14:2 አንድም መድቅሕ ግለት ነው። ዶንጊያ በመዶሻ ተጠርቦ ለሕንፃ ሥራ እንዲውል አሕዛብም በርሱ ትምህርት ታንፀው ለገቢረጽድቅ ይበቃሉና ቀዳሚ ሰሙ ሳውል ነው፣ ሳውልም ግለት ጸጋ እግዚአብሔር ግለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ብንያም ነው። ፊል 3:5 አባቱ ዮስአል ይባላል። የተወለደው ጌታ በተወለደ በ5 ዓመት በጠርሴስ ነው። ከ15ቱ ዓመቱ ጀምሮ ኢየሩሳሌም በታላቅ እኅቱ ቤት ተቀምጠ ከመምህር ገማልያል ሕገ አሪትን መጻሕፍተ ነቢያትን ሲማር አድጓል ሐዋ 22:3 ለሕገ አሪት ቀናዒ ከመሆኑ የተነሣ ከርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ ወንጌልን ዲቃላ ሕግ እያለ ሐዋርያትን ይታወም ምእመናንን ያሳድድ ነበር። በወንጌል ያመነው ጌታ ባረገ በ8ኛ ዓመት ነው። «ወሳውልሰ ዓዲሁ ይትቁየም ይላል» ምእመናንን ለማሳደድ ከሊቀ ካህናት የሹመት ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ደማስቆ ሊሄድ መብረቅ ጣለበት፣ ደንግጦ ወደቀ ወዲያውም ሳውል ሳውል ለምንት ትሰድደኒ ለምን ታሳድደኛለህ? የሚል ድምጽ ሰማ። አንተ ማነህ አለ ምእመናንን ከዋሉበት አሳሳድር ካደሩበት አሳውል የምትልብኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ፣ ይብእስከ ረጊጽ ውስተ ቀኖት በሊህ የተሳለውን ሰይፍ ቢረግጡት የረገጠው ሰው እንጂ ሰይፉ ይጐዳልን፣ አንተስ እኔን ብትከድ ምእመናንን ብታሳድድ አንተ እንጂ -እኔ እጐዳለሁን አለው። አሁን ምን ላድርግ አለው ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባ የምታደርገውን ይነግሩሀል አለው። ከርሱ ጋር የነበሩም ድምጹን ይሰማሉ መልኩን ግን አላዩም፣ ከወደቀበት ተነሥቶ ዓይኑ ጠፍጅልና ሰዎች እየመሩት ቤቷ ይሁዳ አደረሱት እኅል ውኃ ሳይቀምስ። 3 ቀን ውሉ አድሯል።

ከ 72 ቱ አርድዕት አንዱ ሐናንያ በደማስቆ ይኖር ነበር ጌታ በራዕይ ታይቶ ጳውሎስን አሳምነህ አጥምቀው አለው ምእመናንን ከዋሉበት አሳሳድር ካደሩበት አሳውል የሚል አይደለምን አለ። እስመ ንዋየ ጎሩየ ሩሰይክም ሊተ - ምርጥ ዕቃ አድርጌዋለሁና ሂድ ይቀበልሀል አለው። ሄዶ ወንድሜ ሳውል

በመንገድ የታየህ ጌታችን ኢየሱስ ከፎስቶስ መንፈስ ቅዱስ ያድርብህ ዘንድ ወዳንተ ልኮኛል ብሎ ቢጸልሰው ዓይኑን ሸፍናት የነበረው እንደ ቅርፊት ተቀርፎ ወድቆለታል:: ሐዋ 9:1-19

ከዚህ በኋላ በክርስቶስ እመኑ እያለ ያስተምር ጀመረ አይሁድ ተደነቁበት በርናባስ በደማስቆ መጠራቱን በምኩራብ ማስተማሩን አይቶ ነበርና ከሐዋርያት ጋር አገናኝቶት ከርሱ ጋር የሚያስተምር ሆነ በልስጥራን ሲያስተምሩ ሽባ ሆኖ የተወለደ ሰው አግኝተው «ለክ እብለክ በስሙ ለእግዚአየ ኢየሱስ ክርስቶስ ተንሥእ ወቁም ቢለው እግሩ ጸንቶ ከወደቀበት ተነሥቶ ቆሟል ሕዝቡም ይህን አይተው «አማልክት ተመስሉ ሰብአ ወወረዱ ኀቤነ አማልክት ሰው መስለው ወደኛ መጥተዋል» ብለው መሥዋዕት ሊሠውላቸው ካሳሙ ወፈረውን መርጠው አመጡ:: ልብሳቸውን ቀደው ትብያ ነስንሰው እንደእናንተ ሰዎች ነን አማልክት አይደለንም ብለው ከለከሏቸው መሥዋዕቱን ትተው በወንጌል አምነው ተጠምቀዋል:: ስማቸውን ለውጠው ጳውሎስን ሄርሜን በርባባስን ድያ ብለዋቸዋል ሐዋ 14:8 – 18

አይሁድ ሰምቀኝነት አያርፋምና ነገር እየሠሩ ያሥሩት ይገርፉት ነበር:: በሶርያ በኪል ቅያ ሲያስተምር ሲሳስን ጨምረው ዝበያ ለዝበያ እየነተቱ ወስደው አሠሯቸው መንፈቀ ሌሊት ሲሆን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲዘምሩ «ወሰቤሃ ኮነ ዐቢይ ድልቅልቅ ወአንቀልቀሉ መሠረተ ቤተሞትህ» ይላል የእስር ቤቱ መሠረት እስኪናጋ ድረስ ኃይለኛ መናወጥ ሆሃ፣ ጠባቂው የመሠረቱን መናጋት የበሩን መከፈት አይቶ ወጥተው የሄዱ መስሎት የአለቆቹን ቁጣ ተሰቆ ራሱን ሊያጠፋ ሰይፉን መዘዘ፣ ቅጳውሎስ ሁላችንም አለን፣ አንድ እንኳ የጠፋ ሳይኖር ራስህን ትገድላለህን አለው በዚህ ምክንያት አምኗል:: ሐዋ 16:19 – 34

ቅዱስ ጳውሎስ የሚያስተምረው በጥበብ ነበር፣ ጣዖት የሚያመልኩትን መሞለኪ ጣዖት መስሉ አስተምሯል «ወኮንክዎሙ ለእለ አልቦሙ ሕግ ከመ ዘእልቦ ሕግ» እንዲል 1 ቆሮ 9:21 ይህስ እንደምነው ነው ቢሉ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከየሀገረ ሰብክታቸው ተመልሰው በኢየሩሳሌም ሳሉ ሄዳችሁ አንጸኪያ አስተምሩ አላቸው ዕረፍት ሽተው ነበርና በደመና አፋፍሶ አንጸኪያ አደረሳቸው:: ገብተው ሲያስተምሩ ሕዝቡ ፍቅረ ጣዖት አድሮባቸዋልና ጴጥሮስን ደብድበው ከእግረ ጣዖቱ፣ ዮሐንስን በደረቁ ላጭተው ከደጃፋ ጣሉት:: እሱ ካህነ ጣዖቱ የሚለብ ሰውን ለበብሶ እሱኑ መስሎ መጣ:: ዮሐንስን ከበር ወድቆ አገኘው አንተ ፍቁረ እግዚእ አይደለህምን ምነው ከዚህ ወድቀህል አለው:: እኔን አልክ እንጂ

ሊቀሐዋርያት ጴጥሮስም ተደብድቦ ከእግረ ጣዖቱ ወድቋል አለው ወደ ውስጥ ገብቶ መጥቅዕ ሙቶ ሕዝቡን ሰብስቦ ከቄሣር ተልኬ መጥቻለሁ እንዲህ እያሉ የሚያስተምሩ አሉና ይዛችሁ ስደዱልኝ ብሏል:: አላቸው:: እኛም እንጂ ይዘን ደብድበን ከዚህ ጥለናቸዋል አሉት:: ወዲህ አምጧቸው አሰና መጡ:: ምን እያላችሁ ታስተምራላችሁ? አላቸው ጌታ ከሰማያት ወረደ ከድንግል ተወለደ ሞተ ተቀበረ ተነሣ ዐረገ ዳግመኛ ይመጣል ብለን አሉት:: ድንግል ልትወልድ ሙት ሊነሣ ይችላልን ቀጣፊ ብሎ ጴጥሮስን በጥፊ መታው :: ወደቀደመ ግብሩ የተመለሰ መስሎት ተመየጥከኑ ጳውሊ ጎበ ዘቀዳሚ ግብርከ ወደ ቀደመው ግብህር ተመለስህን? አለ:: የምትሉት እውነት ከሆነ ሙት አስነሥታችሁ አሳዩን ብሎ የንጉሡ ልጅ ከሞተ 2 ወር ሆኖት ነበርና ከመቃብሩ ወሰዳቸው:: ጸሉት ጀመሩ:: አሱም በለሆሳስ ይጸልያል ሙቱ ተነሥቶ ማን አስነሣህ ሲሉት የቅዱስ ጳውሎስን መልክ ከአግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጸጉሩ ልትም አድርጎ ዘርዝሮ እርሱ አስነሣኝ ብሏል ተጠራጥረውት ስለነበር እንጂ የተነሣስ በሁሉም ጸሉት ነው በዚህም ሕዝቡ ሁሉ አምነው ተጠምቀዋል::

ሕሙማንንም ሕሙም መስሉ አስተምሯል:: «ወኮንክዎሙ ለድኩማን ከመድኩም ከመ እርብሐሙ ለድኩማን» እንዲል 1 ቆሮ 9:22 ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ታመምኩ ብሎ ከቤተ ሕሙማን ገብቶ 40 ቀን እኅል ውኃ ሳይቀምስ ሲጮህ ቆየ:: በ40 ቀኑ እናንተ በኢየሩሳሌም ተነሥቶ የነበረው ክርስቶስ ካመኑበት ያድናል ሲሉ ሰምቼ ነበር አላቸው:: እንኪያስ ካንተ የባሰበት የለምና እመንና ዳን አሉት፣ አመንኩ ብሎ ቢነሣ ሰውነቱ ተንቋቁቶለት ተጽናንቷል:: ይህን ይዘው አመነ በክርስቶስ እያሉ ከ 200 ያላነሱ ሕሙማን ድውያን ድነው ተነሥተዋል በወንጌልም አምነው ተጠምቀዋል::

ቃል ለቃል ከማስተማሩም ሌላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማዳረስ ከአንዱ ሀገር ወደሌላው ሲሄድ ምእመናን ከሃይማኖት እንዳይናወጹ ከገቢረ ጽድቅ እንዳይወጡ 14 መልእክታትን ጽፎላቸዋል::

ከዚህ በኋላ በ 69 ዓ.ም ሮም ገብቶ ሲያስተምር ንጉሡ ኔሮን ቄሣር አሥሮት ነበርና አካይያ ዘምቶ ጠላት ድል ነሥቶ ሲመለስ ጥሩት አለ፣ መስቀሉን በእጁ ይዞ ቀረበ፣ ተቆጥቶ በሰይፍ ቅጡት አለ፣ እንደ በግ እየነዱ ሲወስዱት የንጉሡ ልጅ አገኘቻቸው፣ አምና ነበርና መጉናጸፊያሽን ስጪኝ አላት ሰጠችው በዚያ ሽፋፍነው ሰይፈውታል:: ደሙም ሰማየ ሰማያት ወጥቶ ቀተሉኒ በዓመጻ እያለ

ተካሏቸዋል። «ደምከ ኤጥሮስ ወልደዮና በጽዋዐ መስቀል ተቀድሐ፡ ወደመ ጳውሎስ ሰማያተ እርሐ» እንዳለ ደራሲ አሱን ገድለው ሲመለሱ የንጉሥ ልጅ አገኝቻቸው ጳውሎስስ? አለቻቸው። በልብስሽ ሽፋፍነን በሰይፍ ጊያልነው አሏት። ልብሴን መልሰልኝ ከጴጥሮስ ጋር አሁን በዚህ ሲያልፍ እያየሁት ገደልነው ትሱኖላችሁን አለቻቸው ልብሷን አይተው አምነዋል። ተቆርጦ የወደቀ ራሱንም ከአንገቱ ቢያጋጥሙት እንደ ቀድሞው ሆኖላቸው ቀብረውታል። መዋዕለ ስብከቱ 42 ዓመት ሲሆን ሲያርፍ የ74 ዓመት አረጋዊ ነበር። /ገድ ሐዋ፣ ዜና ሐዋ/

➢ ቅ.ጴጥሮስና ቅ.ጳውሎስ የሞቱትም የተቀበሩትም ባንድ ቦታና ባንድ ቀን ነው። በብዙ መጻሕፍት ግን ያረፋት በ67 ዓ.ም እንደሆነ ተጽፏል ይህ ከሆነ ግን መዋዕለ ስብከታቸው ቀንሶ የጴጥሮስ 34 የጳውሎስ 26 ዓመት ብቻ ሊሆን ነው።

ብርሃናተ ዓለም ኤጥሮስ ጳውሎስ
ግደሪያዎች ናቸው ለመንፈስ ቅዱስ
የጠፋት ተገኙ ቀረቡ የራቁት
በኤጥሮስ ድንት ቃል በጳውሎስ ስብከት
ዓለም ተቀደሰች በነርሱ ትምህርት
ከጨለማ ወጣች ብርሃን ሆነላት
ወጥመቀት በቁርባን እኒህ ሐዋርያት
ከፈጣሪዋ ጋር ባያስታርቋት
ዓለም ትቀር ነበር ጨለማ ውሷት

እርሷ ግን ኡ ሥቀም ወዳጅ ጠላቷን
ከእልፍኝ አስቀምጣ በዛብኛ ባያቷን
ይጥፋልኝ ከፊቴ እልይ አነርሱን
ብላ ገፋቻቸው ኤጥሮስ ጳውሎስን
የወንጌልን ብርሃን ያበሩላትን
ከክህደት ግዞት ቤት ሰዎች እንዲወጡ
ቤዛ ሊሆኗቸው ነፍሳቸውን ሰጡ
ከንቱ ወረተኛ ናትና ዓለም
ለመልካም ሰው መልካም መቼም አትከፍልም

ዮሐ 15: 18 – 20 ፡ 17 :14

ሐምሌ 6 ዕዝራ

ሱቱ ኤልም ይለዋል፣ትውልዱ ከነገደ ሌዊ ነው አባቱ አዛርያስ ይባላል በምርኮ ጊዜ ፋርስ ባቢሎን ይኖር ነበር። ሚጠትን ሲሻ ቀኖና ቢገባ የበለጠ የጌታ ሰው መሆን ተገልያለት «አንበሳ ወጽአ እምገዳም ውእቱኪ ወልድ ዋሕድ» ብሉ ተናግሯል። ዕዝ

አንድ ቀን በጀርባው ተንጋሎ የኢየሩሳሌምን ጥፋት የእስራኤልን መገፋት ሲያሰላስል ልቡ ታወከበት ስምህን የሚጠራ አንተን የሚፈራ እስራኤል ስምህን በማይጠሩ ቃልህን በማያከብሩ ዐላውያን መገፋቱ የእስራኤል ኃጢአት ከባቢሎናውያን ከፋት በልጦ ነውን? ተመዝኖ ቢታይ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እንኳ በልጦ ባልተገኘ ነበር አለ። ቅዱስ ዑራኤል መጥቶ ድሉ እሳተ በመድሎት ወስፍር ነፋሰ በሳጻን አው ጸውዓ ለሰለት እንተ ትማልም ኀልፈት

እሳቱን በሚዛን መዝነህ ነፋሱን በሳፋን ሰፍረህ የትናንትናውን ቀን ዛሬ አድርገህ አሳየኝ አለው ሥጋ ለባሽ ይህ እንደምን ይቻለዋል? አለው እንዲሁ ባሕርየ እግዚአብሔርን በመመርመር ግዝፉ ማድረግ የሚቻለው የለም አለው። ወዲያውም መጻእያቱ ኃላፍያቱን የሚታየውን የማይታየውን ሁሉ ገልጸለታል። ሱቱ . ዕዝ 21.

ከዚህ በኋላ 6 ቀን ቅጠል ቀምሶ ደንጊያ ተንተርሶ በምድረ በዳ ተቀ መጠ። ጌታ በራዕይ ይነጋገረዋል። በገኖው ቀን ጽዮንን በእምሳለ ብእሊት አደርታታል። ልብሷን ተዳ አመድ ነስንሳ ታለቅሳለች፣ ምን ሆነሽል አሳት 30 ዘመን መከን ሆኜ ልጅ አጥቼ ሳዝን እየር ነበር፣ ከ 30 ዓመት በኋላ ጌታ ግዝኔን አይቶ ወንድ ልጅ ሥጠኝ፣ አክል ሥጠን ቢያደርስ ሚስት አጨሁለት፣ ወልድየ ቦአ ቤተ ሙርሃኩ ያቢያ ወድቀ ወሞት ወደ ሜንሳ ቤት ሲገባ ወድቆ ሞተብኝ በዚህ ምክንያት አዝኜ ከሀገሬ ወተቼ ከመንኖቼ ተለይቼ ወደዚህ መጣሁ፣ እንግዲህም ከምገብ ተከልክዬ በዚህ እኖራለሁ እንጂ ወደ ሀገሬ አልመለስም አለችው እኖ ታቦተ ጽዮን ጠ ፍታብን መምህራን ካህናት አልቀውብን እናዘናለን አንቺ ግን ለእንድ ልጅሽ ታለትሺያለሽ፣ ይልቁን ወደ ሀገርሽ ተመልሺ አሳት። ይህን ሲላት ድንገት አርአያዋ ተለውጦ መሠረቷ ጽኑ እንደ ፀሐይ የምታበራ ሀገር ሆና ታየችው። «አይቴ ሀሎከ አ መልአከ ዑራኤል - መልአኩ ዑራኤል ሆይ ወዴት አለህ? ብሉ ምኝ። ቅዱስ ዑራኤል ጭጥቶ ከወደቀበት አንሥቶ ያየውን ራዕይ – ያየህት ሴት ጽዮን ናት፣ 30 ዘመን ያለችህ መሥዋዕት ላይሠዋባት የኖረችበት 3000 ዘመን ነው፣ ልጄ ከሜንሳ ቤት ወድቆ ሞተ ያለችህም ሰሉሞን የሠራው መሥዋዕተ እግዚአብሔር የሚሠዋበት ቤተ መቅደስ መመዝበሩን ስትነግርህ ነው፣ ኃላም ፈጅ እንደፀሐይ ሲያበራ ማየትህ ሁለተኛ መታነጿን ሲያጠይትህ ነው ብሉ ተርጉሞበታል።

ከዚህ በኋላ ሕዝብህ ሕግህን እንዳያውቁ ሠርተው እንዳይጸድቁ መምህራን አለፉ መጻሕፍት ጠፉ ፈታድህስ ከሆነ ግለጽልኝና መጻሕፍቱን ላጽፍ ብሉ ወደ ጌታ አመለከተ። ሕዝቡን ተሰናብተህ ሶርያን፣ ደርብያንን፣ ሰላምያን፣ ኢሉናንና አሳሄልን፣ አስክትለህ ተመለስ አለው። ሕዝቡን ተሰናብቶ እነ ሶርያን አስክትሎ መጥቶ ከፍፍ ሥር ተቀመጠ ቅዱስ ዑራኤል ዕዝራ ዕዝራ አርጉ አፋክ አፍህን ከፈት የምሰተህንም ጠጣ ብሉ ጽዋዐ ሕይወት አጠጣው ያን ጠጥቶ ያለፈው የሚመጣው ሁሉ ተገልጸለት የብሉይ መጻሕፍትን በ40 ቀን አጽፏል። አንሰ በውዕቶን መዋዕል ኢበላዕኩ አክለ ወኢሰተይኩ ማየ እሙንቱሰ መዓልተ ይጽሕፋ ወሠርክ ይዴረሩ ይላል እነሱ ቀን እየጻፉ ምሽት ይመገባሉ እርሱ ግን ሌሊት የሚያጽፋቸውን እያሰበ ቀን እየተናገረ ያጽፋቸው ነበርና እኅል ውሃ አልቀመሰም ከ40 ቀን በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ የጻፈውን አንብበላቸው

ሥርዓት ሠርቶላቸው ከፈጸመ በኋላ መላእክት በአካለ ሥጋ አብርገው ብሔረ ሕያዋን አግብተውታል። ዕዝ. ሱቱ. ምዕ.13 በ፦ሉ

➤ የጻፈው ታሪክ በዘመኑ ከ537 – 458 ዓ.ዓ / የተፈጸመውን ነው።

ሐሙስ 7 – በዓለ ቅድስት ሥላሴ

ሥላሴ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ቅድስት የሚለው ስያሜ ለምን እንደተቀጸለባቸው፣ እንድነትና ሶስትነታቸው እንዴት እንደሆነ፣ በማይመረመር ጥበብ ፍጥረታትን መፍጠራቸውን፣ ባሕይያቸው ቢሕግም በሞት የማይለወጥ መሆኑንና በኖኅ ዘመን በንፍር ውኃ ከዚያም በኋላ በክሉስ በሉጥ ዘመንም በእሳት በመጸዋቸን መቅጣታቸውን በክፍል 1 መጽሐፋችን መግራችን ይታወሳል። / ገጽ 144 / በዚህ ክፍል ደግሞ ወደ አብርሃም ቤት መግባታቸውን እንግራለን።

አብርሃም ቤቱን ከተመሳቀለ ጎጻና ሠርቶ የወጣ የወረደውን ያለፈ ያገደመውን እንግድነት ሲቀበል ይኖር ነበር። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ፈተን እንግድነት ከከበሰ ከመንገድ ቆይቶ እንግዶቹን ወዲት ትሄዳላችሁ? ይላቸዋል፣ ርቦን ሊያበላን ጠምቶን ሊያጠጣን ከአብርሃም ዘንድ ይሉታል፣ የወትር አብርሃም መሰላችሁን እኔም እንደናንተ ርቦኝ ያበላኛል ጠምቶኝ ያጠጣኛል ብቤ ብሄድ ፈሴን ገምሶ አጥንቴን ከከክሶ ሰደደኝ ይላቸዋል እያዘኑ በመጡበት ይመለሳሉ። እንዲህ አድርጎ 3 ቀን ሙሉ እንግዳ ከለከለበት አሱም ያለምከበር ግብር አላገኝም ብሉ ሳይመገብ ቆይቷል።

በሶስተኛው ቀን በቀትር ከድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሥላሴ በለምሳለ እይው በመምሬ አድባር ዛፍ /

> በአብርሃም ወዳጅ በአሞራዊው መምሬ ስም የተሠየመ
> በኬብሮን አጠገብ ያለ ታላቅ ዛፍ ዘፍ 13:18 1 14:13

ሥር ተቀምጠው ታዩት። ሄደ ኸሡ አጋፅዝትየ ቤቷ ገብርከሙ አብርሃም ጌቶቹ ከዚት ገብታችሁ እረፉ አላቸው። ደከሞናልና አዘለን አሉት። እንዴን እንሹ ቢገ ሁለቱ በግብር አምሳካዊ ገብተው ተኝተዋል። እሱም ሶስት እንደሆኑ አውቆ ሳራን 3 መስፈሪያ ዱቄት ወስደሽ አንድ እንጎም አድርገሽ ጋገሪው አላት፣ ጋገራ አቀረበች፣ እርሱም ወይፈን አርዶላቸው ወተት እርጎ ጨምሮ አትርቦላቸው ተመገበዋል፣ አቅረበ ሱሙ ሐሊበ ዕፀነ ወዕጉለ ሳህም / / እንዲል። መብላቸው ግን እሳት ቅቤ በላ እንደ ማለት ነው። ይህንንም ሲያጠይቅ አርዶ አወራርዶ ያቀረበው ወይፈን ተነሥቶ «ሰብሐት ለአብ ሰብሐት ለወልድ ሰብሐት ለመንፈስ ቅዱስ» ብሉ አመስግኗል። «ድኅረ በላዕኩሙ ሳህሙ አንበይነ ፍቅረ ሰብእ ፍጹም፣ ዘበኃይለክሙ ሐይወ ሳህም፣ ሥላሴ ክቡራነ ስም»እንላለ ደራሲ።

በሚሄዱም ጊዜ ከሳቱ አንዱ እግዚአብሔር ቃል አመ ከመቅደ እትፈቅ ገጽክ የዛሬ ዓመት እንደዛሬ ወዳንተ እመለሳለሁ ሚስትህ ሳራ ወንድ ልጅ

ትወልድልሀለች ብሉ ለጊዜው ልደተ ይስሐቅን ፍጻሜው ግን ሰው ሆኖ የሚያድነው መሆኑን ነገርታል። ዘፍ 18: 1 – 15

➤ ታሪኩ የተፈጸመው በ2000 እና በ1850 ዓ.ም መካከል ነው።

ለ. ዕረፍቱ ለአባ ሊኖጳ

ሊኖጳ ማለት ተአምኒ ማለት ነው። ሀገሩ እስክንድርያ ነው። አባት እናቱ በንባል የሚባል ቦታ ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን እናቱ ውኃ ልትቀዳ ስትሄድ አባ ክርስጣርኮስ ደቀመዛሙርቱን አስከትሉ ሲሄድ አገኛት፣ ቡርክት አንቲ ወቡሩክ ፍሬ ክርሥቲ - ለቀደሙት ቅዱሳን ወንድማችው ለጓለኞችም አባታቸው የሚሆን ቡሩክ ፍሬ በማነገሽ አለና የተባረከሽ ነሽ ብሉ 3 ጊዜ ራሷን ሳማት። ደቀመዛሙርቱ አባታችን ሴት አነጋገር አያውቅም ነበር ዛራ ምን ሆኗል? አሉ ይህን አውቆ የልጇን ክብር ነግሯቸዋል።

ያደገው ያባቱን በጎች ሲጠብቅ ነው። ሌሊት መንጋውን አስማርቶ እሱ ከጉድጋድ ገብቶ ሲጸልይ ያድር ነበር። እንድ አረጋዊ ከጉድጓድ ገብቶ ሲጸልይ አሥሩ ጣቶቹ እንዳፋና ሲያበሩ አይቶ አባት እናቱን እንዲህ ያለ ደግ የወለዳችሁ ምን ብዙዓን ናችሁ አላቸው እንዲህማ ከሆነ የእግዚአብሔር እንጂ የኛ አይደለም ብለው ለመሾር ሰጡት ሲሰጡትም ናሁ ይሰመይ አርስመቅሪዶስ ለኩሉ ዓለም እዝሃ የኀሕታውያን ራብ ይባላል የሚል ድምጽ ከመደላይ ተሰምቷል።

ከዚህ በኋላ እየተግሪ እያገለገለ በለም በጨሉት ተወስኖ በትጎርምት ኗሪ ቢሆን መልእክቱ የኤልያስን አስኬማ የዮሐንስን ቅናት ሲሰጠው መምህሩ በራዕይ አየ፣ በማሥጠም የሰጠሀን ለሲኖጳ አልብሰው አለው መዓርገ ምንኩስና ሰጠቶታል። ጓዳም እሱ ይህን መንፈሳዊ ሀብት ለሌላው የሚሰጥ ሆኗል።

በ431 ዓ.ም ለአውግዙተ ንስጥሮስ በቁስጥንጥንያ በተደረገው ጉባኤ ቅዱስ ቄርሎስን ተከትሉ ተገኝቷል። ንስጥሮስን አውግዘው ሃይማኖት መልሰው ሲመለሱ መርከባቸው ሊቀጸጸላቱ በተሳፈረበት መርከብ አትሳፈርም ብለው ከለከሉት፣ ጌታ ብሩህ ደመና አሥለት በዚያ ተጭኖ ሲሄድ በመርከቡ አንጻር ሲደርስ የመርከቡ ጣሪያ አንደመስታውት ሆኖላቸው አሱና ሊቀጸጸላቱ ተያያተው እጅ ተነሣስተዋል። እኒያም ክብሩን አይተው ደግ ሰው አስተይመናል ብለው ተጸጽተዋል።

በመጨረሻም በክሎ ጥርቅ ውኃ ለደኃ አስከመከጠት ድረስ በክሎ በጎ የሠራውን እንደሚያርሰት ጌታ ቃል ኪዳን ወተቶት ሕማም ደካም ሳይሰማው በተወለደ በ120 ዓመቱ ዐርፏል።

➤ የክበረው በ5ኛ ምዕ ዓመት ድ/ል/ክ ነው።

ለዛም ለሊናጳ ክህነ ለውል	መጣለት ደመና አምላክ ለክለት
ዋሔም ተከራሚ ሰጪ ወንጌል	ፈተኖ አንዲያደርሰው ከሚኖርበት
ዘውትር ሲተጋ ያገንባች ፈርዩት	ሬጣሪም አንደበው ቢዓት ደኃውን
ተኑን ለተሰዶት ሌሊት ለጸሉት	ምን ይሰና ነበር የእኛን ገበን
አሥሩ ጣቶቹ ሙጎሰት መብራት	ጸሩ ግን ሰው እንጂ እርሱ አይንተውም
በውስጥ የለበሰው የፀርያን ልብሱን	ይደጋገሪዋል ሊወድት ቢፍገሙም
ሳይመለከቱ አይተው ጳውን	ደኃን ስለሌሰ መኖት አይኝም
መርከብ ለመሳፈር ሰዎች ቢነፍጉት	ሰው በሥራዉ እንጂ ዕልበስ አይለኩም

ምሳ 22:9 ሲራ 10:23

እናታቸው ደግ ክርስቲያናዊት ነበረች፣ መልአክ ከልጆችሽ አንዱን ጌታውን እንዲያገለግለው ሰጪኝ ሲላት፣ እርሷም ከ7ቱ የመረጥከውን ውሰድ ስትለው የብሶዬን ራስ ይዞ «ዝ ውእቱ ኅሩይ ለእግዚአብሔር» ሲላት ራዕይ አይቻለሁና ከሌት ርቀህ ንጽሕ ጠብቀህ ጌታህን አገልግል ብላ አሰናበተቻቸው። ገዳመ አስቄጥስ ገብተው የአባ ባሞይ ሪድዕ ሆነው በጸም በጸሉት ተወስነው ሲኖሩ መናንያኑ በጸሎቱ ይጠብቀናል በትሩፋት ያጸድቀናል ብለው ለሹመት መርጠዋቸዋል።
ከገዳማውያን አንዱ ባሕርየ ሥላሴን ሲመራመር መንፈስ ቅዱስ የሰም አለ እርሳቸው በምሳሌ አስተምረውት ተመልሷል። አንድ ቀንም ሲጸልዩ ዘሰጠ ንጢናስ በአክናፈ እሳት ወደ ኢየሩሳሌም ሰግደዋት ሲያርጉ አይቶ በአካለ ነፍስ መጥቶ «ሰላም ለክሙ እ ብፁዓን መነኮሳት አላቸው፣ » አንተም እንጂ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቆሚልና ብፁዕ ነህ» አሉት የመነኮሳት ክብራችሁ እንዲህ መሆኑንስ ባውቅ መንግሥቴን ለቅቄ ከዚህ ወድቄ ዳዋ ጥሼ ቤዛ ልሼ በኖርሁ ነበር ብሎታል ከሄደ በኋላ ደቀመዛሙርቱ አባታችን ከማን ጋር ትነጋገር ነበር? አሉት ቄስጠንጢናስ በአካለ ነፍስ መጥቶ እንዲህ አለኝ እኔም እንዲህ አልሁት ብለዋቸዋል። ከትሩፋታቸውም የተነሣ ጌታ እንግዳ መስሉ መጥቶ እንግድነት ተቀብለውታል፣ እግሩንም አጥበዋል።
የአበሩት በ 5ኛው ም. ዓመት ድ/ል/ክ ነው።

ሐምሌ 10 – ናትናኤል ሐዋርያ

ናትናኤል ማለት ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው። ቀዳሚ ስሙ ስምዖን ነው። ትውልዱ ከነገደ ብንያም ነው። የተወለደው በቃና ነው፣ ወስምዖን ቀናዊ እንዲለው ማቴ 10:4 ኦሪቱ ቀለዮጥ ይባላል። ጌታ በተወለደበት ዘመን ተወልዷል። ወደጌታ ያቀረበው ፊልጶስ ነው። ሙሴ በኦሪት የጻፋለትን ነቢያት ትንቢት የተናገሩለትን መሲሕ ክርስቶስን አግኝነው አለው በውኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ሊገኝ ይችላልን አለው። «ነግ ትርአይ – መጥተህ እይ አለው። ቢሄድ ጌታ «ነዋ ዘበአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሑት ውስተ ልቡ - ክፉት ተንኮል የሌለበት እስራኤላዊ እነሆ አለ። ከወዴት ታውቀኛለህ አለው። ሄሮድስ በጌታ ምክንያት በቤተልሔም 14 እልፍ ከ 4 ሺህ ሕፃናት ባስፈጀ ጊዜ እናቱ በተፎ አድርጋ ከበለስ ሥር ደብቃው ነበርና ያን ጊዜ ከሞት ያዳንኩህ እኔ ነኝ፣ የበለስ ቅጠል ሰፊ እንደሆነ ኃጢአት ሰፍኖብህ አንደነበር አውቅህለሁ ሲለው ነው። እሱም «ረቢ በእማን አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ወንጉሠ እስራኤል - በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ የእስራኤልም ንጉሥ ነህ» ብሎ አምኖ ተከትሎታል።

ሀገረ ስብከቱ ሰሜን አፍሪካን ይዞ ግብጽ ድረስ ነው። ከዚያ ገብቶ ሲያስተምር ሕዝቡ ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው አመኑ ተጠመቁ። ጥቂት መፍቀርያነ ጣዖት ተመቅኝተውት ከንጉሥ እንድርያኖስ ነገር ሠርተው አጣሉት። ጠርቶ ሲጠይቀው ሳይፈራ የጌታን ልደቱን ጥምቀቱን፣ ሞቱን ትንሣኤውን ፣ ዕርገቱን ዳግም ምጽአቱን ተርትሮ ዘርዝሮ ነገረው። ግን ፈቀደልህ ብሎ ተቆጣበት፣ አንተንም እኔንም የፈጠረ እርሱ ነው አለው። በዚህ ምክንያት በሰይፍ አስመትቶት ዐርፏል።

ሐምሌ 12 በዓሉ ሊቀ - ሚካኤል ሊ.ቀ.መ

በዚህ ዕለት ሕዝቅያስን ሊረዳ ተልኳል

ወእመ ዐሠርቱ ወአርባዕቱ ዓመተ መንግሥቱ ለሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ ዐርገ ሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ኀበ ሕዝቅያስ 2 ነገ 18:9 የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ በይሁዳ በነገሠ በ14 ዓመት የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም ወደ ኢየሩሳሌም ዘመተ። እስራኤል ኃጢአት እየሠሩ ጣዖት እያመለኩ እግዚአብሔርን አሳዝኑት ነበርና ሊያጠፋ ታዞ መጥቷል። 2 ነገ 18:25 2 ነገ 19:25

ከዚህ በኋላ ራፋስቂስንና ራፋሰርስን ላካቸው። ከቅጽሩ ሆነው የሕዝቅያስ ብላቴና ብለው ተጣሩ፣ ሕዝቅያስ የሚናገሩትን ብቻ ሰምታችሁ ኑ ብሎ ሳምናስን ዮአስንና ኤልያቄምን ሰደደ።

በልም ለሕዝቅያስ በመኑ ተወኪለከ ዐለውከኒ በበትረ ባሕሩስኑ ቅጥቁጥ እንተ ግብጽ ወሰብ ተመርጉዘ ቡቱ ብእሲ ይሰብር ወይበውእ ሥርዋጽ ውስተ እዴሁ መክዖ ይቁስል ወይሙት በማን ተምኖህል ሸንቡቆ ቢመረኩዙት ተሰብሮ ስንጣሪው ከእጅ ገብቶ አቁስሉ ይገድላል፣ የግብጽ ንጉሥ ሳጎልም እንኳ ሌላውን ራሱንም አያድንም፣ አሁንም ሰግዶያን እንጸጠፋሁ ኢየሩሳሌምንም አጠፋታለሁ ፈጣሪ አለኝ የምትሰው ያድንህ መስሉህ ድንኳንህን ቆልፋህ ደጅህን ዘግተህ ቆየኝ ብሉህል በሉት አሏቸው ፊታቸውን ቅሎም አድርገው ገብተው ነገሩት እንዲህ ያለ ጠላት በጸሉት እንጂ በጦር አይመለስምና ሄዳችሁ ለአቢዶ ለኢሳይያስ ንገሩት አላቸው። ነገሩት።

ኢሳይያስ ሲጸልይ የሚሆነው ተገልጸለት አይዞህ ከከተማ ሳይደርስ በመጫበት ይመለሳል ብሎ ወደ ሕዝቅያስ ላከ። ከዚህ በኋላ ሰናክሬም አልፎ በለኪሶን ሰፈረ ሌሊቱን ቅዱስ ሚካል ሰደፈ መላኩን መሥ ቢታያቸው ከ14 እልፍ 5 ሺህ የበዙ ሠራዊት አንቀላፍተው ተገኝተዋል። እርሱንም መላእክት የነጋሪት ድምጽ የፈረስ ኮቴ እያሰሙት ሕዝቅያስ መጣብኝ ብሎ ልብሱን ዘውዱን ጥሎ እየሮጠ ወደ ሀገሩ

ተመልሷል። ዘውዱን ኣቢያት ካህናት እግኝተውት ለሕዝቅያስ አቀዳጅተውታል።
ሰናክሬም ከዚቱ ደርሶ ለሣያቱ ሲሰግድ ልጆቹ አድራማ ሌኸና ሶርሶር ሠራዊቱን ወዴት ጥለህ መጣህ? አሉት፣ የሕዝቅያስ አምላክ ፈረደብኝ ሞቱ አላቸው ኃያላኑን ሁሉ ለቃቅሞ ወስዶ ነበርና ያን ያህል ሠራዊት አጥፍተህ ዳግመኛ በማን ላይ ልትነግሥ መጣህ? ብለው ወይከውን መቃብሪከ ታሕተ እግረ ስብኽከ ተብሎ ትንቢት ተገማርበት ነበርና ከጣያቱ ሥር እንዳለ በዘነዘና ቀጥቅጠው ገድለውታል። «ወእንዘ ይሰግድ ውስተ ቤተ ሊድራከ አምላኩ፣ ቀተልዎ አድራማሌክ ወሶርሶር ዝኩ» እንዲል አርኪ።እንዲያጠፋ ታዞ ከመጣማ ለምን እንዲህ ሆነ ቢሉ ኃጥአኑን ሊያጠፋ እንጂ በእግዚአብሔርና በደጉ ንጉሥ ላይ እንዲገዳደር አልነበረምና ነው፣ ዳግመኛም ሕዝቅያስ ተመለስልኝ ብሎ 300 መክሊት ብር 30 መክሊት ወርቅ ከሰጠው በኋላ ሁለተኛ በማን ተማምነህል? ብሎ ዘብቶበታልና ስለዚህ ነው።

ታሪኩ የተፈጸመው በ 701 ዓ.ዓ ገደማ ነው።

ያላንጻች ጥርጥር በአምላክ መታመን
መገሰጫው ይህ ነው የበጎው ምእመን
በእምነት ወደ እምላኩ አንገቱን ያቀና
ድል ያደርጋል እንጂ አይወድቅ በፈተና
በኃይለ ግሥራዊት በብይፍ በጦር
ፈጽሞ አይድንም የሰው ልጅ በምድር
ግና በሃይማኖት የጸና ምእመን
ሳይሞት ይገድለዋል ባለጋራውን

ጠላት ተነግብኝ ብለህ አትደንግጥ
ይልቅ ሆኅብህን ለአምላክህ ስጥ
እርሱ ያድንህል ሳያዘገይ በቶሎ
ከቆፈረው ጉድጓድ ጠላትህን ጥሉ
ሹመት አለኝ ብሎ ከታበየ ሹሙ
በወርቅና በብር ከተመካ ሀብታሙ
ዝንኛም ከኩራ በዝነኛ ሰሙ
እኒህ ራሳቸውን ሰውንም አይጠቅሙ
እንደ ነቀዘ ግንድ ሳይወድቁም አይከርሙ።

መዝ 36:35 ምሳ 16:5 ሲራ 10:9

ሐምሌ 15 – ኤፍሬም ሶርያዊ /ከ306 – 373 ዓ.ዓ

ሀገሩ ሶርያ ነው የያዕቆብ ዘንጽቢን ደቀመዝሙር ነው። ያዕቆብ ዘንጽቢን ለአውግዞተ አርዮስ ወደ ኒቅያ ሲሄድ አስከትሎት ሄዶ ነበር። አርዮስን አውግዘው ሃይማኖት መልሰው ካደሩበት ሌሊት ዓምደ ብርሃን ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ ብርሃኑ በዓለሙ መልቶ ራዕይ አየ። ባለቤቱን ግለጽልኝ ብሎ ቢያመለክት የታዘዘ መልአክ መጥቶ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ነው የሰውን ልቡና በትምህርቱ ብሩህ ያደርጋልና እንዲህ ባለ አርአያ አየኸው

ለመረዳት ቂሣርያ ሄደ። በወርቅ ወንበር ተቀምጦ በወርቅ አትሮንስ የወርቅ ወንጌል አዘርግቶ ኩፋር ጠምጥሞ ካባ ላንቃ ለብሶ እጀታው የወርቅ የሆነ የሐር መነሳንስ ይዞ ሲያስተምር አገኘው። ወተሐዘበ ልቡ ለኢፍሬም ከመሥጋዊ ውእቱ ይላል፣ እርሱ መሆኑን ተጠራጠረ አራት ነገር አይቶ ይረዳል። መጀመሪያ ከአፋ ነጸብራቁ እስሳት እየወጣ ሕዝቡን ሲዋሀጻቸው ያያል ትምህርቱ ነው፣ ሁለተኛ ተሐዋስያን ከልብሱ ላይ እያረፋ እንደ ቆሉ ሲረግፉ፣ ሰባተኛ ነጭ ርግብ መጥታ በራሱ ላይ ስታርፍበት ያያል አራተኛ ስሙን ያውቅ ሀገሩን ያይጠይቅ ኤፍሬም ሶርያዊ ኤፍሬም ለብሐዊ ብላችሁ ጥሩልኝ ከማዕዘነ ቤተ. ክርስቲያን ባንዱ ቁሞ ይጸልይላቹህል ብሎ አስጠራው እያደነቀ ቀርቦ የባስልዮስ ቋንቋ ለኤፍሬም የኤፍሬም ቋንቋ ለባስልዮስ ተገልጸላቸው ሲጨዋወቱ አድረው ሲነጋ አሰናብተኝ ልሂድ አለው። ልትኖር እንጂ ልትሄድ አምጥቶህልን ብሎ ሕዝባዊ ነው ቢሉ ዲቁና ዲያቆን ነው ቢሉ ቅስና ሹሞ ከሀገረ ስብከቱ ሀገር ከፍሎ አስተምር ብሎ ሰጠው። ባስልዮስ ይህን መልዕኩ ስለ ክብረ. ወንጌል ነው። ዛሬ ካህናት አክሊል ደፍተው ካባ ላንቃ ለብሰው ሥጋውን ደሙን እንዲያከብሩ እንዲለውጡ። እሱ ግን በውስጠ'ሚለብሰው ግት ነበረ።
ለብሕዊ የተባለው ሞ ቢረሱ መርጠብ ብርጭቆ ኩዝ ካባ እየሰራ ሽጠ የዓመት ልብሱን የዕለት ጉርሱን እያስቀረ ሌላውን በእመቤታችን ስም ይመጸውት ስለነበር ነው። እመቤታችንን ከመውደዱ የተነሣ የእመቤቴ ምስጋናዋ እንደ ሰማይ ከከብ እንደ ባሕር አሸዋ በዝቶልኝ እንደ ልብስ ለብሼው እንደ ምግብ ተመግቤው ጠግቤው እንደውኃ ጠጥቼው ረክቸዉ እያለ ሲመኝ ይኖር ነበረ። የሹትን መግለጽ ለመንፈስ ቅዱስ ልግዱ ነውና ገልጸለት እልፍ ካራት ሺህ ደርሶት ደርሷል። አኃዝ እግዚእ መዋግደ ጸጋከ. እስኪል ድረስ። ጸሎቱም ከወንጌለ ሉቃስ ወበሳድስ ወርኅን ጸሎተ እግዝእትነን እውጥቶ 64 ጊዜ ይደግም ነበር። ከጊዜያት ባንዱ ዕለቱ ሰኑይ ጊዜው ነግህ ነው። የነግህ ተግባሩን አድርሶ ከመካነ ግብሩ ተቀምጦ ላለ እመቤታችን ትመጣለች የብርሃን ምንጻፍ ይነጽፋል የብርሃን ድባብ ይዘረጋል። ከዚያ ላይ ሁና ሰላም ለከ ኦ.ፍቁርየ ወፍቁረ ወልድየ ኤፍሬም ትለዋለች ታጥቆ እጅ ነስቶ ይቆማል። ወድሰኒ ትለዋለች። እፎ እክል ወድሶ ተኪ ዘኢይክሉ ሰማያውያን ወምድራውያን ሰማያውያን መላእክት ምድራውያን ጻድቃን ሰማዕታት አንቺን ማመስገን የማይቻላቸው ለእኔ እንደምን ይቻለኛል አላት። በከመ አለበወከ መንፈስ ቅዱስ – መንፈስ ቅዱስ እንዳቀበለህ ተናገር አለችው። ባርከኒ ይላታል በረከተ ወልድየ ወአቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ይኅድር በላዕሌከ ትለዋለች። ተብርኮ እንዳጸናው ቀለም ሰተት አድርጉ አመስግኗል። ስታስደርሰውም በሰባት ክፍላ አስደርሳዋለች። ምስጋናውም የሰባቱ ዕለታት ወጸሊ ማርያም ነው። ዜማውን ቅዱስ ያሬድ ደርሶታል። ገጽ - ተመልከት ሲጨርስም

በያዘችው መስቀሉ ብርሃን ባርነው ተስፋውን ነግራው ወርጋለች። እሱም የበለጠ ሲያገለግላት ኑሮ በዚህ ዕለት ወርዷል።

ሰላም ላንተ ኤፍሬም ደግ አባት ቅዱስ
ከእሾህ ግንድ ላይ የበቀልህ በለስ
ፍሬም ደስ እንዲለን ጠጥተን ረከተን
ውዳሴ ማርያምን አደልትህልን
ከማርና ወተት የጣፈጠውን
የድንግል ውዳሴ ነውና ምግብህ

ጠንክረህ በመንፈስ ኃይልም አገኘህ
እስኪሸሽህ ፊርቶ ሰይጣን ጠላትህ
ወደርሱ እንዲያቀርብኝ እምላክ በምሕረት
በአንተ ልሙና በአንተ ጸሎት
ልጅህ የሞህ ልሁን በልቤም ትሁት

ቆላ 3:12

ሐምሌ 18 ለያዕቆብ እጉሁ ለእግዚእን

ያዕቆብ ማለት አዕቆጼ ሰኩና ማለት ነው። በትምህርቱ የአይሁድን ትምክህት ምጽድቅ ይነቅፋልና እጉሁ ለእግዚእን ይለዋል። ዝምድናውን አይቶ አልአዛር ቅስራንና ማትያንን ይወልዳል ቅስራ ኢያቄምን አያቄም አመቤታችንን አመቤታችን ጌታን ወልዳለች። በአንጻሩ ማትያን ዮሴፍን ዮሴፍ ያዕቆብን ወልዶታል። ዳግመኛም አመቤታችን ከዜቱ ዮሴፍ ስትሆነ እናቱ ሙታበት በሕፃንነቱ አግኝታ ከጌታ ጋራ አንድ አድርጋ አሳድጋዋለችና አይሁድም አክኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለጸራቢ ወስማ ለእሙ ማርያም ወእኃ ዊሁኔ ያዕቆብ ወዮሳ ወሰምዖን ወይሁዳ ማቴ 13:55 ማለታቸው ቅሉ ስለዚህ ነው። ወከነ እግሩ ከመ እግረ ነጌ ይላል ከገድል ጽናት የተነሣ እግሩ እንደ ሙቀጫ ተድበልብሉ ነበር። በዚያውም ላይ ምሁረ አሪት ነበርና የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በራ እንዲሉ የአየሁድ ፀባያቸውን የሚያውቅ እሱ ነው እሱ ያስተምራቸው ብለው በሊያሩላሌም ኤጲስ ቆጶስነት ሹመውታል።

ከዚህ በኋላ ብዙ አሳምኖ ብዙ አጥምቆ የሚኖር ቢሆን አይሁድ ለምቀኝነት አያርፍምና በምን ነገር እንጣላው ብለው ተነሣ ፀረገ ስለምትለው ስለ ኢየሱስ ናዝራዊ አስተምረን አሉት። ከደርቡ ወጥቶ መንበር አዘርግቶ ከዚያ ላይ ሁኖ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክነት ሲያስተምራቸው ኋረ ይህ ደፋር የማርያምን ልጅ አምላክ ይላል ብለው ጎትተው አውርደው ቀጥቅጠው ገድለውታል።

➢ ሰማዕት የሆነው በ 62 ዓ.ም ነው

ሐምሌ 19 – በዓሉ ለቅዱስ ገብርኤል ሊቀ.መ

ገብርኤል ማለት እግዚእ ኃበር ማለት መሆኑን ሊቀ መላእክት መጋቤ ሐዲስ አብሳሬ ትስብእት ፍጡነ ረድኤት መሆኑን በክፍል 1



መጽሐፋችን ተምረናል። በዚህም ዕለት ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣን ከእሳት ማዳኑን እንማራለን።

ቅዱስ ቂርቆስ ሀገሩ ሮም አንጌቤን ነው አባቱ ቆዝሞስ ይባላል እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ በትውልዷ ከአዝማደ ነገሥት ነች። ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ በ20 ዓመት በአባ ባጋሞስ ምክንያት «አብያተ ጣዖታት ይትራንዋ ወአብያተ ክርስቲያናት ይትዐጸዋ ብሎ አወጀ /በ303 ዓ.ም/ በዚህ ጊዜ እኩሌቹ ተሰደዱ ቅድስት ኢየሉጣም ልጇ የ 3 ዓመት ሕፃን ነበርና ለርሱ ብላ ወደ ኢቆንዮን ሸሸች።

መስፍን ብሔሩ አለእስክንድሮስ ክርስቶስን ካጂ ልጣዖት ስገጂ አላት ዓይን እያለው ለማያይ ጆሮ እያለው ለማይሰማ በቃልህ አዘዘ በእጅህ ሠርተህ ለቆምከው ምስል አልሰግድም አለች። እይሆንም ካልሽማ በሰይፍ ትቀጪያለሽ ብሎ አስፈራራት። እስኪ ይህን ሕፃን ጠይቀው አለችው። አንተ ሕፃን ወርቅ እሰጥሀለሁ ለዚህ ጣዖት ስገድ አለው መንፈስ ቅዱስ አድሮባታልና አንስ ኢይሰግድ ለአማልክቲክ ርኩሳን ዘኢይክሉ አድጎኖ ርእሰሙ ራሳቸውን እንኪ ማዳን ለማይችሉ ርሱሳን ጣዖታትህ አልሰግድም አለው ተበሳጨ በብረት ጋን ውኃ አፍልታችሁ ከዚያ ውስጥ ጣሏቸው አለ ዝፍት ተይ ጨምረው እንድደው በብሪት ጋን ውኃ አፈሱ ድምጻ ለጽሕርት ከመነጉድጋደ ክረምት ይላል የውኃው ፍላት እንደ ክረምት ነጉድጋድ 42 ምዕራፍ ድረስ ይሰማ ነበር። ሊከቷቸው ሲወሰዷቸው ኢየሉጣ ልቧ በፍርሀት ታወከ እሱ ግን ፍርሃቷን አርቅላት እያለ ይጸልይላት እሷንም ጥብዒኬ እምየ እምዝ ዳግመ ኢይ ረክበነ ሞት ሁለተኛ ሞት አያገኝንምና እናቴ ሆይ በርቺ ጨክኚ በዚያውስ ላይ ዘአድጎኖሙ ለአናንያ ወአዛርያ ሚሳኤል ውእቱ ያድጎነነ አናንያ አዛርያ ሚሳኤልን ያጻነ እኛንስ ያድነን የለምን እያለ እያጽናናት ልብሷን እየጐተተ ከእሳቱ ቀረቡ ከዚህ በኋላ እሷም ጨክና በፍጹም ልብ ሆነው ተያይዘው ከእሳቱ ከውኃው ገብተዋል። በዚህ ጊዜም ከዐላውያን ነገሥታት ከዐላውያን መሳፍንት ገብተው የመሰከሩለት በስሙ መከራ የተቀበሉለት ጌታ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ በብትረ መስቀሉ እሳቱን አጥፍቶ የፈላውን ውኃ አቀዝቅዞ አውጥቷቸዋል። በወጡም ጊዜ ልብሳቸው ላይለለለ ሰውነታቸው ላይሸበሸብ ቢያዩ ከአሕዝብ ብዙዎቹ

አምነው አንገታቸውን ለሰለት ሥጋቸውን ለእሳት ሰጥተው በሰማዕትነት ዐርፈዋል።

ቂርቆስ ኢየሉጣ ቅዱሳን ሰማዕት
ከነፈረው ውኃ ጻኑ ከእሳት
በገብርኤል በትር ያላንጻች ኑጻት
ወቶቆች ነን ብቦች እንተን ቢከጹህ
ለሦስት ዓመት ሕፃን ምሥጢርን ገልፀህ
አምላክነትህን መስክረልህ።
እንዲህ ነው ልጅ ማለት ወደ ዓለም መድኀን

በርቺ እናቱ እያለ የሚመራ እናቱን
እየታገተቹ ገብተው ከዕቶን
ጎብኝተውት ወጡ የውኃውን ጋን
እምነት የሌለው ሰው ጌታውን የናቀ
መነግቱን እንጂ አንዲ ከወደቀ
ሃይማኖት ያለው ግን ተሸንፎ አያወድቅም
ጊንሙን ቢረግጥ እንኪ አንዳች አይጉዳውም

ማር 16:15 ቆላ 2:7

ሐምሌ 24 አባ ኖብ ጻድቅ

ኖብ ማለት ጽሩይ ወርቅ ማለት ነው ሀገራቸው ደቡብ ግብጽ ንሂሳ ነው። በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ዓላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ሲያፈርሱ የምእመናን ደማቸውን ሲያፈሱ በመንፈሳዊ ቅናት ተነሣስተው ለመመስከር ወደ ንሥኑዲ ሄዱ የጣዖትን ከንቱነት የእግዚአብሔርን አምላክነት ሲመሰክሩ መስፍኑ ብሔሩ ሉክዮስ ፈጣሪህን ክደህ ለጣዖት ስገድ አላቸው። ፈጣሪዬን አልክድም ለጣዖትም አልሰግድም አሉ። በሰይፍ እቀጣሀለሁ አላቸው ከዚህ ሁሉ አምላክ እንደሚያድነኝ አምናለሁ። አሉት ያገኛቸው መርከብ ሲሳፈር ነበርና በመርከቡ ምሰሶ ቁልቁል አስቅሉ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አስገረፋቸው።

ከዚህ በኋላ ብላቴኖቹ ምግቡን መጠጡን አቀረቡለት ። እመሸለሁ ቢል ደንጊያ ሆኖበታል። ብላቴኖቹም ዓይናቸው ታውሯል። እሳቸውን ግን የታዘዘ መልአክ ፈውሶ ከሰቅላት አውርዷቸዋል። ምድረ እትሪክ ሲደርሱ ወደ ጌታ ቢያመለክቱ ብላቴኖቹ ዓይኖቻቸው በርተውላቸዋል። በአምላካቸው አምነው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው በሰማዕትነት አርፈዋል። አባ ኖብን ግን ሥቃዩ ይጽናበት ብሎ በብረት አልጋ በብረት ችንካር ችንክሮ አሳት አስነደደባቸው መልአኩ መጥቶ ፈወሳቸው። የተቀበሉት መከራ ይህ ብቻ አይደለም። ዓይን ከማየት ጆሮ ከማስማት እንዳያቋርጥ እሳቸውም ስመ እግዚአብሔር ጠርተው አምላክነቱን መስክረው ከመሠቃየት ያረፉበት ጊዜ የለም። ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ በቃል ኪዳናቸው የተማጸኑውን ሁሉ አሳቸው ከሸቡበት መካነ ዕረፍት እንዲያገኛላቸው ተሰፋቸውን ነግሯቸው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው በሰማዕትነት ዐርፈዋል። በሺህ የሚቆጠሩ አማንያንም አሠራቸውን ተከትለው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው በሰማዕታት ዐርፈዋል።

➢ የነበሩት በ4 ኛው ም/ዓመት ድ/ል/ክ ሲሆን በሀገራችን ቡልጋ ውስጥ አቲሳ አካባቢ በስማቸው የታነጸ ቤተክርስቲያን አለ።

ሐምሌ 26 ዕረፍቱ ለዮሲፍ ጻድቅ /ከ 5440 ዓ.ዓ - 44 ዓ.ም/

ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ከቤተ ዳዊት ነው። አባቱ ያዕቆብ ይባላል። እግዚአብሔርን የሚፈራ ለሰው የሚራራ ደግ ሰው ነበር። ማቴዎስ ወዮሴፍ ፈጻሪሃ እስመ ጻድቅ ውእቱ ኢፈቀደ ይክሥታ ሲል መስክሮለታል። ማቴ 1:19 ድግር ጠርቦ ጥርብ አለዝቦ ሸጦ ይኖር ነበር። ጌታም አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለጸራቢ መባሉ ቅሉ ስለዚህ ነው። ማቴ 13:54 ያዕቆብ ዮሳ ስምዖን ይሁዳ የተባሉ አራት ወንዶችና ለሳት ሴቶች ልጆች ወልዷል። ሚስቱ ከሞተችበት በኋላ አይሁድ በእመቤታችን ላይ በጠላትነት ተነስተው ከቤተ መቅደስ ትውጣልን ባሉ ጊዜ ልማዘሥሉስ ጥፋ በሥሉስ እንዲሉ በሶስት ነገር ተመስክሮለት እመቤታችንን ወስዶ ከቤቱ አስቀምጧታል። ከዚህ በኋላ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በደስታዋም በኀዘናም ጊዜ አልተለያትም። ጌታን በወለደች ጊዜ ዳስ ሠርቶ ግርግም አዘጋጅቶ አገልግሏታል።

ልጇን ከሄሮድስ ሰይፍ ለማዳን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ረሀቡን ጽሙን ሐሩረ መዓልቱን ቁረ ሌሊቱን ታግሣ በረሀ ለበረሀ በተንከራተተችበትም ወቅት አልተለያትም።

«አልቦ እንበለ ሰሎሜ ዘያስተብርየኪ ለኪ፣ ወዮሴፍ አረጋዊ ዘይጸውር ስንቀኪ» እንዳለ ደራሲ።

ከሚጠቅም በኋላ ጌታን እንደ አባት ሆኖ አሳድጐታል። አይሁድ ጌታን ወልደ ዮሴፍ ማለታቸው ቅሉ ይህን ይዘው ነው። ያረፈው በ104 ዓመቱ ነው። መላእክቱን አስከትሉ ደቀመዛሙርቱን በደመና አምጥቶ ካለበት ሰብስቦ ክብርት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ አሳርጓታል። ሥጋውንም በእጁ ዳሰ እንዳይፈርስ እንዳይበሰብስ አድርጓታል።

ሰው ሁሉ ባወቀው ታማኝነትህ
ሊያዩህ ከርስቶስ ቸሩ ፈጣሪህ
ከደጋጎች ሁሉ አንተኑ መርጦህ
ድንግል ወላዲቱን እደራ ሰጠህ
አፈጋሪ ዮሴፍ አንተስ ብፁዕ ነህ
ጽድቅህ እንዲታወቅ ፍጹምነትህ
ጻድቅ ሰው ነው ብሎ መስክሮልህ
ማቴዎስ በወንጌል ተረድቶት ክብርህ
አባ ሕርያቆስም የመንፈስ ልጅህ

ጽድል እንደሆነ ንጽሕና ሀብትህ
ድንግል ደስ ቢላት እንተኮ ደስ ብሎህ
ሊከሱት ተከፍተህ በታዝን አዝነህ
ስትራብ ተርበህ ሲጠማት ጠምተህ
መከራዋን ሁሉ አንተም ተቀብለህ
እመቤትነቷን እምላክ ገልጠልህ።
ዮሴፍ ጻድቅ ሆኖ ክብርን የመረጠው
ጌታን ከእናቱ ጋር በማገልገሉ ነው
እኛም እናገልግል ድንግልን ቤሐት
ባሰኟል እንድንሆን ለእምላክ ጽድቅ።

ምሳ 22:9 ሲራ 10:23

ለ. ዕረፍቱ ለአቡነ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/
/ከ328 – 350 ዓ.ም መዋ ሢመት/

የትውልድ ሀገራቸው ሶርያ ነው። ቀዳሚ ስማቸው ፍሬምናጦስ ነው። የመጀመሪያው ጳጳስና በትምህርታቸው በትሩፋታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከዝቢረ ኃጢአት ወደ ዝረ ጽድቅ የመለሱ ሐዋርያዊ ናቸው። «ሰላማ ኖኅት ዘምሕረት ወተሣህሎ፣ አሥረቀ በኢትዮጵያ ለብርሃን ክርስቶስ ጳጳሱ፣እንዘ ላዕሌሃ ጽልመት ወቆባርህሉ» እንዲል አርኬ-

ሀገራቸው ሶርያ ከሆነማ ወዲህ ምን አመጣቸው? ትለኝ እንደሆነ በፈቃደ እግዚአብሔር መጥተዋል። መረጳዶስ የሚባል ነጋዴ ዘመድ ነበራቸው። እሳቸውንና ሲድራኮስን አስከትሉ ለንግድ ወደ ሀገራችን መጥቶ ሲመለስ ከመንገድ ወንበዴዎች ደብድበው ገደሉት ሕፃናቱን ማርከው ለመንግሥት ሰጧቸው። ንጉሡ አይዞህ ይባላል። የአብርሃ ወአጽብሃ አባት ነው። ስነ. ምግባራቸውን ጽንዐ. ኃይላቸውን አይቶ ሲድራኮስን ከቤተ.መንግሥት ፍሬምናጦስን ከቤተ መዛግብት አስገባቸው። ፍሬምናጦስ ከገዘዘ አከሱም ከእንበረም ብሉይ ሲማሩ አድገዋል። አንድ ቀን የሀገራቸውን ሥርዓት አጽንተው እምነት ብከሙ ግዝረት ብከሙ ጥምቀትሰ ወቀረበ ቁርባን አልብከሙ አምናቹሀል ተገዝራቹሀል ጥምቀትና ቁርባን ግን የላችሁም አሉት። ግዝረትንግ አባቶቻችን ሊዋውያን አምጥተውልናል እምነትንም የሕንደኬ በጅርንድ አስተምሮን አምነናል። ለዝንቱሰ ኢተፈነወ ለነ ሐዋርያ ለጥምቀት ሰቁርባን ግን ሐዋርያ አልተላከልንም አላቸው። ምነው እስክንድርያ ቅርብ አይደለችም ሄዳችሁ አታመጡም አሉት። ከቤተ. መንግሥት ተማክሮ አንተ ባወቅህ አምጣልን ብለው 500 ወቄት ወርቅ ሰጥተው ሰደዷቸው ቢሄዱ ሊቀ ጳጳሳቱ አባ አለ አስክንድርሰ ለጉባዔ ኒቅያ ሄዶ አገኙ። ተከትለው ሄደው ሠለስቱ ምዕት አርዮስን አውግዘው ሲለያዩ አግኝተው ነገሩት። ይህግ ደግ ነገር ነው ሳላማኸር አደርገዋለሁን ብሎ ሠለስቱ ምዕትን ሰብስቦ አንዲት ያለ ሐዋርያ ያመነች ሀገር አለች አላቸው። ያንተ ዕጸ ናትና አንተን መስላ ትደር አንተ ሹምሳት አሉት። እሱም ከጉባዔ ከተመለሰ በኋላ አልሰነበተም።ከሱ ቀጥሎ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ተሾመ። ባህላቸውን የለመደ ቋንቋቸውን ያወቀ ካንተ ሌላ ወዲት ይሾል ብሎ አምስት ዓመት ሐዲስ አስተምሮ አባ ሰላማ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ ብሎ ሾሞ ልኳቸዋል። ሰላማ ማለት ሰላማዊ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብአ ማለት ነው።

ከዚህ በኋላ ከእንበረም ጀምረው ቀሳውስትን ዲያቆናትን ሾመው ዙረው ተሢዙረው አስተምረዋል። መጻሕፍት ቅዱሳትንም ከሱርስት ከዘርዐ ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል። የሰባው ያንንም የፊደል አቀማመጥ የለወጡትና ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍና የማንበብን ዘዴ ያስገኙ እሳቸው ናቸው። በዚህ አኳኃን ሐዋርያዊ ተልዕኳቸውን በትጋት ሲፈጽሙ ኑረው በዚህ ዕለት በሰላም ዐርፈዋል።

ሐዋርያ መንፈሳዊ ደግ አባት ሰላማ
የተዋሕዶ ፋና የኢትዮጵያ ጉርማ
ሀገሬ ኢትዮጵያ መቼም አትረሳህ
በአምላክ ሰም ተጠምቃ ቆርባለች በእጅህ
አባ በአሉትህ በትሩፋትህ
የታመመ ደነው ቆሙ በፈትህ

ፍኖም መንፈሳዊ ፍቅር አገበርህ
ወጥተህ ተራራውን ቆላውን ወርደህ
ምቀኛ ጣዖትን ነቃቅለህ ጥለህ
በሰውና በአምላክ ዕርቅን አደረገህ
ሰለዚህም በአውነት ሰላማ ተባልህ
ሰውን ከአምላኩ የሚያስታርቅ መክር

በሕይወት ይኖራል በሰማያት ክብር

ማቴ 5:9 2ቆር 5:20

ምዕራፍ 6

ነሐሴ 1 አቦሊ ስማዕት

ሀገሩ አንጾኪያ ነው። አቤቱ ዮስጦስ እናቱ ታውክልያ ይባላሉ። ዮስጦስ የንጉሥ ኑማርያኖስ ልጅ ነው። ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ እያለ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥል መጻሕፍትን ሲቁነጠል ሰይፋን መዞ ሊጣላው ሲሄድ ፋሲለደስ ስለ ሃይማኖትማ በሰይፍ ልንሞት እንጂ ልንገድል አይገባም ተው ብሎ መልሶታል። ዲዮቅልጥያኖስ ሰይፋን ቢመዝበት ፈርቶ ወደ ማጀት ሸሽቶ ነበር። ከቁጣው ሲመለስ መጥቶ ሃይማኖትህን ከደህ ለአጵሎን ሰግደህ እኔን መስለህ እኔን አክለህ አትኖርምን አለው። አይሆንም አለው። አጎቱን አግብቼ ከመንግሥቱ ገብቼ እንዴት ልጣላው ብሎ ሚስቱ ታውክልያንና ልጁ አቦሊን ጨምሮ ወደ እስክንድርያ ላካቸው። መስፍኑ ሄርሜኔዎስ ይባላል። የንጉሥ ልጅ ንጉሥ እንዲት ብዬ እናግረዋለሁ ብሎ ከፋም በጉም አልተናገረውም። ለያያቸው የሚል ትእዛዝ ደረሰው። አንድ አንድ ብላቴና እየሰጠ ዮስጦስን ወደ አንዲናው ታውክልያን ወደ ፃ ሰደዳቸው መከራውን ተቀብለው በስማዕትነት ዐርፈዋል። አቦሊንም ወደ ብስጣ ሰዱታል። መስፍኑ ለጣያቱ ስገድ አለው። አይሆንም አለ በደንጊያ አስወግሮ በእሳት አስተኩሶ ገደለው። የታዘዘ መልአክ መጥቶ አንስቶታል። ብዙዎች በእውነት መግደል ማዳን የሚችል የክርስቲያን አምላክ ነው ብለው አምነው እንገታቸውን ለሰይፍ ሰውነታቸውን ለእሳት እየሰጡ በሰማዕትነት አርፈዋል። እሱን ግን መከራው ይጽናበት ብሎ ቆዳውን አስገፍፎ በጨው ሆምጣጤ የተዘፈዘፈ ጨርቅ ጠቅልሎ ቆዳውን አሸክሞ ዝበያ ለገቢያ አዙሮታል። መከራው ቢፀናበት ወደ ጌታ አመለከተ። ቅዱስ ሚካኤል ተልኮ መጥቶ ፈውሶታል። ከዚህ በኋላ እንደ ቶማስ ዘሕንደኬ በሰልጥው ሕሙማንን እየፈወሰ ሙታንን እያስነሳ አሕዛብን በወንጌል እንዲያምኑ ክርስትና እንዲቀበሉ ከገዢ ጽድቅ እንዲመለሱ አድርጓል።

አበስኪሮስ የሚባል ባለጸጋ ሕንፃ ያሰራ ነበር። ከሕንፃው ጽኑዕ ደንጊያ ወድቆ ሁለቱ ልጆቹንና 12 ብላቴኖቹን ራሳቸውን ዝምሶ አጥንታቸውን ከስክሶ ገደላቸው። ልብሱን ቀዶ ትቢያ ነስንሶ ዋይ ይል ጀመር። እኒህን ሙታን ባስነሳልህ በእምላኬ እታመንምን አለው። አምናለሁ አለ። በስሙ ለእግዚአየ እየሱስ ክርስቶስ ወልደ

እግዚአብሔር ሕያው ተንሥኡ ሕያዋ ኒክሙ እያለ ስልቻውን ቢያስነሳቸው ተነስተውለታል። አበስኪሮስም ከነቤተሰቦቹ በመንገሌ አምኗል።

መስፍኑ ዝዚህ ቢያፍር እንጉቡን በሰይፍ አስመትቶት በሰማዕትነት ወርቷል: ከዚህም አስተድሞ ጌታ በተነሱህ ያመነውን በኪዳንህ የተማለኩን ሁሉ ከጻህበት ውሳጤ መንጦላዕት አዝዋለሁ ብሎ ተሰፋውን ነግሮታል።

➢ ሰማዕትነት የተቀበለው በ4ኛው ም.ዓ.ሙት ድ/ልክ መጀመሪያ ላይ ነው።

ነሐሴ 2 ቅድስት አትናስያ

ሀገሯ ሙኑፍ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ለሰው የምትራራ ደግ ሴት ነበረች። ከደግነቷም የተነሣ ቤቷን ከፍት አድርጋ የወጣ የወረደውን ያለፈ ያገደመውን እንግድነት ስትቀበል ትኖር ነበር። ያላትን ሰጥታ ስትጨርስ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ፍቅረ ዝሙት አሳደረባት እሺ በጀ ቢፃኝ ፍጥፋትን ሁሉ ግባ በይው የምትል ሆነች። ከመንኮሳት አንዱ ዮሐንስ ሐጺር አገኖ ተከዞ ሄደ። አልጋዋን አንጽፋ ከዚያ ላይ ሁና ና ከጉኔ ተቀመጥ አለችው። ከፈጅ በወንበር ተቀምጠ እያያት ያለቅስ ጀመር። የመጣህበትን ትተህ ያልመጣህበትን ምን ያስለቅስህል አለችው። ከዝሪ ጽድት ወደ ዝሪ ኃጢአት ተመለሰች ብለውኝ አዝኜ ተከዥ ብመጣ ሲደጣናት በራስሽ ላይ ሆነው ሲሳለቁብሽ እያየሁ ይህ አያሳዝንምን አላት። እንኪያስ ምን ይሻለኛል አለችው ድኅነተ.ነፍስ ከፈለግሽ ተከተይኝ ብሏት ወጣ። ሀብቴን ንብረቴን ትተቴን ማቴን ሳትል ተከተለችው እሱ ፊት ይሄዳል እሷ ኋላ ትሮጣለች። አባቴ ቆየኝ ትለዋለች ድረገብኝ ይላታል። ሸኩ ጋራጣው ሲወጋት ባለ ጉብር ቀሚሷን እየቀደደች እግሯን አያሰረች ተከተለች።

ከበዓቱ ሲደርሱ አሷን ከምንዳደ እባተ ትተ ቢጸልይ አድሯል። የብርሃን መሰላል ተተክሎ መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ አይቷል ሲነጋ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ያመጣህት ቤት አርፋለችና አናብስት መቃብሯን ይቆፍሩልህል ገንዘህ ቅበራት አለው። ያስ ይሁን ይህን ያህል ስትወጡ ስትወርዱ ያደራችሁት ለምንድን ነው አለው። ነፍሷን ስናሰርግ ነው አለው። ተቀበላችን አለው እሷንግ ትጥቴን ማቴን ሳትል ከቤቷ ወጥታ በተከተለችህ ጊዜ ነው የግራት አለው። ቢሄድ ዐረፋ አገኛት። አናብስት መቃብሯን ቆፍረውለት ቀብሯታል።

የአበራችው በ ኛው ክ.ዘ ድ/ል/ክ ነው።

ቅድስት አትናስያ አምላክ ያደላት
ወደ ሕይወት ገሸች አምልማ ክሞት
ከዓለም ተድላ ይልቅ ያንድአፍታ ደስታ
ከአምላክ ጋር መኖር መሻሉን ተረድታ
ወደርሱ ዘንድ ሄደች ቤቷን ክፍቱን ትታ
ሮጣ ያልጠገበች ኛ ቀንጆ ሳለች
ሁሉን ነገር ትታ አምላኳን ፈለገች
ዮሐንስ መምህሯን እየተከተለች
ወደገዳም ስትሄድ አምራ እያነባች
ምድሩን አራሰችው ደሟን እያዘራች።
ከፈጣሪዋ ዘንድ አግኝታ ምሕረት
የቅዱሳንን ሞት ደከማ ስትሞት
በጥዑም ዝማሬ በቃል ማኅሌት
በክብር አሳረጉ ነፍሷን መላእክት
የጉየአ መመለስ ወደ አምላኩ ፊት
ደስታቸው ኑሮና ሰነርሱ በእውነት

ማቴ 18:13 ሉቃ 15:7

ነሐሴ 6 ማርያም መግደላዊት

ማርያም ማለት የዋሂት ርኅርኅት ማለት ነው። ቁጥሯ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ነው። መልከ መልካም ተወዳጅ እህት ነበረቻት። ወዲህ መውለድ ወዲህ መወደድ እያለች ትቀናባታለች። በዚህ ምክንያት 7 አጋንንት አድረውባት ነበር። መንፈሰ ትዕቢት፣ መንፈሰ ጽርፈት /ስድብ/፣ መንፈሰ ቅንዓት፣ መንፈሰ ትውዝፍት /የምንዝር ጌጥ ማድረግ/ መንፈሰ ዝሙት፣ መንፈሰ ሐሜት፣ መንፈሰ ሐሰት ናቸው። ጌታን እምና በተከተለችው ጊዜ ይህን ሁሉ አጥፍቶላታል። ጌታም ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ መጀመሪያ የታየው ለእሷ ነው። ወተንሢእ በጽባሕ በእሁድ ሰንበት አስተርእያ ቅድመ ለማርያም መግደላዊት እንተ እምኔሃ አውጽአ ሰብአተ አጋንንተ እንዲል ማር 6:9 ከዕርገቱም በኋላ ሐዋርያትን በተልዕኮ ስታገለግላቸው ኑሯ በዚህ ዕለት ዐርፋለች።

ነሐሴ 7 ጽንስታ ለእግዝትነ

እያቶጅ ቴክታ በጥሪያ ይባላሉ። ብዙ የወንድ ባሪያ የሴት ባሪያ የቀንድ ከብት፣ የጋማ ከብት የነበራቸው ባለጸጐች ነበሩ። ከወርቁ በዛት የተነሣ እንደ ቀለበት እንደ አምባር እያሰሩ ከበሬው ከላሙ ቀንድ እያደረጉ ይህን ያህል የወርቅ ቀንድ ይህን ያህል የብር ቀንድ አለን ይሉ ነበር። አንድ ቀን ቴክታ ከዚተ መዛግብት ገብቶ ወርቁ ብሩ ተዝረክርኮ አይቶ በጥሪቃ ሀብታችን ብዙ ንብረታችን ብዙ ነገር ግን የወለድነው ያሳደግነው ልጅ የለንም ለማን ይሆናል አሳት። እግዚአብሔር እንጂ ከኔ ባይሰጥህ ከሌላ ይሰጥህ ይሆናል አግብተህ አትወልድምን አለቸው። ሕያው እግዚአብሔርን አሳደረገውም አሳት። በዚህ ጊዜ አዘኑ ሴሊት በሕልሟ እንበላ ከበረታቸው ስትወጣ እንበላይቱ እንበላ እየመለደች እስከ ስድስት ስትደርስ ስድስተኛይቱ ጨረቃን ጨረቃ ፀሐይን ስትወልድ አይታ እንዲህ ያለ ሕልም አለምሁ አለቸው። ከመተርጕመ ሕልም ሄደው ቢጠይቁ ዳግ ልጅ ትወልዳላችሁ ጨረቃይቱ ከፋጡራን በላይ የምትሆን ልጅ ትወልዳላችሁ የፀሐይ ነገር ግን አልተገለጸልኝም እንደ ዝኪይ እንደ ንጉሥ ያለ ይሆናል አሳቸው። ጊዜ ይተርጕመው ብለውት ሄዱ ከዚህ በኋላ ጰንጠ ወለደች ስሟን ረከብኩ ስዕለትየ ስትል ሄኤሜን አለቻት። ሄኤሜን ዴርዴን፣ ዴርዴ ቶናን፣ ቶና ሲካርን፣ ሲካር ሄርሜላን፣ ሄርሜላ ሐናን ወለደች። ሐናም ዕሡቱ ማኅፀን ሁና ልጅ አጥታ ስታዝን ትኖር ነበር። ዘማዊት ጐረቤት አለቻት። አንድ ቀን ሐና ልብሴ ቆሽሿል እንጂ እመለስ ነበር አለች። ልብስማ የኔ ልብስ ሣጥን መልቶ ተርፎ የለምን እንዱን ለብስሽ እትሄጅምን አለቻት። ያንቺ ልብስ በአስብ ዝሙት የተሰበሰበ ነው ንፁሕ ባሕርይ ጌታ ንፁሕ ነገር ይወዳልና ይህን ለብሼ ብለምነው እይሰማኝም ብዬ ነዋ አለቻት። ሐና እኔስ ጌታ ስለምን ልጅ ሦስት እያልኩ ሳዝንልሽ እኖር ነበር። ለካስ በዚህ ክፉትሽ ነው እንደ ድንጊያ አጠጥሮ እንደ ግንድ ገትሮ ያስቀረሽ አለቻት። በዚህ አዝናለች።

ሊቀ ካህናቱ ሮቤል ይባላል። እናንተ እንጂ ወኢይተዌከፍ መባየሙ ለመከናት ይላል። ብዙኑ ወተባዝኑ ያለውን ያስተረባችሁ ርኅማን ብትሆኑ አይደለምን መባችሁን አልተበልም አላቸው። ሁለተኛም ወላድያን የሚመዝኑት ተረፈ መስዋዕት ነበረ። ያን ከልክሏቸው እያዘኑ ሲመለሱ ከዛፍ ጥላ ሥር አረፉ። ሐና አእዋፍ ከልጆቻቸው ጋር ሲጫወቱ አይታ አእዋፍን ከባሕርያቸው እንዲራቡ ዕጽዋትን እንዲያፈሩ ስታደርግ ሐና ባሪያህን በምን ነገር ልጅ ነሳህት በውኑ ተፈጥሮዬ ከደንጊያ ነውን ብላ አዘነች። ከዚት ሲደርሱ ወንድ ልጅ ብንወልድ እርፍ አርቆ ተከል አዕድቆ ይርዳን አንልም። ለቤተ እግዚአብሔር ምንጻፍ አንጣፊ መጋረጃ ጋራጅ ይሆናል እንጂ ሴትም ብንወልድ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ ትርዳን አንልም መሶብ ወርቅ በፍታ መጋረጃ ፈትላ ሴት እግዚአብሔር ታገለግል እንጂ ብለው ብፅዓት ገብተዋል።

ሐምሌ 30 እሷ ለርሱ ግምጃ ሲያስታጥቁት መጂያው አፍርታ ፍጥረት ፍሬዋን ሲመዝኩ እሱ ለእሷ ኑሮ ርኅብ ሰባቱን ሰግያት ሰንጥቃ መጥታ በቀኝ ጀርዋ ገብታ በግዕዘንዋ ስታድር ሕልም አለሙ። ሄደው ለመፈከረ ሕልም ነገሩት። የከበረች ልጅ ትወልዳላችሁ አላቸው። የግይመስላቸው ቢሆን ጊዜ ይፍታው እንጂ አንተስ አልፈታኸውም ብለውት ተመለሱ። ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ በሕሊና አምላክ ታስባ ትኖር የነበረች እመቤታችን የተነገረላት ትንቢት ሊፈጸም የአባት የእናቷ ራዕይ ሊተረጐም ጌታ የፈቀደበት ጊዜ ሲደርስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ኢያቄምን ሚስትህ ሐና ትጸንሳለች ደግ ልጅም ትወልዳለች አለው። ዝሙት ይሆንብናል ብለው ምንጻፍ ለይተው ይኖሩ ነበር። ፈቃዱስ ከሆነ ብለው በሉንድ ምንጻፍ አድረዋል። እመቤታችን በዚህ ሌሊት ተፀንሳለች።

ታሪኩ የተፈጸመው በ16 ዓ.ዓ ነው።

በገብርኤል ብሥራት ከአያቱም ከሐና
ድንግል ተጸነሰች የነሐም ሁሉ ጨኗ
ሁሉም ደስንቀሻል መሪሚ ስደትን
የሙ ሁሉ እናት ሆና ቦግነን።
ጻሩ ግን ለሰማዕት ሆነች እርአያቸው

የጋ እንዲያገኙበት ከሻር አምላካቸው።
መድኃኒትነቷ እንዲታወቅ ነልቶ
ከብሯን መስክረ የሞተው ተነሥቶ
ሕመማንም ዋሉ እያመነኩ
የሐና ማኅፀኗን ላለው እየላኩ

ነገረ ማር

ነሐሴ 9 አልዓዛር ካህን

ከሞርኮ መልኩ በ169 ዓ.ዓ ገደማ/ ከሀገት ከምስፍና ደርዐ ይዞ ይኖር ነበረ። ስምዖን አልፍሞስ መባልስ የሚባሉ ንፁሓን ካህናት ነበሩ። ሹመት

በተርታ ሥጋ በገበታ እንዲሉ ፈንታችንን እንሾም ስጠን አሉት። ለሕዝቡ አስታውቃችሁ ተሸሙአላቸው። ሕዝቡን ሰብስበው ፈንታችንን እንሾም ሹመቱን ስጡን አሏቸው። እሱ ከእግዚአብሔር አማኝቶ ተሹሞታል። እናንተም ከእግዚአብሔር አግኝታችሁ ተሾሙ አሏቸው። ይህማ ለርሱ ማድላታቸው ነው ብለው ጽርዕ ወርደው ንጉሡ እንጥያኮስን የዳዊት የሰሎሞን መንግሥት የሚዳኙት አጥታ ምናምንቴ ካህን ይናኝበታል ሄደህ እጅ አታደርጋትምን በዚያውስ ላይ እንጂ የዛሬን አያድርገውና አባትህ እስከንድር በእጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጉ ይገዛት ነበረ አሉት። አስራኤል ሰምቼ ጽኑዓን አምባቸው ጽኑ ፈጣሪያቸውም ይረዳቸዋል ሲሉ ሰምቼ እንጂ ሳላስበው የቀረሁ ይመስላችኋልን አላቸው። ይህማ ቀላል ነገር ነው አመንሁ ብለህ አዋጅ እያስነገረህ እርያ ከኋላህ ላም በግ ከፊትህ አድርገህ ና ብለው መከረውት ተመለሱ። ከዮት መሰሻችሁ አሏቸው እናንተ ከሁለት ሹመት አንዱን ስጡን ብንላችሁ አይሆንም አላችሁ። እኛ ግን ጽርዕ ወርደን እንጥያኮስን ያህል ጉናና ንጉሥ ሃይማኖት ከምግባር አስተምረን መጣን አሏቸው።

እንጥያኮስም እርያውን ከኋላ ላሙን ቦጉን ከፊት አድርጉ ከዋለበት ካደረበት ሁሉ አዋጅ እያስነገረ መጥቶ አምባ ከፈቱልኝ መሥዋዕታችሁን ልውዋ በዓላችሁን በዓል ላድርግ አላቸው። አሪት ኢይባእ ምእባዊ ወአሞናዊ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ብላለች ብለው አይሆንም አሉት። ነገሩን ለማስወደድ አይሆንም ካላችሁማ ብሉ ፊቱን መለሰ። ሰስቱ ካህናት አያችሁ ዝና ለዝና ርስት ይጠበናል ብለው በእግዚአብሔር ያመነውን ሲከለክሉት እያሉ ይለፍፉ ጀመር። እውነት መስሏቸው ደጃ እንጂ አሉ። ጥቂት ራብሀን ሁህ ገብተህ ሂድ ሠውተህ አሉት። ፊታውራሪዬን ቢትወደዴን በጅሮንዴን እያለ ሠራዊቱን ሁሉ ይዞ ገባ።

የሠራዊቱን መብዛት የሕዝቡን ማነስ አይቶ አልዓዛርን አስጠርቶ አንተ መንጅካ ለእኔና ላንተ በግ ሠዋ በግራ እጅህ የእርያ ሥጋ በቀኝ እጅህ ቢላዋ ይዘህ የበላህ መስለህ ሕዝቡን አሳምንልኝ አለው ጌታዬ የበጉ አብነት አደረገኝ እንጂ የክፋ አብነት አድርጉኖልን አይሆንም አለው። ይሠለሳል ብሎ ለክህነት የደረሱ 7 ልጆቹን ከፊቱ አሰልፎ በብይፍ መታቸው: የማይመለስ ሆነ ሚስቱ መክብዩ ትባላለች በጡትና በጡታ መካከል በብረት አለቅዞ ሰቀላት: አሁንም አልተመለሰም በቁመቱ ልክ ሻሸ አስጠ ምጥሞ ሰም አስነክሮ ብረት ምጣዱን አግሎ በራሱ ላይ ደፋበት ተንጨርጭሮ ሞቷል።

የእኒያስ ፍጻሜያቸው እንደም ነው ቢሉ ንዋያቱን ዘርፎ ሕዝቡን ማርኮ ከተመለሰ በኋላ ለወገኖቻችሁ ያልሆናችሁ ለኔ ምን ልትሆኑኝ ነው ብሎ አንዱን በብይፍ አስመት ቶታል። አንዱን በርጥብ ቆዳ አስጠቅልሎ ገደል ጥሎታል። አንዱን ግን ከምን እንዳደረሰው አልታወተም። እሱም

እልተጠቀመም። ቡኒ ወለተ ዱራ ላግባሽ ስላላት ተናዳ የኑቀዘ እንጪት በረበረበችበት ጉድጋድ ውስጥ ወድቆ ከዚያም ሰይጣ ን ጢቅ ብሎበት ሽቶ ተልቶ ሞቷል።

መኳና ሥቃይ የማይለውጡት
ያ ደን አልአዞር ካህን ነው በእውነት
ስንጥያኮስ ቢለው አንተ ሙት ካህን
ሕዝቡ እንዲቀበሉ ፃጉን አምላኬን
የኔን መሥዋዕት ሙዋ ትተህ ያንተውን፣
እንዲህ ቢል መለሰ ሳይርበተበት
አምላኬ የቀባኝ የሰጠኝ ክህነት
እንድሆን ነው እንጂ በጎ አብነት
አይደለም እንድሞሽ ሕዝቡን እንዳሰት
ከሙሞም አሁን መሥዋዕት ለጣዖት
ና ትሣኘ በለይፍህ ይሻለኛል ሞት
እንጥያኮስ መስሉት ፈርቶ የሚከድ
ሚስቱን አሰቀላት በኩላብ ከግንድ
ሰባት ልጆቹን አንድም ሳያተርፍ
ከፊቱ አቁሞ ፈጃቸው በብይፍ
ይህ ሁሉ ግን እርሱን አላሸረው
ይልቅስ ለአምኑቱ ጽናትን ሠጠው
እንጥያኮስ አይቶ በእምኑቱ መጽናቱን
ሲተማሙ ወሰነ አብዝቶ ሥቃዩን
በፈርቅ ጠቅሉ በሰም ውጠም ነክር
የጋለውን ምጣድ በራሱ አኑሮ
እንደትቢ በእሳት ሞተ ተንጨርጭር
ጻሩ ግን አልቀረም ደሙ እንዳፈሰሰ
አምላኩ ሰሰርቡ ጠላቱን ወቀሰ
ከፋው አንጥያኮስ ስላልተመለሰ
ሽቶ ተልቶ ሞተ በቁሙ በሰብሰ

ዘሌ 19:18 ዘጻ 32:35 ሮሜ 12:19

ነሐሴ 13 ደብረ ታቦር

ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት አንዱ ነው። ምን አድርጉበታል ቢሉ ብርሃነ መለኮቱን ለሐዋርያት በደብረ ታቦር ገልጸበታል። ደብር ተራራ፣ ታቦር የተራራ ስም ነው ጌታ በመዋዕለ ስብከቱ ብዙውን ጊዜ የሚያስተምረው ተአምራት የሚያደርገው በተራራ ላይ ነበር። በዚህም ዕለት ዘጠኙን ከእግሩ ደብር ትቶ ሰብቱ ኤጥሮስን ዮሐንስንና ያዕቆብን አስከትሉ ከርእሰ ደብር ወጣ። ወተመለጠ ራዕዩ በቅድሚሆሙ ወአብርሀ ገጹ ከመ ፀሐይ ወአልባሊሁኒ ኮነ ጸዓዳ ከመ. በረድ ይላል አርአያው ተለውጦ ፊቱ እንደ ፀሐይ አብርቶ ልብሱ እንደ በረድ ነጽቶ ሙሴና ኤልያስ በቀኝ በግራው ሆነው ታዩአቸው። ሙሴን ኤልያስን መምረጡ ስለምንድርነው ቢሉ ሙሴ 570 ጊዜ ቃል ለቃል ተነጋግሮ ባይህ እወዳለሁ አለው። አልቦ ዘይራኢ ገጽየ ወየሐዩ አሐተ ሰዓተ እምዘሕይወቁ በዲበ ምድር ፊቴን አይቶ እንድ ሰዓት እንኳ መቆም መቆየት የሚቻለው የለም አለው። ይህ ካልሆነማ ባለሟል መባሉ ምኑ ላይ ነው።

ቢለው ድኅረሰ ትሬኢ ገጽየ መሥዋዕት ሁኜ በምቀርብበት ጊዜ እታይሀለሁ ብሉት ነበርና /ዘጸ 33:18+23/ ነው። ያን ለመፈጸም ኤልያስም እንዲሁ ተስፋ ነበረውና አንድም ጌታ ዕውር ቢያበራ ሙት ቢያነሳ ሙሴ ሹው ኤልያስ ነው ብለውት ነበርና የኛን ጌታ ግን ሙሴ ኤልያስ ይልሀል የሙሴ የኤልያስ ጌታ ደብሉህ እንጂ ብለው እንዲመለከሩ አምጥቷቸዋል። ፍጻሜውው ግን ደብረ ታቦር

የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት። ሕጋዎያንም ደናግልም እንዲመርሷት ስማለየት ከሕጋውያን ሙሴን ከደናግል ኢሳያስን አመጣ። ጓላ ግን ስምዖት ተመንተው ብርሃነ መለኮትን ቢገልጽላቸው ከፈቱ ሙቆም ተስናአቸው ሙሴ ትሄደኪ መታበርያ ብሏል። ኢሳያስም ወደ መረዛው ተመልሰዋል።

ጴጥሮስ እመብ ትፈትድ ንንበር ዝ ወንጠር መለስተ ግንደረ ኢሐደ ስክ ኢሐደ ለሙሴ መኢሐደ ለኢሳያስ ብትመድስ እንዴን ላንተ እንዴን ለሙሴ እንዴን ለኢሳያስ ለስት ነጀ መርተን በዚህ እንኑር አሥ ። መጽአ ደመና ብሩህ መጸለሙ ይላል ይህን ሲናገር ብሩህ ደመና መጥቶ ጋ ነሳቸው። ወሊያውም «ዝንቱ ወልዳ ወልደየ ዘእረቅር ወሱቱ ስሙዎ ፀድ ደስ . ረሰኝ ልጀ ደህ ነው እሱን ስሙት» የሚል ድምጽ ከመጸላይ ተሰምቷል። እነ ጴጥሮስ ደንግጠው ወደቁ ተንሥኡ ወኢትፍርሁ ብሉ እንስቷቸዋል ከርእለ ደብር ቢመርዱም ያዩትን የሰሙትን እስከ ትንሣኤው ስማንም እንዳይናገሩ አዟቸዋል። ማቴ 17:3-9

ደመኾን በእገሪ ደብር ትቶ ለስቱን አስከትሉ መውጣቱ ስለምንድር ነው ቢሉ ከመጠ ብርሃነ መለኮቱን ሊያይ የማይገባው ይሁዳ ነበርና ትቶትም ቢሄድ ስኖ ዓል ነበርና እንድም ጴጥሮስ እምታለሁ እንጠፋ ብሎ ከንቱ ይራት ብሉት ነበርና እሱን ለመት የሚልውን እንዲሰማ አምጥቶታል: ዮሐንስና ያዕቆብንም በመንገሥቱ በመጣ ጊዜ ወቶን በገሪ መተመጥን ጀተው ነበርና ነው። ያስ ቢሆን ከተራሮች ሁሉ ታቦርን ስለምን መረጠ ብሉ ጻዲት «ታቦር መእርጦንሉም በስመ ዚእክ ይትፈሥሑ» መዝ 87:12 ብሉ ነበርና ያን ለመጀመር ነው።

እንሂ ደብረ ታቦር ምንኛ ታደለ
ጌታ መሰኮብን የመሰዳሬ
ያው ያሳው ሁሉን ስመሰከረ
በብርሃን ተመሳተል ይመነትን
ስመንግሥተ ሰማይ ምሳሌ ሆነ
ዝም እንዲያመጋቡት በእምሳክቱ
እዝ ይቃር ታየ ጌትነቱ
እብ መዘረስት ወደመና እሙ

የምጽው ልጅ ይህ ነው ሰሙት ብሉ
መሰና ኢሳያስ ካሰብት መተተው
ቀመው መሰክሩ ስተን በገሪው
ከፋና የሐንስ ያዕቆብ ሀሳችሁ
ጌታ ጌትነቱን ገልጾ ያሳያችሁ
የክብሩ ናኖው ያዩ ገደናቸው
እኛም በእዛችን ገሐብን እንመን
እንደ ሐዋርያት እንድናይ ክብሩን።

ምዝ 23:4 ማቴ 5:8

ነሐሴ 16 ፍልሰተ ሥጋሃ ለእግዚእትነ

እመቤታችን ጥር ሃያ አንድ እሁድ ተነ ግረጅን ወሰሩል ፤ መጽሐፏን ተምረናል። ሐዋርያት ሊተብጅት ዓዝር አድርገው ወደ ጌቱ ሲሚኒ ይሠዋት ዚሄዱ አደሁድ ስምተኝነት አያርፋምና ተድሞ ልጇን ተነግ ወረገ እያሉ ዚያውኩን ይኖራል። እሁን ደግም እሳን ተነሳች ወረገች እያሉ ሊያውኩን አደደለም ገው ናውሚ ሥጋ ስግርያም ሥጋን እናቃተል ብሎ ዜጠላትነት ተነሳ። ከሁሉ እንዱ ታውሩንስ ተራምዶ አዘዙን ወሰጠው የታዘዘ መልአክ ሁለት እጇን ወደይፍ ተሣው። ከእግሯ ተንጠልተሱ ተረ። ወድያው ማሬና ብሉ ዚማሬናት ራሳን ዘገፀል አድርጋ ጴጥሮስን እንደገረው አድርገት አለችው። ዚመልው ድኖ ተነስቷል። ከዚህ በኋላ የሐንስን ወሌምር ከመጨለማው ነጥቆ ኸት በዚህ አይወት ሥር አኑሯታል።የሐንስን እንደምን ሞኝ አሉት። ኸት በዚህ

አይወት ሥር አኑሯታል አሳቸው። የሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ብለው ከኑሐሴ ማባቻ ጀምረው ሱባዔ ገቡ። ሁለት ሱባዔ ሲጨርሱ 14 አምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረዋታል፣ ሞክሞ ተነሥታለች ። ተግስ አልክረምና ደመና ጠቅሶ ከሀገረ ስብኩቱ ሲመጣ ስታርግ አማቸት። ወፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ ይላል ተድሞ የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ እሁን ደግም ያንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁን ብሎ ተናደደ እኒያ ትንሣኤዬን ዕርገቴን አላዩም እንተ ግን እይተሀል አሁንም ሄደህ ተነሣች ዕረገች በላቸው ብላ ሰበደን ሰጠቸው። ሄደ የእመቤታችን ነገር እንደምን ሆነ? አላቸው። አግኝተን ተበርናት አሉት። ሞት በጥር በኔሐሴ መታበር ለስሚም እያምር ተውይህ ነገር አይመስለኝም አላቸው። ጴጥሮስ አንተን እንጂ መጠርጠር ልግድህ ነው ተጠራጥርህ ሰውን ስታጠራጥር ትኖራለህ አለው። ጴጥሮስ ተቆጥቶ ፊት ፊት እየርጠ እነሱ እየተከተሉ ጌቲ ሰግኔ ከመቃብሯ ደረሱ። ቢከፍተው አጣት ደንግጸ ቆመ አታምኑንም ብሎ እንጂ አመቤታችንስ ተነሣች ዐረገች አላቸው። ምን ይዘህል አሉት። ዚዘ ሰበን አልንሣችሁምን አላቸው። ትንሣኤ ዕርገቷን አምነው ለበኑን ለበረከት ተካፋለውታል።

በማመቤ ቶማስ አይቶ እኛ ሳናይ እንቀራለንን ብለው ሱባኤ ገቡ። በአሥራ ሰድስተኛው ቀን ጌታ ከሰማያት ወርዶ እመቤታችንን መንበር ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን አስጠ ፋኖስን ሠራዊ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ አቀርቧቸዋል።

የእመቤታችን ያረገችው በ 49 ዓ.ም ነው።

ደብርግል ይደንቃል የድንግል ዕረፍት
የአምላክ እናት ሆና ሞትን ስትዋት
ስድሳ አረት ዓመት ዚዘሀች ንስም ስትኖር
ደስታ አልነበራትም ከመከራ በቀር
ኖ ስትመሚ እንሚ ከስናቷ ማነሠን
ንስም ያዕያታት ነዘረ ስጸትን
በመንፈስ ቅዱስ ጥበር ሰጇንም ስትወልድ
ታሳድጓት ነበር በዘይቂ በትመድ
ፕቂት ዘመናትን ከዕያችም ጓላ
ደግም አዘዘራትት ሰጇን ዘእንጨት ስትላ
ያዋችው መክራ ድንግል በዚያች ዕለት
ሬጽሞ አያልችም ዚመሬ እንኪ ጓመት
ምንም ብትጠናና አይታ ትንሣኤውን
ታዝንነበር ሁሉ ስለታየችን መጻን
አይደንችም ወይ ታዲያ የአምላክ ሥራው

እጅግ የከበረች ንጽሕት ማደሪያው
እንደሰው ሳትኖር ስትሞት አንደሰው።
ስዕተድላ ስደስታ ሳትኖር ስማለት ነው:/
ፕር ሃያ አንድ ቀን ስዘም ዕለት
ተቀምጣ ሳለች ስሐንስ ዜቴ
ጌታ ስክብር መጥቶ ስእምታ መጣት።
ከንለም ሊያሳርፋት መምጣቱን ስትሰማ
አለችው እንደምን ደሀዋሰ ይሆማ
ወሊያው በተመከሰ ንልጠ አብያት
ጽጽን ስሊአል ያሉትን ነፍሳት።
ነፍሳትን ስሊአል ፈሙታዊ አይታ
እኔ ልሙት አለች ስለነርሱ ፈንታ።
ጌታም ዚያረሳት ቃል ኪዳኑን ጎበቶ
ነፍሷን አሳረገ ከሥጋ ለይቶ።

ነፍሳት ገነት ገቡ ከሞት ጉድጋድ ወጥተው
የድንግል ዕረፍቷ መድኃኒት ሆኗቸው
ሐዋርያት ጀተው ሥጋውን ሊቀብሩ
ወደጌቴ ሲማን ይዘዋት አመሩ
ደግሞ እንደ ልጇ ትነሣለች ብለው
አይሁድ ዚያታዋሷት መጡ ተሰብስበው
ታውሩንያ ዘሉ አልጋውን ሲይዘው
የታዘዘ መልአክ እጆቹን ቆረጠው
ለርሷ ግን ደግነት ልማጇ ነውና
በክብር ተነጠቀች እጆቹን አድና።
የሐንስ ሲመለስ ልቡን ደስ እንዳለው
በዕፀ ሕይወት ሥር መሆኗን ነግሯቸው
ሱባዔ ጀመሩ ሊያዩአት ተመኝተው
ሁለት ሱባዔ ጸመው ነሐሴን
አምጥቶ ሠጣቸው ጌታ ሥጋዋን
እነርሱም ተበሯት በጌታ ሲማን።
በስስተኛውም ቀን በዕለተ ሠሉስ
ከሙታን ተነሣች እንደ ክርስቶስ
በመላእክት አጀብ በጥውም ማጎሌት
ተግስ በጸሙና ስታርግ አያት
ዕርገቷን ከተግስ ሐዋርያት ሰምተው
በዓመቱም በአንድነት በሱባዔ ተግተው
በአሥራ ስድስት ቀን ጌታ መጥቶላቸው
በርሷ መንበርነት ተድሶ አቁርቧቸው
ዕርገቷን ሰበኩ በዓለም ሁሉ ዞረው።
ወትተውም ንግሥት እንዳለ ጸዊት
ሕያው ሆና አለች ዛሬም የእኛ እናት
በልጇ ቀኝ ሆና ከብራ በስብሐት
ለፍጥረቱ ሁሉ ስታሠጥ ምሕረት

ለ. /ፍልሰታ ሥጋሁ ለቅዱስ ጊዮርጊስ/

ፀሐይ ከመመላለስ ማይ ከማፍሰስ እንደማያቋርጥ ክርስቶስን አልከድም የሚል አንድ እንኳ በጠፋበት ጊዜ በክርስቶስ አምላክነት የጣያትን ከንቱነት በመመስከር ያለማቋረጥ 7 ዓመት ሲሰቃይ 3 ጊዜ ሲሞት ሲነሣ ቆይቶ በ4ኛው ሚያዚያ 23 ቀን ዐርፏል። ጌታም እንደወደደው ወዶታልና እንዳከበረው አክብሮታል ና ዕረፍቱን እሱ ለቤዛ ብዙኃን በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ባረፈባት ዕለተ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት አንዳደረገለት ፍልሰተ ሥጋውንም ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕርገተ ሥጋ ጋር አንድ አድርገው እንዲያከብሩት በዚሁ ዕለት በሀገረ ሙላዱልዳ በስሙ ወጳንጹለት ቤተ ክርስቲያን እንዲያፈልሱት አድርጓል።

ሐ. ዕረፍቱ ለጊጋር መስፍን ሶርያ

መስፍን ሶርያ ነበረ። እመቤታችን ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ ከዚቱ እንግድነት ሰንብታለች። ወጥታ ከሄደች በኋላ የሄርድስ ብላቴኖች መጥተው እንዲህ ያሉ ሰዎች ከቤትህ ገብተዋል። አውጣ አሉት። እኔ በእጃችሁ ቤቷ ከፈታችሁ ገብታችሁ ማየት ትችሉ የለምን አላቸው። ገብተው ፈልገው ቢያጧቸው ደብቀህቸው ነው እንጂ ብለው ባሰይፍ መተውታል።

➢ ሰማዕት የሆነው በ 2 ዓ.ም ነው።

ነሐሴ 22 ዕረፍቱ ለሚኪያስ ነቢይ

ሚኪያስ ማለት መኑ ከመ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም ነው። ቁጥሩ ከ 12 ደቂቀ ነቢያት ነው። ንጉሡ አክዓብ ይባላል። የይሁዳውን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ከኔ ጋራ ወደ ሬማት ዘገለዓድ አትወጣምን አለው። ያስ ቢሆን ፈታደ እግዚአብሔር ሳንጠይቅ ይሆናልኋ አለው። ደግ ነገር አይናገርልኝም እንጂ ሚኪያስ ወልደይምላ ነብር አለው። ጥሩት አለ፡ ነቢየ እግዚአብሔር ወደሬማት ዘገለዓድ ልውጣን አለው። አስራኤል ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ቢቅበዘበዙ አይቻለሁና ሂድ ተከናወን አለው ይሸውልየ ክፋ እንጂ ደግ ነገር አይናገርልኝም አላልሁምን አለው። አንተ ከነቢያት ሁሉ የተለየህ ነህን አሉት። እሊያንማ ጌታ አክዓብን ወደሬማት ዘገለዓድ እንዲወጣ የሚያታልል ማነው ቢል ከመናፍስት አንዱ እኔ በነቢያቱ አፍ መንፈሰ ሐሰት አለው። ሲዲቅያስ ዘሱ ፈቱን ጸፋው። አክዐብም በደኅና እስክመለስ ድረስ የመከራ እንጀራ እየመገብህ አኑረው ብሎ ወደ ኢዮአስ ሰደደው። ያም አልተረ አክዓብ በጦር ተወግቶ ሙቷል። እስራኤል ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ተቅበዝብዘዋል። 2 ዜና 18:1 – 3

ከዚህም የበለጠ የሥጋዊ ነገር ተገልጸልት ወእንቲኒ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ ኢትቲሁቲ እምነገሥተ ይሁዳ አስመ እምኔኪ ይወድእ ንጉሥ ዘይፌሥሎ ለሕዝቡየ እስራኤል ሲል የጌታን ከሰማያት መወረድ በቤተልሔም መወለድ አንድም ቤተልሔም ቤተ ኅብስት ከተባለች እመቤታችን እንደሚወለድ ትንቢት ተናግሯል። ሚክ 5:2

ከዘሁም በኋላ እስከ ሕዝቅያስ ዋልዲአ ካዝ ንጉሠ አስራኤል ድረስ አስተምሯል።

➢ መዋዕለ ትንቢቱ ከ 735 – 688 ዓ.ም ነው።

ነሐሴ 24 ዕረፍቱ ለቶማስ ዘመርዓስ

በመርዓስ ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሟል ሲያስተምር ዐሳዉያን ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ ዐጽቱ ዐጽቁን እየቆረጡ ለጣዖት ሲያጥኑት ኑረዋል።

ከዚህ በኋላ ዘመነ.ሰደት አልፎ በንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ቀርነሃይማኖት ቆሞ ባለ አርዮስ ወልድ ፍጡር ብሎ ተነሣ። ንጉሡ በኒቅያ ጉባዔ ይሁን ብሎ አዋጅ ነገረ። ደቀመዛሙርቱ በቅርጫት አድርገው በአህያ ጭነው ሲሄዱ ካደረሱት ቦታ አርዮሳውያን ሌሊት ካደረበት አህዮቹን አንገት አንገታቸውን ቆርጠው ጣሏቸው። እሱም በጸጋ እውቆ ካህ ሳይቀድ ተነሥቶ ልጆቼ ሜኑ አላቸው። ቢሄዱ ተቆራርጠው አገኟቸው ምኑን ሜነው እንዲህ አድርገዋቸዋል አሉት። ራሳቸውን ካንገታቸው ገጠሙ አላቸው። አህዮቹ አንዲቷ ጥቁር አንዲቷ ነጭ ነበሩ። የነጭነቱን ከጥቁሪት የጥቁሪቱን ከነጭቱ አድርገው ገጠሙት። ቢባርካቸው ተነሥተዋል። ከዚያም ሲደርስ ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ ስነ. ጽድቁን ተረድቶ አባቴ በረከትህ ይድረሰኝ አያለ ከሰይፍ የቀረ ሰውነቱን ዳሰታል። አርዮስን አውግዞ ሃይማኖት መልሶ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ብዙም አልቆየም በዚህ ዕለት ዐርፏል።

ለ. ዕረፍቱ ለአቡነ ተክለሃማኖት/ከ 1215-1313/

ተክለሃይማኖት ማለት ተክለ.አብ ተክለ.ወልድ ተክለ.መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው። ብሔረ ሙላቸው ጽላልሽ /ዞረሬ/ ነው። አባታቸው ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚአ ኃረያ ይባላሉ። ቀዳሚ ስማቸው ፍስሓ ጽዮን ነው። ዓመት ከሶስት ወር ሲሆናቸው በምድረ.ሸዋ ይልቁንም በጽላልሽ ረሀብ ሆነ። እግዚአ ኃርያ የቅዱስ ሚካኤል በዓል ሲታሳልብን ነው? አያለች ስታለቅስ እንባዋን ጠረጉላት የቅዱስ ሚካኤል በዓል ሊታገልብኝ እንደሆነ አያውቅ ምን ይሰኛል ብላ ጡቷን አሳረስቻቸው። መጥባቱን ትተው ወደ ቤት አንድታገባቸው አመለከቷት። ይዛቸው ገባች። አፍኝ የስንዴ ዱቄት ያለበት እንቅብ ነበረ። እጇቸውን ቢጭንብት መልቶ ፈሰሰ። ዘጠኝ እንቅብ አስመጥታ አቀረበችላቸው። አየዘገኑ ጠብ ጠብ ቢያደርጉበት ዘጠኙም መልተው ተገኝተዋል። የቅቤውንም ማሰር

አስመጥታ እቅቸውን ብትከተው ከአባት እንደ ጣዱት ፈልቶ መልቷል። ሌላውንም የሚያስፈልጋትን ሁሉ በእቅቸው እየዳሰሰ አበርክተውላታል። ይህንንም በዓይነቱ አዘጋጅተው መጋቢት 12 ቀን በቅዱስ ሚንኤል ስም የወጣ የወረዳውን ያሰፈ ያገደመውን ሁሉ ሲያበሱ ሲያጠቡ ውለዋል። አነሱም እንጂ የረሀቡ ዘመን አስኪያልፍ ድረስ ሲመገቡት ኑረዋል።

ስለት አመትሲሆናቸው አባት እናታቸው ሕይወት ብነበጽዮን ስሚባል መምህር ስሚቸው። ጌታ ልቡናቸውን ብሩህ ልሳናቸውን በሊህ አድርጓቸው መምህራቸው ከሚነግራቸው ሌላ መጻፍትን አንብበው ምሥጢር የሚተረጉሙ ሁነዋል። ከዚህ በኋላ ጸጋ ዘአብ ዲቁና ሲያሾሚቸው ከአባ ጌርሎስ ይዘዋቸው ሄዱ። ቅዱስ ሚካኤል እስመናሁ ይመጽአ ንዜነ ወልድ ኅሩይ ዘኢይከውኑ ሰማይ ወምድር ሄጠ.አሐቲ ሥዕርተ.ርእሱ-ሰማይና ምድር የአንዲት ጸጉሩ ዋጋ የማይሆኑ የእግዚአብሔር ምርጥ መጥቷልና ተቀብለህ መዓርገ.ዲቁና ሰጥተህ አሰናብተው አላቸው።አላቸው ተደስተው አነሱንም አስደስተው ተቀብለው መዓርገ ዲቁና ሰጠተው አሰናብተዋቸዋል።

ሲመለሱ ጊዜው መሸተባቸው ስንት አልቆባቸው ከመንደር ገብተው ሰላም ለእናንተ ይሁን አሏቸው። እናትህን ሰላም ይንሳት ምን ልትሆን መጥተህል አሏቸው። ይልቁንም አንዱ ፊታቸውን ጸፋቸው። ወደጌታ ቢያመለክቱ ቅዱስ ሚካኤል በአውታረ.ነፋስ ውሃሮበአስዋጠ.አሳት እየገረፈ ማረኝ ማረኝ አሰብሎታል። መጸጸተን አይተው ጸልየው አውርደውታል።

መሠርያን መስለውት ጸልቷቸው ነበር። አሁን ግን ከቤቱ አስገብቶ ማዕድ ሠርቶ መግቢቸዋል። ሚስትና ልጁ ድውያን ነበሩ። የእቅቸውን የእግራቸውን አጣቢ ቢረጫቸው ድነው ተነስተዋል። በዚህ ጊዜ የ1ኛ ዓመት ልጅ ነበሩ። አካለ መጠን ሲያደርሱ ሚስት አሞተው አመጡላቸው። ሽሽተው ሄደዋል። ከዚያም ዘንድ ከጸጸሉ ከአቡነ ጌርሎስ ሄደው መዓርገ ቅስና ተቀብለው ለቀ ካህናት ዘምድረ ሸዋ ተብለዋል። ከዚህ በኋላ አባት እናታቸው በ 5 ቀን ልዩነት ተከታትለው ዐረፉ። ዕዳሰ.ማውታ ሁኔ ቀረሁ ብለው አዘኑ። አንድ ቀን ሲያድኑ ወደ ዱር ሄዱ። ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ ለካህናት የማይረባውን አይን ልታድን መጣህን አላቸው። ወዲያውም ጌታ በቅዱስ ሚካኤል ክንፍ አርፎ ኢፍቀርየ ፍስሓጽዮን ናሁ ኅረይኩከ ከመ.ትኩን ሐዲስ ሐዋርያ -ሐዲስ ሐዋርያ አንድትሆን መረጥሁህ እምይእዜሰ ኢትንሰው አራዊተ አላ ትንውነፍሳተ አንግዲህም ነፍሳትን አንጂ አንሰሳ አታድንም ስምከሰ ይኩን ተክለ.ሃይማኖት ስምህም ተክለ ሃይማኖት ይባላል ብሏቸዋል። አላቸውም ይህን ከሰሙ በኋላ ልዋል ልደር አላሉም። ሰሰቱን ቤታቸውን ከፍቱን ትተው ማስተማር ጀመረዋል። ጣዖታቱን እያፈራረሱ ኢጋንጉቱን እየደመሰሱ ከተታ ደረሱ በወንጌል እመነ ክርስትና ተቀበሉ አሏቸው። እምላክችንን ትተን አይሆንም አሉ። ማንን ታመልካላችሁ? አሏቸው። ብንቸገር የሚረዳን ብንታመም የሚያድነን ታሳት ዛፍ አለ አሏቸው። እንግዲያስ እኔም እንድሰግድሰት ካለበት አድርሱኝ አሏቸው። ይዘዋቸውሄዱ። ሲደርሱ ሶስት ምዕራፍ ሲቀራቸው በዚያ ያደረ ሰይጣን ተነስሃይማኖትን መልሰክኝ እያለ ይጮህ ጀመረ። ስምህ እንግዳ ምግባርህ እንግዳ አምላካችን አልወደደህም ከዚህ ቶይ አሏቸው። ወደጌታ ቢያመለክቱ ዛፉ ተነቅሎ መጥቶ ከፊታቸው ቆመ። ሰይጣኑንም ቅዱስ ሚካኤል በሐጸ.እሳት እየነደፈ አጠፋው.ው። ዛፉ ሲነቀል ከሥሩ ጎንበስ ቀና ሲሉ የነበሩ ሰዎች



ሞተው ነበር። ቀድሞ ከሞቱትም 15ቱን ፈጠምረው አስነስተዋቸዋል። በዚህም በዚህም ከሰምንት አልፍ ያላነሱ ነፍሳት አምነው ተጠምቀዋል።
መስፍን.ብሔሩ ድል አሰግድ ይባላል። በዚህ ዛፍ ምክንያት በቀን 100 ወቂት ያገኝ ነበር። እንግዲህማ ይህ ሁሉ ሲቀርብኝ አይደለምን ብሎ ብላቴናቹን አስከትሎ ሄደ። አላቸው ለመፍቀደ ደብር ይሆንኛል ብለው ያን ዛፍ ያስፈልጠ ነበር። እማላቸዋለሁ ብሎ ሲንደረደር የአንጨት ስንጣሪ ከላይኑ ገብታ አንደ አሳት ጠበሰችው። ዋይ አለ ፈውሰውት ከነቤተሰቡ አምኖ ተጠምቋል።
ከዚህ በኋላ ምድረ.ጻሞት ገቡ። ንጉሡ ሞተሰሚ ነው። ከወዴት መጥተህል አላቸው። እማልከትህን አንጻጠፋ ከጌታ ተልኬ መጥቻለሁ አሉት። አንተን እንድናመልክህ መጥተህ ብሎ በቀፎ አድርጎ ጠመግራር ከሚባል ገደል አስጣላቸው። ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ከንጉሥ ፊት አደረሳቸው። ሁለተኛ አስጣላቸው። የጣኒቸውን ብላቴኖች ቀድመው ከደጁ ተገኙ። ይህ መሠርይ ብሎ ሰይቱን ቢወረውር ከእጁ ተጠቅልላ ቀረች። ሁለተኛም ቢወረውር ከእጁ ተጠቅልላ ቀረች ሥቃዩ ጸናበት። ዋይ አለ። ያድኑኛል ይጠብቁኛል የምትላቸው ካህናተ.ጣዖትህ አያድኑህምን አሉት አስጠርቶ አድኑኝ አላቸው። የዚህን ሥራይ መፍታት እንደምን ይቻለናል አሉ። እኔ ካዳንኩህ እነሱን ካላዳንኩህ እኔን እንድትቀጣ ቃል ግባልኝ አሉት። ቃል ገባላቸው። ጸልየው አድነው.ታል። ይልቁንም ከ 25 አመት በፊት እናታቸው እግዚእ ኃሌያን አማሰሁ ብሎ ከጣዖቱ ፊት ባቆማት ጊዜ በተፈጸመው ግሩም ርእይ ልቡን አጥቶ አንድ ጊዜ ገደሉት አንድ ጊዜ አድኑት ከአየር ላይ ቤት ስሩልኝ ከምድር በታች ዘር ዝሩልኝ ሲል ደናር ነበር ከዚህ ሁሉ ጀመሰለው.ታል። ካህናተ.ጣዖቱ ገበሰይፍ አስፈጅቷቸዋል።

አሱም አምና ተጠምቋል። ከዚህም የበዙ ተአምራትን እያደረጉ አያስተማሩ አብያተ ክርስትያናት እያሠሩ 12 ዓመት ኑረዋል።

ከ 12 ዓመት በኋላ ወደ ምድረ አምሐራ ሄደው ከአባ በአሉት ሚካኤል ገዳም አዕል አየፈጩ ሙሃ አየቀዱ እንጨት አሰበሩ ይልቁንም ሐሙም አየፈወሱ ሊጋንነትን እየደመሰሱ 10 ዓመት ኑረዋል። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል ሐያቱን እንደ ደንቢያ እንደ ብረት አጽንቶላቸዋው በአግራቸው አየተራመዱ ከአባ ኢየሱስ ሞአ ገብተው ልብሰ ምንኩስና ለብሰው በጾም በጸሎት ተወስነው 10 ዓመት ኑረዋል። ከ10 ዓመት በኋላ ደብረ ዳሞ ገብተው ከአባ ዮሐኒ አስኬማ ምንኩስና ተቀብለው 10 ዓመት አገልግለዋል። በዜዳ ጊዜ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ይሙት በቃ ብሎ የማጠርዱበትን ገመድ ከሥሩ ነቀለባቸው። ጌታ ሆነራ በቀኝ ሶስት ሶስት /ስድስት/ አክናፍ ሠጥታቸው በዚያ በረው ወርደዋል።

ኢየሩሳሌም ደርሺ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነስቼ ልምጣ ብለው በሠረገላ ብርሃን ተጭነው ሲሄዱ በጽንፈ ኤርትራ አንድ ሙት አገኙ። እንተ ምውት ለእመ ኮነ ክርስቲያነቂ ተንሥእ እብለክ በስሙ ለአግዚአየ ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥ አሉት። ተነሥኧል። ምን ሆነህ ሞትክ አሉት። ኢየሩሳሌም ሂጀ እጅ ነስቼ እመጣለሁ ብዬ ከዚህ ስደርስ ውኃ ጽም ጸንቶብኝ ሞትኩ አላቸው። አስከትለውት ሄደው ቅዱሳት መካናትን ተሣልመው ሊቀጳጳሰቱ ዮሐንስ ይባላል እጅ ነስተውት ተመለሱ። በዚህ ዓመት ሶስት ጊዜ ኢየሩሳሌም ደርሰው ተመልሰዋል። ሊቀጳጳሳቱ መነኮስ በዓት ሠርቶ ብፅዓት ገብቶ በጽሙና በብትሕውና ይኖራል አንጂ ይዞራልን በዓት ሰርተህ ብፅዓት ገብተህ በጽሙና በብህትውና ኑር አላቸው። ከኤርትራ ጀምረው እያስተማሩ ተመልሰው በደብረ ሊባኖስ በዓት ሠርተው ብፅዓት ገብተው ተቀምጠዋል። በዚህም ላይ አጋንንቱን መሠርያኑን በኃይለ አግዚአብሔር ድል ነስተው አሕዛብን በሃይማኖት ወልደው በምግባር አሰድገው የሚኖሩ ሁነዋል። ካመኑት ብዙዎቹ አሣቸውን ተከትለው ከወገኖቻቸው ተለይተው ሥርዓተ ምንኩስና ተምረው በጽሙና በብሕትውና የሚኖሩ ሁነዋል። ከሳቸውም ፍጹምነት የተነሣ ደቀመዛሙርቶቻቸው ወንዶችም ሴቶችም በግብረ ኃጢአት ላይተዋወቁ ባንድ ላይ ያድሩ ነበር።

ከዚህ በኋላ ከበዓታቸው ገብተው ወደፊት ወደኋላ ቁጭ ብድግ እንዳይሉ ከፊት ከኋላቸው ከግራ ከቀኛቸው ስምንት ጦር ተክለው ሱባዔ ያዙ። ከቁመት ብዛት ከገድል ጽናት የተነሣ አንድ እግራቸው ጥር 24 ቀን (13 06 ዓ.ም) ተቆርጦ ወድቋል። ከዚህም በኋላ ባንድ እግራቸው ቆመው 7 ዓመት ኑረዋል። ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ እመቤታችንን መላእክትን ነቢያትን ሐዋርያትን ጻድቃን ሰማዕታትን አስከትሎ መጥቶ ኢፍቁርየ ተክለሃይማኖት ወዳጀ ተክለሃይማኖት ሆይ ሰማዕኩ ጸሎተከ ወስእለተከ ልመናህን ሰምቼ ወናሁ አእርፈከ እምብዙኅ ጸማ ከድካምህ ላሳርፍህ መጣሁ ኀበ ሀሎ ፍስሓ ህየ አነብረከ መንፈሳዊ ደስታ ካለበት አሳርፍሀለሁ እምዝ ዳግመ ኢይፈክዘከ ሞት እንግዲህም ሁለተኛ ሞት አያገኝህም በተስፋህ ያመነውን በቃል ኪዳንህ የተማጸነውን ሥጋህን የቆረስክበትን ደምህን ያፈሰስክበትንም ቦታ እጅ የነሣውን ሁሉ ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም አድንልሀለሁ በዚህችም ቦታ በተስፋህ ጸንተው በክዳንህ ተማጽነው የሚኖሩ ልጆችህን እንደ ሰማይ ከዋክብትን ባሕር አሸዋ አበዛልሀለሁ ብሎ ተስፋቸውን ነግሯቸዋል። ከዚህ በኋላ ሕማመ ብድበድ ለሞታቸው ምክንያት ሁናቸው በተወለዱ በ 99 ዓመት ከ 10 ወር ከ 10 ቀናቸው በዚህ ዕለት ዐርፈዋል።

አባ ተክለሃይማኖት ክቡር ወቅዱስ ከክህደተ ያለተማ ከአጋንንት ግዛት
ሐዲስ ሐዋርያ ሶታሬ ተማስ። በወንጌል ቃል ማርከ ነፍሳትን ከሞት
እርሱን ለምስጋና ጌታ ቢመርጠው እጅ መንሻ አቀረበ በአምላኩ ፊት
ኘ የእናቱን ጡት ጠብቶ ሳይጠግበው ጻድቃንን እናክብር ስንኖር በምድር
ቅዱስ ቅዱስ ብሎ አመሰገነው። እንደተናነገረው ዳዊት በመዝሙር
በጥዋም ምስጋናው በሥሙር ጸሎቱ ጽግ ጻድቅ አባት የሕግ መምህር
በአምላክ ቢረክት ተመላች ምድሪቱ። ቢረክት ያሰጣል መንፈሳዊ ክብር።
መንፈስ ቅዱስ በርቡ ሰላደረበት

መዝ 53:6 ማቴ 10:41 ·

ሊ. ዕረፍታ ለ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ

ሀገሯ ቡልጋ ቅዱስጌ ነው። አባቷ ደርባኒ ኢናቷ ዕሌኒ ይባላሉ አካለ መጠን ስታደርስ ሠምረጊዮርጊስ ለሚባል ደግ ካህን ዳሯት። ሁለት ልጆች ወልዳለታለች። ንጉሡ አጼ ገብረመስቀል የልቧን ትንነት የግብሯን ደግነት ሰምተው የምትሰብሰው የምታነጽፈው አልባሲውርቅ ወጥተው ወርደው የሚያገለግሏት 174 ብላቴኖች ሰደውላታል። አንዲቷ ቤጠባዬአዋ በሥራዋም ታስቆጣት ነበር። አንድ ቀን ከአሳት ዳር ሳሰች አገኘ አጣውን እየቀባጠረች ብታስጨንቃት ፍሙን በአጇ ታፍና ከአፏ ጣለችባት። ቁስላ ሞታለች። ሕገ.እግዚአብሔር አፍርሺከጌታዬ ተጣልቼ የምሾልክበት ቀዳዳ የምሮጥበት ሜዳ አጥቼ ቀረ ብላ ታስቅ ስ ጀመር ወዲያውም ይህች ቁላቴና ብታነሳልኝ ከዓለም ተለይቼ ገዳም ገብቼ ባገለገልሁህ ነበር አለች። ተነስታለች። ከዚህ በኋላ አልባስ ምንኩስና አዘጋጅታ ሕፃኑን ወንድ ከዚህ አደፃብም ቢሷት ከአንቀፁ ትታ ገብታለች። ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ሄርድስ ካስፈጃቸው 14 አልፍ ከ4 ሺህ ሕፃናት ደበሮታል። አሷንም በክንፉ ተሸክሞ ጽንፈ ጣና አድርሷታል።

ከመከራዋ ብዛት ከገድሏ ጽናት ሰውነቷ ተቡሰስቶ የዓሣ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ክፍሉሩ ገብታ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ላትል 12 ዓመት ኑራለች። ጌታ መጥቶ ምን እንዳደርግልሽ ትወድጃለሽ አላት። ከአንጨት የማይጠሰ ከብረት የማይዝግ ከሰውም የማይበድል የሰምና ውሉዲአዳም እንዳይሰቁ ዲያብሎስን ማርልኝ አለችው። ምሕረትን ቸርነትን አይሻም እንጂ ከሆነልሽስ ጠርተሽ አምጪው አላት። ቅዱስ ሚካኤል ወስዶ ጽንፈ.ሲኦል አደረሳት። ጌታ ምሬሐለሁ ብሏልና ና ውጣ አለችው። በምድር ፈልጌ ባጣሽ ሳዝን እኖር ነበር አሁንማ ከቤቴ መጣሽልኝ ብሎ ጎትቶ አስገባት። ቅዱስ ሚካኤል ተከትሎ ገብቶ በክንፉ ነጥቆ አውጥቷታል። ስትወጣም ስለመከራዋ ብዛት ስለ ገድሏ ጽናት 6 ክንፍ ተሰጥቷት ነበር።። በዚያ ነፍሳትን ማርካ ወጥታለች።

ከዚህ በኋላ ዜና.ገድሏ ስነ.ጸድቋ በየአህጉሩ ተሰምቶ ከ 1279 ያላነሱ ደናግል ተሰብስበውላት ጽመና ብሕትውና የምታስተምራቸው ሆናለች። በፍጻሜ ዘመኗ በቁመቷ ልክ በዓት ሠርታ ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ 12 ጦር ተክላ ወዲያ ወዲህ ላትል ቆማ 12 ዓመት ኑራለች። ከዚያውም ዘንድ አሰግዳለሁ አያለች ጎንበስ ቀና ስትል ሥጋዋ በጦር ተወግቶ ተፈቶላ አልቋል። ጌታም ይህን ሁሉ መከራዋን አንደመሥዋዕት ቆጥሮላት አእላፍ መላእክቱን አስከትሎ መጥቶ በተስፋዋ ያመነውን በቃል ኪዳኗ የተማጸነውን አስከ

ለሰምታ ይድረሰት ለክርስቶስ ሠምራ
ለውን የምታስምር ራሷ ተምራ።
ቤት ንብረት ልጃነን ትታ ዘመዶቿን
ጋሽዋ አድርጋ መከታ አምላኳን
በትዝርምት ኖረች ለአያሌ ዘመን፡
በጭለት መዋረድ መረገም በጸደን
ነፍሷ ተጨንቃባት ተሰምቷት ጎዘን
ይተወዋል ብላ ስቶ ማሰቱን
ያንን ከንቱ ፍጡር ዓመጻኛውን

ትተከው ውሻና የሳት ግሳቱን
ላስታርችህ አለችው ከአምላክህ አሁን።
እርሱ ግን ውርደቱን ቀጥሮት እንደክብር
አልወደደም ከአምላክ ታርቆ ለመኖር
ድርም አይጥግትም ለክህያ ማር።
ከፈጣሪ ጋራ ተጣልቶ መኖር
እያዩ መግባት ነው ወደእሳት ባሕር።
ይሉትስ ይሽሳል መታረት በቶሱ
ዋይ ዋይ ላለማለት በሊአል ተጥሱ።

ሐዋ 9:5 2 ቆሮ 5:16-21

ነሐሴ 28. ተዝካሮሙ ለአብርሃም ወይስሐቅ ወያዕቆብ /ከ 2000 - 1825 ዓ.ዓ/ከ 1900 1720 ዓ.ዓ እና ከ 1840 1693 ዓ.ዓ/

አብርሃም ማለት አቢሀኩታን ማለት ነው። ትውልዱ ከነንዲሁም ነው። አባቱ ታራ ይባላል፡ ከፍጥረት ጉበተው ቢቆጥሩት ሃያ አንደኛ ትውልድ ነው። ዓቢር የሚባል ወንድም ነበረው ኢያ 24:2 ሚስቱም ሣራ ትባላለች። አባቱ ታራ ዩቅራጣስ ያደረበት ጣያት እየቀረጸ የሚሸጥ ነበር። አንድ ቀን ሽጠህ ና ብሉ ጣያት አዜዘው። ከሣንድ ራሰና አብላኛ ጠማኛ አጠጣኝ አለው። ዝም አለው ያም ባይሆን አጫውተኝ አለው። ዝም አለው። ከዚያ ሲደርስ ዓይን አያለው የማይሰማ እግር ሳለው የማይዳስስ እጅ ሳለው የማይዳስስ አምላክ አለላችሁ ግዙ አለቸው። የማያውቁት እሱ ያዋረዱውን ማን ይገዛቸል ብሉ ይደኮግል ብለው አደነቁበት የማያውቁትም አብርሃም ሣሬስ አእምሮውን አጣ ብለው ዘበቱበት የሚገው አጥቶ ይጽ ሲመለስ ራብኛ አብላኛ ጠማኛ አጠጣኝ ያም ባይሆን አጫውተኝ አለው፣ ዝም አለው። አሳዋቂነቱ እንጂ አንተማ በፍጡር እጅ የተሰራህ እንጨት አይደለህማ ብሉ ከላይ ዳንጊያ ከታች ደንጊያ አድርጎ ቀጥቅጦ ሰብሮታል። ከዚህ በኋላ ማንን ላምልክ ብሉ አምላኩን ይፈልግ ጀመረ። ነፋስ ረቂቅ ነው የሚዳሰበት የሚመዝነት አይታወቅም እሱን ላምልክ አለ። ቢመሸምረው ግድግዳ ተራራ ሲከለክለው አይቶ ሕጸጽ አገኘበት። እሱን ትቶ ውኃ ቢታጠቡት ያነጻል ቢጠጡት ያረካል እሱን ላምልክ አለ። ቢመረምረው አፈር ጠጠር ሲገድፍው አይቶ ሕጸጽ አገኘበት። እሱን ትቶ ፀሐይ ብርሃኑ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳል የረጠበውን ያደርቃል እሱን ላምልክ ብሉ አሰቡ። ቢመረምረው ቀንና ሌሊት ሲፈራረቀው አይቶ ሕጸጽ አገኘበት። ከዚህ በኋላ አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ የፀሐይ አምላክ ተናገረኝ አለ። ጌታም ሃይማኖቱን ለማጽናት አብርሃም አብርሃም ጻእ እምህገርከ ወተፈለጥ እምአሕማቲከ ከመየጥከ ተሰይተህ ከሀገርህ ወጥተህ እኔ በምላይህ ቦታ ተቀመጥ አለው። አባቱ ሞቶ ነበር ግሰቱና የአጎቱ ልጅ ሎጥን አስከትሎ ከቡቱን ንድቶ ሄዶ በከነንን ተቀመጠ።

በዘሙት ረሀብ ቢሆን ወደግብጽ ተሰደደ። ሚስቱ ሣራ ከአቦር ጥፍጅ አስከራስ ጸጉሯ ድረስ ደህ ቀረጀ የማትባል ቆንጆ ነበረች። አጎቱ አንቅን ሲሉ እኔን እንዳይገድሉኝ እህቱ ነች አለሁ ወንድሜ ነው ብይ አሉት። እሽ አሰችው። ፈርዖን አሱን ከአንግዳ ማረፊያ አስቀምጦ እርሷን ወደ እልፍኝ አስገባት። የታዘዘ መልክ መጥቶ ገሠጸው ቤተሰቡንም መቅሰፍት መታቸው። ጠርቶ ለምን ሸዋገከኝ አለው። ብፈራ አለው የወንድ ባሪያ የሴት ባሪያ ወርቅ ብር ከብት ሠጥቶ አሰናበተው። ዘፍ፡ 12:10-20 ከዚህም በኋላ ባለሸጋ ሁኖ በክብርን ይኖር ነበር። ከደግነቱም የተነሣ ቤቱን ከተመሳቀሰ ጎዳና ሠርቶ... ብሰህ ከጥጽ - ተርክ ተጨግራ ከዚያ በፊት አብርሃም ልጅ አጥቶ ሲያዝን ይኖር ነበር ከሰያልዩ ባንዱ ወደ ሚዳ ወስዶ ቁልት ከየክብተ.ለማይ የሰማይ ከየክብትን ቁፐር አለው ሊይክል ቁል ቆቶሙ አይቻለኝም አለ። ከማሁ ይክውኑ ዘርዕከ ዘርሀ እንዲሁ ይበዛሉ ብሎታል። ከቀኖትም ባንዱ ከክሕር ወሰዶ ቁልት ኖዲባክር የባክርን አሸሞ ቁፐር አለው። ሊይክል ቁልቆቶሙ አይቻለኝም አለ። ከማሁ ይክውኑ ዘርዕከ ዘርሀ እንዲሁ ይበዛሉ ብሎታል። ወተአመነ በክሱ ልቡ ከመ ይክል ገቢራሱቱ እግዚአብሔር ይለል እኔ ሙቀት ልምላሜ ተለይቶቸል ሚስቱም ልማደ አንስት አልፎባታል፡ ሳይል ይህን ሁሉ እግዚአብሔር ሊያደርግለት እንደሚችል በፍጹም ልቡ አመነ ማመኑም ጽድቅ ሆኖ ተቆጥሮለታል። ዘፍ 15:1-7 ሮሜ 4፡ 17-24

ከዚህ በኋላ ዘመነረሀብ ቢሆን በምድረገራራ መጻተኛ ሁኖ ተቀመጠ። ንጉሡ አቢሜሊክ ይባላል። ምንህ ናት አለው። እኅቴ አለ። የሰባ አርዶ የጻራ አውርዶ ሲበሉ ሲጠጡ ቆይተው ሲመሽ ወደ እልፍኝ ይሂት ገባ ባታ ብልቱን በአብጭ ቀመታው፡ ዋይ አለ። ሰባለቤቷ ካልመለሰሎ ት ትሞታለህ አለው። አስጠርቶ ለምን እኅቴ ናት አልክ አለው ብሬራ አለው። ጸልዮ መቅሰፍቱን አርቆለታል፡ ሰርቡም ሚስቱን መልሶለታል። የሚኖርበትን ቦታ የሚተዳደርበትን ከብትና የወንድ የሴት ባርያ ሰጥቶታል፡ ዘፍ 20:1-18 ከዚህ በኋላ ጌታ የሚያደርገውን አይናገር የተናገረውን አያስተር ውንድ ልጅ ሰጥቶታል።ስሙን ይስሐቅ ብሎታል። ትፍሥሕት ማለት ነው። በ8 ቀን ግዝረት ፈጽሟል። ዘፍ 21፡ 1-4

ከጊዚያት ባንዱ ጌታ ብሎ አርክ በዲቢድር አብርሃም ፍቁርየ በምድር ላይ አብርሃም ወላጀ አለኝ አለ። መላእክትም ተቀብለው አብርሃም ፍቁረአግዚአብሔር አብርሃም አርክ እግዚአብሔር ብለው አመሰገኑ። ሰይጣን ሰምቀኝነት አያርፍምና እንዲያው ወላጀ ትሰዋለህ እንጂ ካረጀ ካረጀ በኋላ የወለደው ልጁን ሠዋልኝ ብትሰው አይሠዋልህም አለ ጌታም የአብርሃም ጽድቁን የሰይጣን ሐሰቱን ለመግለጽ አብርሃም አብርሃም ሠሪ ሊተ ይስሐትሃ ወልደከ ይስሐቅ ልጅህን ሠዋልኝ አለው። ቆይ ዛሬ ነገ ስትል ታዘናጋኛለች ብሎ ሰሣራ ሳይነግራት እንጨቱን በአሀያ ጭኖ ብላቴኖቹን አስከትሎ ወደ ጥርያም ሄደ። ከእግረደብር ሲደርስ እኔና ልጀ መሥዋዕት ሠውተን እንመጣለን ከዚህ ቆዩኝ ብሎ ብላቴኖቹን ከዚያ ትቶ እንጨቱን ሰደስሐት አሸክሞ አሳቱን ቢላውን እሱ ይዞ ከርእሰደብር ወጡ። አባቱ እኔ እንጨቱን ይገሾሰሁ አንተ አሳቱን ቢላውን ይዘሀል የሚሰዋው በግ ወዴት አለ? አለው?። ልጀ በጉን ጌታ ያዘጋጃል አለው። ሁለተኛ መልሶ አባቱ የሚሠዋው በግ ወዴት አለ? አለው። ልጀ በጉን ጌታ ያዘጋጃል አለው። ከሶስቱ ተራሮች ባንዱ የብርሃን ዓላማ ተተክሎ ሲጠቅሰው አየ። ከዚህ ሠዋ ሲለኝ ነው

ብሎ ደንጊያውን ይጸፈጽፍ እንጨቱን ይረበርብ ጀመር። በጉ ሳይገኝ ደንጊያ መጸፍጸፍህ እንጨት መረብረብህ ስለምንድር ነው አለው። ልጁ በጉን ጌታ ያዘጋጀል አላልኩህምን አለው። እንግዲህ በጉ ከምን ተገኝቶ እኔን ልትሠዋኝ ይሆናል እንጅ አለው። ያስ ቢሆንትጠቀምበታለህ እንጅ ትጎዳበታለህን አለው። አገግዲያስ ጎልማሳ ነኝና ጸእረ.ምት ይዘኝ ስንፈራገጥ ልብ አራስህን እንዳልልህ እጅ እግሬን አሰረኝ አለው። አሠረው ዐይኔ ከብል ከብለል ቢል አይተህ ራርተህ እንዳትተወኝ በሆዴ አስተኛኝ አለው። ወአስከብ በከብዱ ይላል በሆዱ አስተኛው ቢላውን እንሥቶ ካንጉቱ ሊያሳርፈው ጌታ አብርሃም አብርሃም ኢታከብድ ኤደከ በላዕለ.ወልድከ ይለሐት አስመ አኮ ዘይድኅን ዓለም በደመ.ወልድከ አላ በደምየ /በደመወልድየ/ ዓለም የሚድን በኔ ደም /በኔ ልጅ ደም/ እንጅ በልጅህ ደም አይደምና እጅህን በልጅህ ሳይ አትዘርጋው አለው። ወረደ ሱቱ ቤዛሁ በማዕዘአኑዝ አቅርንቲሁ በዕፀ. ሳቤቅ ይላል መለስ ቢል ጸዓዳ በግዕ በሀረግሬሳ ተይዞ አግኝቶ ሠውቷል። ሁለተኛም መልአኩ ይቤ እግዚአብሔር መሐልኩ ለከ በርእሰየ አባርከከ በዘረዝተኖ ወእበዝዘ ለዘርዕከ ከመ.ከከቢሰማይ ወከመ.ኖጻ ዘድንጋ. ባሕር እስመ ኢከልአከኒ ወልደከ አንድ ልጅህ አልነሳህኝምና በዘረከቱ አባርክህሀለሁ ዘርህንም እንደሰማይ ከከብ እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ ብሎሰታል። ዘፍ፡-22:1-24

ሚስቱ ሣራ ቡተወለደች በ127 ዓመቷ ዐረፌች። በዓተ.ከዕበት ይላታል አልፍኝ ከአጻራሽነት ያላት መቃብር ገዝቶ.ቀብሯታል። ዘፍ፡- 23:1-28

አብርሃም ከይስሐቅ ሌላ 7 ልጆች ወልዷል። የመጀመሪያው አስማኤል ነው። ከአጋር ወልዶታል። ዘፍ፡- 16:15 6ቱን ከኬጡራ ወልዷል። ዘፍ፡ 25:1 አቀውም ሲዳንየ ዘምስሌሁ ተብሎ የተነገረለት ግን ይስሐቅ ነውና ስሊሎች ድርሻ ድርሻቸውን ሰጥቶ አሰናብቶ ይስሐቅን ርብቃ ወለተ.ባቱኤልን አጋብቶ በሀብቱ በንብረቱ አሠልጥኖት በተወለደ በ160 ዓመቱ ዐርፏል። ዘፍ፡- 25: 5-11

ስለአምላኩ ፍቅር ሁሉን እየማለ ብሎ ቃል ገባለት ጌታ ለአብርሃም
የፈጣሪን ፈቃድ ስለተከተለ ሆኖ ስላገኘው ታማኝ ያኔው ፍጹም።
የብዙኃን አባት አብርሃም ተባለ። ሰጥቴት ዘመኔ ለምታልፍ በቶሉ
አብርሃምአብርሃም የቅዱሳን ራስ ሕገጻ አላገዘም ቤት አልሠራምብሎ።
የተወለደ ለት ከዘሩ ከርስቶስ። በድንኪን ውስጥ ኖረ ያጣ ደኃመሉሉ
ዘመዶቹን ሁሉ ወናኖቹን ትቶ አብርሃም አብርሃም ደግ አባት መባሉ
ሩቅ ሀገር ሂዶ ከሀገሩ ወጥቶ እንግዳን በፍቅር ነው በመቀበሉ
በአባቱ ፈንታ አምላኩን ተክቶ። ጌታ ደግነቱን ቸርነቱን አይቶ
ዘርህ እንደ አሸዋ እንደ ኮከብ በዝቶ ከዚያች ከድንኳኑ እንደአገኘጓ ገበቶ
ስምህን ይጠራል ምድርን ሁሉ መልቶ። ባጅ አስደሰተው ወራሽ ልጅም ሠጥቶ።

የይስሐቅን ነገር ከዚህ ዮዋጉታል አባቱ ከዕረፍቱ አስቀድሞ ሊያውቀር የሚገባል ሱሴውን ጠርቶ ልጄን ከወንኖቼ ልጆች አንደ ከከነዓን ሴቶች እንዳታጋባው ማልልኝ አለው። ሕያው እግዚአብሔርን እንዳልከው ይሆናል ብሎ ከወርቁ የጸራውን መርጦ 10 ግመል ጭኖ ወደ መስጴጦምያ ሄደ። ወደግታ ከውሃ ጫር ተቀምጦ ያወጣ ያወርድ ጀመር። ውኃ ልሚቀዱት ብላቴኖች ከጌታዬ ዘመዶች ወገን ሁና መልክ ከደምግባት አስተባብራ የያዘች ውኃ አጠጭኝ ብያት አጠጥታኝ ግመሎቼንም ብታጠጣልኝ ኪያሃ አስተዳሎከ ሰንብርከ ይስሐቅ ለባርያህ ይስሐቅ አዘጋጀሀት ባልኩ ነበር አለ። ይህን ተናግር ሳይፈጽም ርብቃ ባጭር ታጥቃ ማድጋዋን ነጥቃ መጣች። ቀድታ ስትነሳ ውኃ አጠጭኝ አላት። ደስ አለው። የማን ልጅ ነሽ አላት የናኮር ልጅ የባቱኤል ልጅ ነኝ አለችው። ከቤትሽ ማደሪያ አይገኝምን አለት ምን ታጥቶ ስንኪ ሳንተ ለግመሎችህ የሚሰጡት ገፈራ የሚያድሩበት ጋጥ አለን አለችው። ሰጣቷ ቀሰበት ለጀርዋ ጉትቻ ሰጥቶ አስጊጦ ሰደጻት። ሳባ የሚባል ወንድም አላት። ማን ሰጠሽ አላት። እንዲህ ያለ ሰው አለችው። የሚሰጠው የሚያስጌጠው መስሉት ዛደ። አንተን ያህል ክቡር ከዚህ ተቀምጠህልን ብሎ ግመሎቹን ነድቶ አሱን መርቶ ይዞ ገባ። እግርህን ታጥብህ አህል ተምሰህ ዐረፍ በል አሉት። ጌታዬ የላከኝን ሳልናገር አይሆንም አለ። በል ተናገር አሉት ጌታዬ አብርሃምን አልቶ አክብሮታል። ካረጀ በኋላ የወለደው የሚወደው ልጅ አለው። ከሶርያ ልጆች እንጂ ከከነዓን ልጆች እንዳታጋባው ብሎ አስምሎኛል። ገዝብ ይገር መጥቼ ከውኃ ጫር ተቀምጬ ሳወጣ ሳወርድ ይህችን ብላቴና መጣች። እንደምታዩት አስጊጬ ሰደድኳት ለጌታዬ ልጅ ሚስት ትሆነው ዘንድ ስጡኝ እናንተም ገዝብችሁን ተቀበሉኝ አላቸው። ንህነ ኢንክል ተናግር ኢሠናየ ወኢእኩየ ይህማ ከወደእግዚአብሔር የመጣ አይደለምን ምን ማለት እንችላለን አሉት። ቁረጡልኝ አላቸው። ይሁን ተቀመጥ አሉት። አደረ። ሲነጋ አሰናብቱኝ ገዝብችሁን ተቀበሉኝ ልጅቷን ስጡኝ አለ። 10 ቀን ትሰንብት አሉት። እግዚአብሔር አትንቱልኝ ላለ አታሰናክሉኝ ሰላቸው። ባይሆን እሷን እንጠይቃት ብለው ቢጠይቋት እሄዳለሁ አለች። ገዝቡን ሰጥቶ ይዞ ቤመለስ ይስሐቅ ወንበዴ እንዳይጣላቸው ብሎ መንገደኛ መስሎ ይሰልል ነበር። አሻግራ አይታ ያ ማን ነው አለችው። የምትሄጅለት የጌታዬ ልጅ ነው አላት። ተራ ልብስ ሰብሳ ነበርና አውርዱኝ ብላ አጌጣ ቆየች። ይዟቸው ሂዷል። በዚህ ጊዜ ይስሐቅ የ 40 ዓመት ጎበዝ ነበር። ዘፍ፡- 24:1- 66 ዘፍ 25:20

ርብቃ እውተ ማኅፀን ነበረች። አዝኖ ተከዘ ወደ ጌታ ቢያመለክት ምክት ተወግዶላት ጸንሳለች። ጽንሱም በማኅፀኗ እየታወከ ቢያስቸግራት ወሐረት ትሰአል ቃለ እግዚአብሔር ይላል ቃለ እግዚአብሔር ልትጠይቅ ወደ መካነ ራዕይ ሄደች። ከልዔቱ ሕዝብ ሀለው ውስተ ክርሥኪ ወከልዔቱ አንጋድ ይወጽኡ እግዣዝንኪ ሕዝብ ዘየዓቢ እምሕዝብ ይተቀነይ ለዘይንዕስ ሁለት ሕዝብ በማኅፀንሽ አሉ። ትልቁ ለትንሹ ይገዛል ብሏታል። መዋዕለ ጽንስ ሲፈጸም ሁለት ልጆች ወልዳለች። የመጀመሪያው ዔሳው ሁለተኛው ያዕቆብ ነው። ያዕቆብ ማለት አጋዣ ለኩና አዕቃኒ ማለት ነው። የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ተወልዷልና በዚህ ጊዜ ይስሐቅ የ65 ዓመት ሰው ነበር። ዘፍ 25:26

እንደ አባቱ በዘመኑ ጽኑ ረሀብ ሆኖ ወደ ጌራራ ሄዶአቤሜሌክ ዘንድ እንግድነት ተቀምጠ ፍልስጥኤማውያን እስኪቀኑበት ድረስ ዘር ዘርቶ ከብት አርብቶ ከከበረ በኋላ አቤሜሌክ በሰላም አሰናብቶት ተመልሷል። ዘፍ 26:1 – 17

ወከነ ይስሐቅ ያፌቅር ለዔሳው እስመ ዘውእቱ ኮዓ ይሴሰይ ወያዕቆብ ንጹሕ እምዝንቱ ይላል ዔሳው ያውሬ ሥጋ እያደነ ይመግበው ነበር። አንድ ቀን ልጂ ዛሬ በረከት የማድልባት ቀን ናትና ሳልሞት አንድመርትህ እንደምወደው አድርገህ አምጣልኝ አለው። ሲቻከል ልብሱን ትቶ ሄደ። ርብቃ ግን ያዕቆብን ትወድ ነበር። ልጂ ዛሬ አባትህ በረከት የሚያድልባት ቀን ናትና እንዲመርትህ ሁለት ጠቦት አምጥተህ አረድልኝ ። እንደሚወደው አድርጌ ሰርቼ አሰጥህለሁ

ጌታ የአብርሃም ሊገለጠው ጸድቁን
ጠርቶ እንዲህ አለው አንት የኔ ምእመን
መሆንን ልጅህን የምትወልድን።
አብርሃም ተንግ ሊፈጽም ትእዛዙን
ልጁን አወጣትሉ ገመሙ ሃገሉት ተን
በባለና ሳሉ ቢግው አንድነት
ደሴሉት አተረብ ተያቁ በደንገት
እባቱ አንተ አለት ያተሉን ይመሰል
እንጨሉንም ለኒ አመኩመሽለ
የመሥማቱ ዘገበ ከመጪት ይመጣል
አብርሃም አለው ልጂ ሆይ ለተንን
ገሥግሠን እንመጣ ይህን ተራራውን
ጌታ ያመቃልና ወኑ ያለበትን።
ተራራውን ወተተው ከሰታው ቢደርሱ
መሠሪያውንም መርተው ቢጠርሱ
ደጉም እቀረበ ተያቁ ወደርሱ።
አዚኒ አንዲ ልኖር አባቱ ወግነ
ውሉን አዘጋጀ ወኑ ላይሽነ
አገዘ የምትመኘ እኔን መለሰነ
አብርሃምም አለ ይኸው ነው እውነት

አትኮለበትም አንተ ነህ መሥማቱ
ሊሠማ መሆኑን ከለሳቱ ሰምቶ
ደለሉት አለከሠውም ወደ አለውሉ ዘከቶ
ደለትም ለአምላኩ መሥዋቱን ገቶ
ከብለል ከብለል ሊለ ዓይኑን ተመለከተ
ሳደለተው አንሳይተር ለፀናው ሬርቶ
አሥር በደረቱ ደፍቶ አሰተኙተ
በቶሉ አንዲመው መከረው አለገቶ
አብርሃምም አሥር አጅና አገሩን
ደፍቶ አሰተኙተ አገደ በገ ልጁን
ከገንቱ አሳረፈ ሰለት ያተሉን
ጌታም ተመልከቶ ታማኙቱን
አብርሃም ተው አለው አትረድ ለጁን
አንድያ ልጅህን ለኒ መስጠትህ
በመሆኑ አኔን ለመውደድህ
የከበረ ደሀን ይሳረክ ጽርፀ
አብርሃምም ልጁን ከአሥራቱ ሬቶ
ጌታ የሰጠውን ነጨሃን በገ መውተ
ወደ ቤቱ ገባ ከልብ ተደሰቱ።

መጋጀው ትመረታለህ አለችው። መከረለት ዲቪ መቅሠቱት አንዲሉ
በረከት ሰዛ መርገም ቢደርሰብኝ ወንድሜ ዔሳው ነው እኔ አንር የለኝ በጁ
ሥለ አደቶ ሣረስ ዓይኔ ደከመኝ ዘበተብኝ ብሎ ይረገመኝ የለምን ?አላት። ወልድየ
መርገምክ ይኩን ላሌየ ልጂ መርገምህ በኒ ይሁን አለችው። አምተቶ ሰማት።
እንደሚወደው አድርጋ መርታ የዘንን አንር በደሙ እየከረጭ ከሬቱ ከደረቱ
ከትከሻው አማላቅ ዔሳው አደን ሲሄድ የሚለብሰትን ለብስ አልብሰ ምክቡን
አዚደዛ ወደደችው አባቱ እንደምትወደው አድርጌ አምተጀለዘሁ በልተህ መርቀኝ
አለው። አንተ ማነህ አለው ዔሳው ወልድክ ዘበኩርክ ዔሳው ነኝ አለው። ወሸ ሥለ
አደቶ አንርክህ ዘዔሳው መታለክ ዘያወቅብ አንርህ የዔሳው ታልህ የያወቅብ እኔ
ምን አገደኝ ሁለታችሁም ልጀቼ ናቸሁ ብሎ በልቶ እምጠሉ ለሰማይ ወእምስሩሉ
ለምድር ይኩን በረከትክ ከኖ እማኢስ ለእነክ በረከትህ ከሰገይ ጠል ከምድር ሰብ
ይብል ለመንድህህ ጌታ ሁነው ብሉ መርቀታል።

ያልቅብ ከወጣ በኋላ ዔሳው መተቶ አባቱ እንደምትወደው አድርጌ
አምተጀለዘሁ በልተህ መርቀኝ አለው። አንተ ማነህ አለው። ዔሳው ወልድክ
ዘበኩርክ ዔሳው ነኝ አለው አሁን እንደምወደው አድርገ መግዘኝ የመረከሉት
ማነው በሩክ ብለሀሁ ብሩክ ነው ያልቅብ ነሥአ በረከተክ በንሕሉት በረከትህን
ያልቅብ ወሰዳት አለው። ቀደም ብክርናዩን አሁን በረከቱን ነወቀኝን ብሉ ያሉትክ
ጀመረ አሉቲት አባ በረከትክ ወአለቦኩ ዘአትረጥክ ሊተ አባቱ በረከትህ እንዲት
ናትን ለእኔ ያከተረሽው የለምን አለው። ወሸ ሥለ ናሁ ኽኛ አልሳኪሁ ለወልድየ
ዋተ ተንቱት ከሜኖ ገዛሞ ከረከት አገዚአቤልር እምጠሉ ለጽግይ ወእምስሩሉ
ለምድር ይኩን በረከትክ እሞው በቀሰትክ ወለእመክ ፈቀደክ ታቅለል ጽር አድንን

ርእለክ - በረከትህ ከሰማይ ጠል ከምድር ሰብ ይብል በቀሰትህ ኑር
ለመንድህህ ተገዝ ብሎታል። ዘፍ 27:1 – 40

ከዚህ ወዲኋ ቀድሞ ብክርናውን አሁን በረከቱን ነተቆኝ ይቀራልን ለብ
ራሱን ብሎ እገድለዋለሁ እያለ ተን ሊቀተር እኖሩ መንድህህ ሊማከህ ይሻልና
ቀሚው እክሲበርድ ሶርያ ከብባ ዘንድ ተተመተ አለችው ሊሂድ መጽናቱት ከመንሂዱ
አልፍ ብሎ ድንጊያ ተንተርሶ ተኛ። ሲዲት ዘአለሙ የመርት መልሊ ከምድር
እስከ ሰማይ ተተከለ መላእክት ሲወጡባት ሲመርዱባት በላይ ዘቆሙን ተዘርግተባት
በላዩ ንገሥ ተተምጠት አያ።ሲነጋ ዛቲ ይእቲዋነታ ለሰማይ ዝ ይትለነጽ ቤተ
እግዚአብሔር ብሎ ደንጊያውን አቀመ ዘይተ አፍለሰባት ሄደ። ሶርያ ሲደርስ
ከአፈግይ ተተምጦ ሳለ የላባ ልጅ ሪዔል ወነጀን አየንላቸ መጣች። የማን ልጅ
ናት አለ። የላባ አሉት እትዩ አድርን ሳጣት። ከሰዲት ታውተኛለህ አለችው የላባ
እንት የርብቃ ልጅ ያልቅብ ነኝ አለት። ሂዳ ለአባቷ ነገረችው። ደስ አሰኝቶ
ተተቢሉታል።

የሥጹን ቀሪው የአየንቱን ፍላጭ ወነጋቱ እገለለሁን ብሉ የምከፍልህን
ንገረኝ አለው። ስለሪዔል 7 ዓመት ለገለህ አለው። ይህን ለለ 7 ዓመት
አገለገሉ ሚስቱን ስጠኝ አለው። የላባ አርዶ የጌረ አውርዶ ዘመድ አዝማድ
ሁሉንም ሲጸሉ ሲጠጡ ውለው ሲመሽ ሊያገ አየንን አዘግሰት። ይህች ሊያ እንገረ ለም
ነበረች። ሲኦጋ መጥቱ ስለ ሪዔል እንጂ ስለ ሊያ ነውን ስለምንድር እንዲህ
አደረገውብኝ አለው። ወገሬዋን ለማድ ታሳት ሳለች ታናሽ አትበርም ይህን
ሳምንት ዘልርስ ሪዔልን ደገም አስተማለሁ። ስለ ርዳም 7 ዓመት ትገለግለህ
አለው። ይህን አለ።

ሳምንትን ዘልርሶ ሪዔልን ሰጠው። ይህ ተረኛ የጉትሳል መለክ መለክም
ነበረች ከለያ ይልቅ እሷን ወደደ።

ከዚህ ወኋላ አመናወተኛ ለሂድ አለው። 14 ዓመት ብትገለገኝ ሁለት
ልጆቼን ሰጠሁህ ለ 6 ዓመት ምን ለክለህ አለው። ከመንታህ ዝመለሙሌ
የመለመን የተዘገረሳረውን ለይቼ ለወሰድ አለው። ይህን አለ። ውኃ ሲጠጡ
ዝመለሙሌ ቀትር ዲያሳያቸው ወነጀ ሁሉ ዝመለሙሌ የመለ የተዘገረጉረ
ወሰሌ። ዋጋውን እየተመጠ ዲያስቸገረው መርቅ ዛጠረ መጠር እነለ ለለረ
እረር እንዲሉ አሳታችሁ መለክም ዛደርገሉት ከሉ አደረገወኝ ጌታም ወደ
ተመለድክበት ሀገር ሂድ አለኝ። ምን ይመክትኋል አለቸው። እኛ ከአሳታችን
እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የለንም እኛን ዜሙ ዋጋችንን ተተብሉ የለምን ያለን
አድርገ አሉት። ግስተዘን ልጀዘን ወንሙል ጭኖ ከቀሰን ነድቶ ገዘነድ ገዛ።

ሳባ መትሳሉን የለምው ወለስተኛው ተን ነው። ብትኔዋን አለከትሉ
ወረረስ ወሰትሉ ሠኖ ያገሉን ቀን መንድ ወነ ተንቱ ደረለበት። የታዘዘ
መልክ ከሉ አንሳትናገረው እመት አለው። ልጀቼን እንዳለው ግድረገው መልክም
ነውን አግልስቱንስ መጪ ትህ ለለምንድን ነው አለው። ድንኳኔ ገዝ ከረትህ
አደደለምን አትፈልግም አለው። የመረቶችው ሪዔል ገሰረት። ከብርቃ ሥር ደጊቃ
ተተመጠቸት። ፈልን ወርብር አማ። ልጀቼ ልጀቼ ወለን ነገር እማተለሉ ብሉ
ሥልስተ ስምል አቀቀ መርጀችው ተመለሰ። ዘፍ ከምዕ 29 – 31

ያልቅብም ለዔሳው ከወጉ ከናሉ ሃያ ሃያውን ከላሙ 40 ከጸረው 10ሩን ከግመሉ
30ውን ከአህያው 20 አጀ መንሻ ለጾ ሚስቶችንና ልጀቹን ፈልገ ያከቀን አችገር
አፉ ብቻውን አደረ። ለሊት በሕልሙ ጌታ ወእምሳለ ወረዛ ተደሕ ወኖ ሲታዘው

ሹለጻው ሲደንዝዝ አትላላ ልተቀኝ ቢለው ካልባረከኝ አስትህም ቢለው ስምህ ማነው ቢለው ያዕቆብ፣ ከሰውም ከእግዚአብሔርም ታግለህ አቸንፈሀልና ስምህ አስራኤል ይሁን ሲለው ራዕይ አየ። ሲነጋ ዔሳው 400 መቶ ራሱን ሁኖ ሊቀበለው መጣ። አንገት ላንገት ተታቅፈው ተላቀሱ። እሊህ ምናችህ ናቸው አለው። ጌታዬ ለባሪያህ የሰጠኝ ልጆቼ ናቸው። አለው ከፊትህ ያለፋትስ አለው። በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ትቀበለኝ ዘንድ የሳኩልህ ነው አለው። ወንድሜ ለኔ ብዙ አለኝ ያንተ ላንተ ይሁን አለው። ግድ አለው። ተቀብሎ እንሂድ አለው። ሕፃናቱን እንሰላቱን እንደምን አድርጌ አንተ ቅደም አለው።

ሶኮት ሲደርስ ከልያ የወለዳት ልጁ ዲና ወደመስክ ወጣች ሴኬም ወልደ ኤሞር አግኝቷት ግድ ብሎ ከክብር አሳነሳት። አባቱን ይህችን ብላቴና ካላጋባኸኝ አለው። ተያይዘው ሄደው ልጅህን ለልጄ ስጥልኝ አለው። ሰምያንና ሌዊ እኅታችንን ለኢንዙር እንሰጣለን ብለው ካልተገረዛችሁ አንሰጥም አሉ። ይህማ ቀላል አይደለምን ብለው ሕዝቡን መከረው ተገረዙ። በ3ኛው ቀን ቆስለው መሄድ አቅታቸው ሳሉ ሰይፍ ሰይፋቸውን መዘው ሄደው እነሱን ፈጅተው እኅታቸውን ይዘው ተመለሰዋል። ዘፍ 34:1-30

ጌታ ወደቤቴል ውጣ አለው። ከልያ ከራሄል ያሉትን አማልክት ተብሮ ሄደ። ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠኋትን ምድር ትወርሳለህ ዘርህንም እንደ ሰማይ እንደባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ አለው። ሐውልት ተክሎ ዘይት አፍስሶበት ስሙን ቤቴል ብሎታል። ምድረ ኤፍራታ ሲደርሱ ራሄል ብንያምን ስትወልድ በምጥ ተጨንቃ ሞተች። እሷን ቀብሮ ወደ አባት እናቱ ገብቷል።

ከከብቱ ብዛት የተነሣ እንድ ላይ መኖር የማይችሉ ሲሆኑ ዔሳውወደ ሴይር ሄደ። ርብቃ ይስሐቅን ያዕቆብ እንኳ በከብታችን በከብቱ ናዙብት እዘዙበት ይለናል ዔሳው ግን ስንኳ በከብቱ በከብታችን አያሳዝዘንም ምን ይመስልሀል አለችው። አሁንማ በዔሳው ያደረ ሰይጣን በያዕቆብ ያደረ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አውቄ ልቤ ወደ ያዕቆብ ተመልሷል አላት። እንዲህ ከሆነማ እናስታርቃቸው አለችው። ጠርተው አስታረቋቸው ከዚህ በኋላ ይስሐቅ በ180 ዓመቱ ዐረፈ። ዘፍ 35:28

የዔሳው ልጆች ዕርቁን አልወደዱምና ተቆጥተው ያዕቆብን ሊጣሉ ተነሱ እርሱም አብሮ ሊጣላው ጦር ሠርቶ ሄደ ወንድምህ ጦር ሁኖ መጣብህ አሉት። ታርቀን የለምን? ሚስቱ ልያ መሞቷን ሰምቶ ሊያላትሰኝ ይሆናል እንጂ አላቸው። ጦር ሰብቆ ሾተል መዞ ነው የመጣው አሉት። አመጣጥህ በሰላም ነውን ብሉ ላከበት። በሳም ይንሳህ ከእንግዲህ የኔና ያንተ ሰላም ውሻ ቀንድ ቢያወጣ ከል የዝ ቢነጣ ነው ብሎ መለሰለት። 200 ራሱን ሁኖ ገጠመው። ይሁዳ የዔሳው ልብ ለቀስት ተመችቶ ታየው የአባትን ታላቅ ወንድም መግደል አባትን መግደል አይደለምን? ቢገድለውም ቢያድነውም እሱ እንደወደደ ያድርገው ብሎ አመቻችቶ ሰጠው። ቢሰብ ልቡን መቶታል። ጠፋም «አውራ የሌለው ንህብ አለቃ የሌለው ሕዝብ» እንዲሉ ተብታትነዋል። እነ ያዕቆብ አየተከተሉ ፈሰን ኤፍራጥስ ድረስ አሳደዋቸዋል። እንግዲህስ ተውን እንጉበር አሏቸው ተውአቸው ይገብሩ አላቸው። ከዚህ በኋላ እስከ በአተ ግብጽ ድረስ 15 ዓመት ገብረውላቸዋል። ሕዝብ ዘየዝኢ እምዝብ ይትቀነይ ለዘይንዕስ ያለው በዚህ ተፈጽሟል።

ያዕቆብ የወለዳቸው ልጆች 13 ናቸው መጽሐፍ ትውልደ አንበት ስለማይቆጥር ዲናንትቶ 12 ብሎ ይቆጥርለታል። 6ቱን ከልያ ወለዷቸዋል። ሮቤል ስምዖን ሌዊ ይሁዳ ይሳኮርና ዛብሎን ናቸው። 2ቱን ከራሄል ወልዷቸዋል።

ቱን ከራሔል ባርያ ከባላ ወልዷቸዋል። ጸንና ንፍታሌም ናቸው። 2 ቱን ከልያ ባርያ ከዘለፋ ወልዷቸዋል። ጋድና አሴር ናቸው። ዲናን ከልያ ወልዷታል። ዘፍ 35:23 ሁለት ሚስት ሳለው ከባርያ መውለዱ ስለምንድር ነው ቢሉልያ 3 ልጅ ስትወልድ ራሔል ዕፀ ጣንወን ሁና ትኖር ነበር። ልጅ ካልሰጠኸኝ እሞታለሁ አለችው። ልጅ መስጠት መንግት የሚቻለኝ እሞላክ ነኝን? አላት። የወለደችው ለኔ ይሁን ብላ ባሪያዋ ባላን ሰጠችው ወልዳታለች ልያም መውለድ ብታቆም የወለደችው ለኔ ይሁን ብላ ባሪያዋ ዘለፋን ሰጠችው። ወልዳለታለች። ዘፍ 30:1 – 13

ይገርመው ምሳሌ ነው። ያዕቆብ የተምህርተ ወንጌል ልያ ራሔል የምእመናን አስራኤል ባላ ዘለፋ የምእመናን አሕዛብ ሕፃናቱ የጸድቃን ሰገዕት ምሳሌ ከባላ ከዘለፋ መውለዱ ወንጌል ከአሕዛብ ደርሳ ከምእመናን አሕዛብ ጸድቃን ሰገዕት ለመገኘታቸው ምሳሌ ነው።

የደጋጉ ልጅ ደጉ ያዕቆብ	ሲሊት ፀራለይ ሬሚውን አደኖ
ክርሱ መጣ በክብር የጽድቁ ክብብ።	አለለትሙ አለ ካለባለሽ ዬቱ
ሶሙን አጨሬችው ለክብንሙ	ጌታም ፍጡም ቀቅሩን አደኖ ባረከው
ከሩ ተወልዶ ድንገል ማርያም።	ሰሙንም ለውጠ አደራሌል አደው
አንድ ቀን ተዝርተው አንድ ቀን ታቀደው	አንደ ዓልር አሸየ ሁብቁን አጨው
ለርሱ ተገሳለት ወንድሙ ዔሳው።	ዝር የዋህ ነውና ያለው ትንሳት
ልጆችም ገቡ ለለፍ በሙድር	አሥራ ሁለት ልጆች ለርሱ ተወለዱ
ለሙትወለድ ድንገል ክርሱ ዝር	በክርሱ አንዲሆን የአለቁ አሰት

ከ15 ዓመት በኋላ ዘመነ ረሀብ ቢሆን በዮሴፍ ጥሪ ለባ ራሱን ሆኖ ገብጽ ወርዷል ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ የሴፍ እናቱ ራሔል ሁለተኛ ልጂ ብንያምን ስትወልድ በምድሪ ሉዛ ወርፋለች። ራሔልን ለለመውደድ እሱን ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር። ከመውደዱም የተነሣ በአራት ጎበር በአምስተኛ መርቅ የተሠራ ልብስ አልብሶት ልብስ አልብሶት ነበር። ወንድሞቹ በዚህ ቀንተውበታል።

ከለያልይ ባንዱ የወንድሞቹ ነጸ ለሱ ነጸ ሲሰጣዉ ሕልም አይቶ ለአባቱ ነገረው። በእህል ምክንያት ይዝለህ ይሆናል አለው። ሁለተኛ ዩሐይ ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብት ላንድ ከክብ ሲሰግዱ አየ ዕሐይና ጨረቃ የተባሉን አኔና እናትህ ነን አሥራ አንድ ከዋክብት አሥራ አንዱ ወንድሞችህ ናቸው አንድ ከክብ አንተ ነህ የኋላ የኋላ ይዝለህ ይሆናል ነገር ግን ወንድሞችህ ከሰው ይጣሉሀልና አትንገራቸው አለው።

ከብቶቻቸውን ይዘው ለምለም ሳር ጥሩ ውኃ ካለበት ደኖራሉ ስንቃቸውን አሲዞ ሰጥተህቸው ና ብሎ ሰደደው። ሲፈልጋቸው ሰንብቶ አጣቸው የታዘዘ መልአክ በአምሳለ ብአሲ ሆኖ ያይታን አሰልህ አለው፣ ሄደ። ከሩት አይተውት ባለ ሕልሙ መጣ ወገረን እንገደለው ከሞተ በኋላ ይነግሥብን እንደሆነ እናያለን አሉ። ያመጣላቸውን ተተባለው ከዘው ይጨቱት ጀመር ሮቤል ግንም ቢሆን ያዋንታችን ሂላቱ የሥጋችን ቅሪቱ አይደለምን ተው ብሎ አዘጣላቸው። ከዚህ በኋላ አቡን ከጉድጋድ ከተው ይሙዙ ጀመር። ሮቤል ከብት ሊመልስ ሄዶ ሳለ እስማኤላውያን

ሙጭ ይሁን መንድግችንን ብንገድለው ምን እንጠተግለን እሽጠው አላቸው። ፹20 ብር ሸጠውታል። ርዪል ተመለስ ቢያሳው እንደሸጡት አውቆ ልብሱን ቀዶ አመድ ነስንሶ ያለቅስ ጀመረ። ጠቦት አርደው ልብሱን በደም ጠምተው ያን ብላቴና ወደቤ ልከዉ ነብርን አውሬም በልቶት እንደሆነ ልብሱን እንዲህ ሆኖ አገኘው ብለው ላክዉት ልጁን ከሱ አውሬ በልተታል እያለ ገብጽ አስኪወርድ ድረስ ቤያለቅስ ኑሯል። ዘፍ 37፡1 -36

እኒያም አስማኤላውያን ገብጽ ገብተው ከፈርዖን የመር አበጋዞች ላንዱ ለጲጥፋራ በሠላሣ ብር ሸጠውለታል። ጲጥፋራ በጦሴዊ ምክንያት ከበረ። ይህ ዕብራዊ ከመጣ ገንዘቤ በዛ ብሎ በቤቱ ላይ አሠለጠነው ወወደ ዮት አዕይን ቲሃ ብእሊተ እገዚኡ ይላል የጲጥፋራ ሚስት ዓይኗን ጣለችበት አንድ ቀን ነኪ ስቅብ ምስሌየ ኖ ከኔ ጋር ተኛ ብላ በግልጽ ነገረችው። ጌታዬ በሀብቱ በንብረቱ ሲያስለጥነኝ ባንቺ ላይ አላስለጠነኛም ብሏት ወጣ። በሌላ ጊዜ ሊሥራ ገቦጃ ቤት ገብቶ ሳለ አንተ ባሪያ ዛፊስ አለቅህም ብላ ተራምጻ የዘቸው ኑዮቴ እሄዳለሁ ሲል ተሚሱ ከወደኋላው ተቀደደ። ብታዋር ተሚሲን ከወደፊቷ ቀዳ ሮጠች። ምን ሆንሽ አላት። ይህ ዋጋቢኛ ባሪያ ልድፈርሽ አለኝ። አይሆንም ብለው ተሚሲን ቀደት ሄደ አለያዙት። ፈቃዱስ ያንቺ ይመስላል። ይህ ባይሆን ያንቺ ከፊትሽ የሱም ከኋላው ባልተቀደደ ነገር ብለው ለጊዜው ደስ ይበላት ብለው አሠሩት።

ኢጥ ፋራም ለሚስቱ አድልቶ ከፈርዖን አስረዋች ደረበው። ወኢገደረ ዘእንበለ ሚሮት እንዲል ያለሽመት አላደረም ከዚያም ቹሙ እስረዋች ባንተ ቃል ይደሩ ብሎ መብት ሰጥቶታል። የፈርዖን ጠጅ አሳላፊና ሥጋ መልከኛ ታሥሪው ነበር። ሕልም አይተው የሚተረጉሞላቸው አጥተው ሲያዝኑ ወሕይ ሲዋት ቆይቶ ገብቶ ምነው አዝናችኋል አላቸው። ሕልም አይተን የሚተረጉመልን አጥተን አሉት የገለጸልት ይተረጉማል ንገሩኝ አላቸው እንጀራ አበዛው፣ በ3 መሶብ ነው እንጀራ ይዤ ወደ ቤተመንግሥት ስገባ አዕዋፍ ከላዬ ገልብጠውት ሲመገቡት አየሁ። አለው። እስከ 7 ቀን ፈርዖን ይሰቅልሃል አዋፍ ይመገቡሀል አለው። ጠጅ አሳላፊው 3 የወይን ዘለላ በጽዋ አድርጌ ለፈርዖን ስሰጠው አየሁ አለ። እስከ 3 ቀን ወደ ቹሙትህ ትመለሳለህ ብሎ ተርጉሞላቸዋል። ጠጅ አሳላፊውንም እኔም ተድሞ በግፍ ተሸጨአለሁ። አሁንም በግፍ ታስሬአለሁና ከፈርዖን ሬት አስታውሰኝ አለው። ተስፋውን በሰው ስላደረገ ጌታ ተጨማሪ 2 ዓመት በግዞት እንዲቆይ አድርጉታል። ትር.ወ በ3ኛው ቀን ፈርዖን የልደት በዓሉን ሲያከብር መኳንንቱ ገብተው እጅ ነሱ እንደምን ውላችኋል አላቸው። በደህና ውሰናልየቀድሞውን ጠጅ አሳላፊ የሬውን እንጀራ አበዛ ለሹመት የተድሞውን እንጀራ አበዛ የሬውን ጠጅ አሳላፊ ልቅጣት ብለናል አሉት። ያን ወደ ሄሙት መልሶታል። እንደራ አድሙን አስቅሉታል።

ያም ወደሄሙት ከተመለሰ በኋላ እስከ 2 ዓመት ድረስ አልተወሰውም። ከ2 ዓመት ቄኋላ ፈርዖን ሕለም አየ ከወንዝ ጽር ያለ ይመስለዋል 7 የመሬሩ ያማሩ ወተተው ሲይግሩ 7 የከሱ የከሳሱ ላሞች ወተተው ውጠዋቸው ያልተጠገቡ ሲመስሉ ሁለተኛ 7 ያሬሩ ያማሩ እሸቶች ሲወጡ 7 የደረቁ የጽዋቁ እሸቶች ወተተው ውጠዋቸው ያልተጠገቡ ሲመስሉ ያያል። ጠዘቅቁን ጠርቶ ተርጉሙልኝ አላቸው። ሊታታቸው በዚህን ጊዜ ያ ጠጅ አሳላፊ ዘየዋሃ እኔኖ ዛለንጀራዬ በነበር ላለን ሕለም አይተን የጲጥፋራ ባሪያ ተረጎመልን እንደሰውም እሱ ሞቱ እኔም ወደ ሹመት ተመለስኩ እሱ ይተረንምለሃል አለው። አስጠርቶ ሕልመን ነገረው።ደግ ምሳሌ እንዳለው ስግጠሮት ደጋግሞሃል 7 የመሬሩ ያማሩ ላሞች 7 ምያሬሩ ያማሩ እሸቶች 7 አሠመነ ጽጋብ ናቸው። 7 የከሱ የከሳሱ ላሞች 7 የደረቁ የጽቀቁ እሸቶች 7 አሠምን ረሀብ ናቸው፣ ውጠዋቸው ያልተጠገቡ መምሰላቸው 7ቱን የጥጋብ ዓመታት የሚያበርሙ 7 የረሀብ ዘመናት ይመጣሉ ብሎ ተርጉሞለታል። ፈርዖንም ቢትወደዱ አድርጉ ሹሞታል።

ከዚህ በኋላ ዮሴፍ የመርቅየብር ጣብሩ አዕል ይሁን ብሎ አዋጅ አስነገር ዖ7 ዓመት እህል በትረፉ አከማቸ።

7 የጽጋብ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ በምድር ላይ ጅኩ ረሃብ ሆነ። የዕቀብ በንግሌ እህል እንዳለ ስምለሀና ሸምታችሁ ኑ ብሎ ለጀዝን ለደሃዎች ቢያዛቸው። የሌዊ አይቶ አወቃቸው ምንድር ናቸሁ? ብላችሁ ጠይቋቸው አለ። ከግዞች ነን አሉ። ሐሰት ሰላዮች ናችሁ አላቸው። ሰላይ ከሆነሱ ተውጣቶ ይመጣል። እኛ ግን ያንድ ሰው ልጆች ነን አሉት ሐሰት አንድ ሰው አሥር ይወልዳልን አላቸው። ኧረ አሥራ ሁለት ነብርን አሉት። ሁለቱ የት ሄደዋል አላቸው። አንዱ ሕጥን ሆኖ ከቤት ቀርቷል። አንዱን ግን አውሬ በልቶታል አሉት። እንግዲያስ ከቤት ያለውን ካመጣችሁት ዘግቶች መሆናችሁን አውቃለሁ። ከዚያ በኋላ ተመላልሳችሁ ትሸምታላችሁ። ያለበለዚያ ግን ሰላዮች መሆናችሁን በዚህ አውቃለሁ ብሉ ስምንን አስቀርቶ ሰንዲውን ከወርቃቸው ጋር በየአደባቃቸው አድርጉ አሰናበታቸው።

ከቤታቸው ደርሰው አደባቃቸውን ሲፈቱ ወርቃቸውን አግኙ አንዱ ለአንዱ ሊተሳ ንብሉተኒ ወርቅየ ይል ጀመረ ሰምንስ አላቸው የህጉ ገዥ አስጠ ብቆታል አሉት።

ያን ባልተው ሲጨርሱ ሄዳችሁ ሸምቱ አላቸው ብንያምን ካላመጣችሁ አይሆንላችሁም ብሎናል እሱን ሰጠን አሉት። ዮሴፍን አውሬ በላው ስምንን አስጠበቀው አላችሁኝ አሁን ደግሞ ብንያምን እንውሰደው ብላችሁ አንድ ነገር ሲሆን ጥሃን ወደ መቃብር ልታወርዱኝ ነው አላቸው። ይሁዳ እኔ ደህና ዓሬመልሰው እዳው በእኔ ይሁን አለ። ሰጣቸው ይዘውት ሄዱ። እናመጣዋለን ያላችሁት ወንድማችሁ ይህ ነውን አላቸው አምን አሉት ዝግጎሌ አባታችሁስ ደህና

አለን አላቸው አምን ይደሰኝ ነው አሉት በሩህ በህሊዙ የተሳረከ በው አለ አባታችንን አመስግነው ብለው እጅ ነው ከሙን ከፈርያን ደርጀ መሣሉ ከመንድማው አናንቸው ብሉት ሂደ። በመደናው ውርት ሊያመን ነው ብለው ተደም የወጽርሙን ውርት ሊለምውርት ደሀን መተተናል አሉ። የአለታችሁ አምላክ ልጅሄው ይወርሳል እንጂ አላቸው።

ከልደን ደርስ ጴጥሮስ ማህድ አመርቶ ከወሉ ከመው በኋላ በሰውቱ አንደ መንደ ሁሉት አንድ ሞገ ሀገው ሲሚውት ብዙያም ገም አለ። ምገው አትማሰት ምገ በሉው አለው መተርጉመገ። አልህ ሲደሰቱ ያገሊት ሊጅ ሁሉ ያገሊት ሊጅ ሁሉ ያገሊት ሊጀት ናቸው። ለከም መንድም ገልገ አመሬ በላው አለው አመ። ጀው ተድም ያመሰሉትን ውርት ሊለም ይሀን ያገለ ውርት ይደው መተተገል አለው: ውርያቸውን አትገስ እመለን ስማቸው ከትገሽ ሊጅ ሊይበት ከማኑን አድርገህ ሊጂን አንረ ተውገህ መሊለህ አምላልን አለው አንሊህ አድርገ ከሆማቸው በኋላ ጥቅት አልፋ ጲሉ ተከትሉ ሂደ ውርት ላከደረ ጠመር አህለ ላከደረ አለር አንሊሉ ጊታቱ ደግ ቢያደርገላቸው ከተ ታደርገህታላቸውን ለከምን ጽጥውን መረታችሁን አላቸው ጀረ አሃ አለመድገም የተገኙት ይመት አሉ። ጥትገ ለምገ ይመት ባረያ ሀፕ ይገ ልገጂ ብሉ ከመጨሉ ጀሰገህ ከወገያም ተገኘ ርገለ ገሰ ለከሉ ለገ አለን አወና ለወናውትልኝ አለው። ለምገ የተገኙትን ትጥ ያልተገኙትን አደሰገም አለው። የሴሩ ደሀን ማድረጉ እሌን እገሚው አውነ ትተውት ደሂሉ ይሀን ብሉ ነው ደህሉ አላቱ እገሊህ ጲል ሰማቸገለውና ጲሮት አላይም እኔ ለከሉ ለገ አለ የተገኙትን ትጥ ያልተገኙትን አደሰገም አለው ከመህ ወንላ ደህ ሁሉ የመንድማችን ተፍ ነው ያተገታችገን ጥሁም የሥጋችገን ቁራጥ ጀተነው ደሳላሉ ጀሥር። በሥተርንም ደነጋገሉ ለወገር የሚሰማው አለመቁሰውም። ወደ አለሞገ ደጂቸው ገብት አነ መጀት የሴሩ ምጂችገሥኝ የገሳችሁን መንድማችሁ የሴሩ እኒ ነገ አላቸው። ደሃነው አደጂችሁ አትደገገው እናገተ ለከሉ ቂታደርጌት ጊታ ለመገ አድርገታል። ደህ ሳደሀገ ደህ ሁሉ ከገት ደመሣ ገመር ብሉ ለብከ ስንት ጠተ ለአቶደም ለብሁን በገቱን የሚመጣከትን መረገከ ጠተ አቶቱን ጀብሌረ ሳጠጽ ያገኙትን ከብር ነገራችሁ አምጠልኝ ብሉ ልደለቸው።

ያዕቆብ የገሴሞን በአይሁት መጥር ሊሰገ ደስ አለው። ሰፃ ፊሁን ሆፕ ገብከ መረጸ የሴሩ ፈርያን አለፈቅለ በምድረ ገለም አለፈረው። ጊዜ ጲርሞት ሲደርስ ለጂ በአለቶቹ ሀገር በአለቶቹ መቃብር እገሂ በአልዘብ ሀገር እገሳትተብረኝ አለው። ዘዳግ 47:22-31 ከዚህ ጀኖ ደንም ሳሽ የሴሩ ለጀከ ምናልና ሌፍፊሞን ወተሃገ በገሬው አቀም አቶገን ለጀከገ ቂርከቸው አለው። መለስተገለፈ እደው ለቂርኩ ሌፍፊም መምናል ደለል እጀከገ አልተሳልር ተኖ አጀን በገሬው የቶመው ሌፍፊም ላይ ገሬውገ በተኖ የቶመው ምናል ላይ አደረጉ። የሴሩ አቶቱ ጀክሩ አክ ደህ ነው አል ምናል። ለጂ ሀቶቱም ታላቅ ሕዝቁ ይመጣል ታናሽ ግን ይደልጣል ብሉ ጥርሂምጣል ትገሊትም ተናገርሃምጣል። ትገሊቱ ጀ12ቱ ለጀከ ሁሉ ነው። እገሊህ ሆፕ ፕር ጀ147 ጎመቱ ጀርጅል። የሴሩ በመረገከ ጥኖ ብቱቶቹገን ለጀከትሉ በከገን በለቶቱቹ መቃብር ተቀርቃል። ከፍ ምዕ 48-49 የሴሩም ጀ110 ጎመቱ አርፍ ሥጋገን ለገሁው ገፉ ተቶተው ጀከገን አድርገው ከጀከው ገከሮ ጋር አይመጡትI ቶይተ አለፈለል አገፍጽ ሊመው ደጀመቱ ወጥተገል። መታጠያው ጥር 28 ተገ ነው።

ያዕቆብ ከሌው አጅገ የሚወደው
የሴሩ የተባል ታናሽ ሊጅ ነበረው።
ልርሱ መንድሞቹ እንዲገጠለት
በምጣሌ አየ ሕልም በለሊት።
መንድሞቹ ሁሉ ይሀገን በምተው
ጠሉት ተመቀኙት አሉ አገየው
ከብት ሲጠብቁ ከሄዳ ሁነው
እገሳይጸየጉሩ በገት ጠሊርበው
ያዕቆብ በፍትሩ የሴፍን ላከው።
አሉም ያሉበትን ቢፈልግ ቀይቶ
ደይታገ አቶሞው ብሉ ተገከራቶ
ሰንቀገ ተተብለው ከሪያውገ ከበው
በውጫ ጀርገጌ መቱት ጠከነው
ይነገሥብገ እንደሁ ሞተ ሀሞ በደገ
አበከ እናሞጥልገ የከህ ሰው ሕልመገ።
አየተባባሉ በአርሱ አየከቱት
ሲረባረበፀት አበዚህ ጉልቱ
የሴፍ ግራ ገባው ታወከት ሕይወቱ።
ቢገል ቢገለፈልጥ ጸፋው በከተወት
ከተወር ጉድባድ አውገ ከተውት
ምሣሙን በሉ ሆነው አገድነት
አሁን ግን ከመጣው ቁራሽ ኑፋጌት።
በልተው ቢወርሱ የልባሞውን
የደሠፋን ምክር ሰምተው ሠሙን
በሃያ ብር ጀጠት ለነጋድያን።
ለአባታቸውም ሞቱን ሊያፈሌት
ለብሱን በጠት ደም ነክረው ላኩለት
ያዕቆብ አዘነ ወድቶ ከመሬት
ሊጂ ሊጂ አያለ አለቀሰለት
የሴፍም ተጨመ በግመል ሀገር
አያገዛገ ከገው ቤት ሲኖር
ሥጋዊ ፈቃጁን አለፈጽም ቢሳት
በገዋ አመፈችው የአሳዳሙ ሚስት።

አኑ ግን ንፁሕ ሰው ነመና ትሑት
ሰዎች ቢጠሉትም በምሳነት
አምላክ አልተመውም ለአንዲት ትዝብት።
ከአሥር ዓመት በኋላ ከገሙት ተመርቶ
የፈርዖን ሕልሙን ተርጉሞና ፈችቶ
በገብጽ ተሾመ ሞገስን አገኘቶ።
ሕልሙን ሲተረጉም የሴፍ እገሳለው።
ሰባቱ የጽጋብ አመታት አልፈው
የረኃቡ ዘመን መጣ በተራው።
ያዕቆብ ሰምና ስንዴ መኖሩን
ወደ ግብፅ ላኩቸው አሥር ሊጆቹን
የሴፍ መንድሞቹን አይቶ አወቃቸው
ነገር ግን አልዳተም እገሊበተላቸው።
በየፍቶት በፍትር ቶሞ አያያቸው
ከወደፊት መጣችሁ ማናችሁ አላቸው
ከአንድ ሰው ተመልደን አሥራ ሁለት ነን
አንዱም ከቤት አሰ አኖም አሥራችን
እንዱን አሥራ በሌተት አጥፎስ ሕይወቱን
ቁሰው ሃገ ሳይሞት አረዱት ሞቱን።
አሰም ሳይቀየም በጥንት በደላቸው
ሰሞቸው ስንዴውን ከነገንዘባቸው
ሊገኙ ሲመጡ ደገመው ተመላለው
መንድማቸው የሴፍ መሆኑን ነገደርቸው
ተወቀ አረሩ በከተ ሥራቸው
ያዕቆብ ደስ አለው ሰልጂ መጥር
ምስጋና አተረበ ለአገዚአብሔር
ዘረሀብ ምክንያት ስለጀም ፍትር
ቤተሰቡን ይዞ አንድ እንኳን ሳይተር
ከሶሌፍ ጋር ኖረ በግብጽ ምድር
በመንድም ላይ ከፉ ማድረግ መጨከን
ያዕቆብ እንጂ አደለማም ጠናን
ከፉውን በከፉ መመለስ ነውር
ከፉውን በበጎ መመለስ ግን ከብር

ማቴ 5:43 ሮሜ 13:19

ምዕራፍ 7

2 - ቂትሜን ዕረፍቱ ለቲቶ

ቲቶ ማለት ሠርቅ ማለት ነው። ሀገሩ ቀርጤስ ነው። አባት እናቱ አረማውያን ነበሩ። እሱም ለሰው የሚራራ የተሞገረ የሚረዳ ደግ ነበረ። በሕአምነ ሞክሊተ ጠምቀ ጸደየን ማር 16:16 ያለ ነመና ሊሊት በራዕይ ሥር የሴለው ዛፍ

ዓምድ የለለው አዳራሽ ሊጸና ይችላልን ካላመንክ ካለተጠመቅህ ምንባር ብቻ አያድንህም አለው። ይህን ሲያውጣ ሲያወርድ ቅዱስ ጳውሎስ ቀርጤስ ደርሶ ሲያስተምር ሙት ሲያነሣ፣ እውር ሲያበራ አይቶ ተከተለው። ከፍሉምንት እንዲደርስ አውቆ ሳየገረዝ አስከትሎታል። ወቲቶስ ዘምስሌየ እንዝ አረማዊ መእቱ ኢየገርክዎ ይትገር እንዲል።

ጓላም ከፍሉምንት እንደደረሰ አውቆ በቀርጤስ ኤጲስ ቆጶሳት ሹሞት ሄዷል። ናቆጵዶል ቦሚባል ቦታም ሳለ እንዲህ አድርግ እንዲህ አታድርግ ሲል በአርጣግ በእጅ መልእክት ልኮታል።

እሱም ወንጌል ካልደረሰበት ሲያደርስ አሕዛብን ከጢሮ ኃጢአት ወደ ጽድቅ ሲመልስ መጻሕፍት ገልጿው የሚያስተምሯቸው ቀድሰው የሚያቆርቧቸው ቀሳውስትን ሲሾምላቸው ቆይቶ በዚህ ዕለት ወርኃል።

ጳጉሜን 3 በዓሉ ለቅዱስ ሩፋኤል ሊቀ መላእክት

ሩፋኤል ማለት ፈታሔ ማኅፀን ማለት ነው። ገልባይ ሊቀ መላእክት ነው። ለሄኖክ ወልደ ያሬድ 6 ዓመት በእግረ ገነት ወድቆ ሳለ ኀበዓቱን ከሥታቱን አሳይቶታል ሄኖ 8:15

ወደ ጠቢት ተልኮ ዓይኑን ፈውሶታል። ቤቱን በበረከት መልቶታል። በዚህ ዕለት ተዝካረ በዓሉ መደረጉ ስለ ሁለት ነገር ነው። የመጀመሪያው በዓል ሚሙቱ ስለሆነ ነው።

ሁለተኛው ቅዳሴ ቤቱ የተከበረበት ነው። የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት አባቱዮፍሎስ እምከመረከብዙ ምዝ በቅድመ አምላኪያ ኢዮኔስን ለዝንቱ አድራሜሉክ ቢል እልአርታ አስከስትራሰት ሦስት ድስት ሙሉ ወርቅ ወርቅ አግኝቶ በእንዱ በድስት ሙሉ ወርቅ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት አሰርቷል። በቅዱስ ሩፋኤል ስም በዛበ ወንበሪ ዐቢይ ቤተክርስቲያን አሰርቶ በዚህ ዕለት ቀድሶታል። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ወንበሪውን ወዲያ ወዲህ አናወፀው። ወደ ጌታ ቢያመለክት ቅዱስ ሩፋኤል መጥቶ በትዕዙዙ ለእግዚአብሔር ቁም ወኢትትህክ አመነንክ ክዐታህ አትንቀሳቀስ ብሎ በዘንጉ ቢነካው ባለበት እንተሳቸዋል።

ለ. ተዝካረ በዓሉ ለመ ልከጼዲቅ ካህን

መልከ ጼዴቅ ማለት ንጉሠ ሰላም / ሳሌም / ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ካም ነው። አባቁ ቃይናን ይባላል። አያቱ ኖኅ ጊዜ ዕረፍቱ ሲደርስ ሴምን ከዛም ወገን ደግ ልጅ ተወልጻልና ከዘመዶቹ አሲ... ናብተህ እኒህን ንዋያትና አጽመ አዳምን አስጠብቀው በንጽሕና በትድስና እንዲኖር ሥርዓት ሥራበት

አለው። ንያያቱ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ሩፋኤል ከገነት አምጥተው ለአዳም የሰጡት ጓላም ሰብእ. ሰገል ለጌታ የገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤ ናቸው።

ከዘመዶቹ አስናብቶ ከሴት አትድረስ ጻባ ልበስ ፀጉርህን አትላጭ ጥፍርህን አትቁረጥ ሥጋ አትብላ ጠጅ አትጠጣ በሰንዲ በወይን አስታኩት ብሎ ሥርዓት ሠርቶ በዱዳሴም /ማዕከለ ምድር/ ንዋያቱንና አጽመ አዳምን አስጠ ብቆታል።

አብርሃም ለአምስቱ ነገሥት ሰዶም ረድቶ አራቱ ነገሥተ ከሎዶጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመለስ ደስ ቢለው በመዋዕል የኑ ትፈኑ ቃለከ ወሚመ ታርእየኒሁ ኪያሃ ዕለተ አው አልቦ ልጅህን በትስብዕት የምትልከው በዘመኔ ነውን ብሎ ወደ ጌታ አመለከተ። እሱን አታየውም ነገር ግን ምሳሌውን ታየለህ ሑር እድዎ ለዮርዳኖስ - ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው። ቢሄድ መልክ ጼዴቅ ኅብስተ አኩቴት ጽዋዐ በረከት ይዞ ተቀብሎታል። ወርቅ ዕጣን ከርቤውንም በዚህ ጊዜ ሰጠቶታል። ዘፍ 14:17-18

ከዚህ በኋላ የሆነሩ ሰዎች ሄደው ንጉሥን አሉት ያስጠበቀኝን ትቼ አይሆንም አላቸው። ቡጣሉ አስታርቀን ሲከራከሩ ፍረድልን እያሉት ያስታርቃቸው ይፈርድላቸው ነበር። ፍርድ የማያጓድል ደኃ የማይበድል የተጣላ የሚያስታርቅ የተበደለ የሚያስከስ ቢሆን ንጉሠ ጽድቅ ንጉሠ ሠላም ብለውታል።

መልክ ጼዴቅ የተመረጠ ከህነትም የተሰጠው ከእግዚአብሔር ነው። ወሰመዮ እግዚአብሔር ሊቀካህናት ዘለዓለም በከመሚመቱ ለመለከጼዴቅ እንዲል የሕይወቱ መጀመያ እንዳልታወቀ የሕይወቱ ፍጻሜም አልታወቀም። ማለት እንደ ሌሎች ክሊያት ካህናት በዚህ ጊዜ ተወልዶ በዚህ ጊዜ ሞተ ተብሎ አልተነገረለትም። እስከ ምጽአት ድረስ ሕያው ሆኖ ይኖራል። ምጽአት ሲደርስ ግን ከእነ ኤልያስ ጋር መጥቶ መስከር በሰማዕትነት ይሞታል። ገጽ _____ ተመልከት። ቅዱስ ጳውሎስ አልቦ ጥንት ለመዋዕሊሁ ወኢማኅለቅት ለመንግሥቱ አምላኪሁ ለወልደ እግዚአብሔር ይነብር ከህነቱ ለዝሉፋ ማለቱ ስለዚህ ነው። ዕብ 7: 1-13

ጳጉሜን 5 አሞጽ ነቢይ

አሞጽ ማለት ጸር /ሸክም/ ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ቁጥሩ ከ12 ደቂቀ ክሊያት ነው። ከብት እያረባ ቡቴቁሔ ይኖር ነበር። ሚስቱ ወንድ ልጅ ስትወልድለት ሀብተ ትንቢት ተሠጥቶት ዐቢይ ነቢይ እንደሚሆን ተረድቶ ኢሳይያስ ብሎታል። ኢሳይያስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው።

ንጉሡ ዮርብዓም ወልደ ዮአስ እግዚአብሔርን የማፈራ ነበርና በሰይፍ ከመሞት አስራአልም ከመማረክ አይቀሩም እያለ ትንቢት ሲናገር ሊቀካህናቱ አዛርያስ ቤቴል የንጉሥ ቤትና ቤተመቅደስ ናትና ወደ ይሁዳ ሄደህ በዚያ ትንቢት ተናገር አለው። ላም ጠባቂ ዋርካ ለቃሚ እንጂ ራዕይ የማይ ትንቢት የምናገር ነቢይ ነኝን ብሎ አይሆንም አለ። ማስተማሩንም ቀጠለ። ትንቢቱም አልቀረ ንጉሡ በሰይፍ ሞቷል አስራአልም ተማርከዋል። መዋዕለ ትንቢቱ 50 ዘመን ነው። የጻፈው በ760 ዓ.ም. ገደማ ነው።

ታላቁ የቅኔ መምህር መምህር መንግሥቱ ዘለዓለም ከዘረፉቸው በርቃታ ቅኔዎች መካከል፦

መወድስ

1. ሃይማኖት ወይን ዘዘሐዋርያ ሠረገላ ሥቃይ ወገድል ማትያስ መዘምር
   ኢተርፈ በከ ወኢተከፅወ በምድር
   ሃይማኖት ወይነ ሐዋርያ አኮኑ መጥር
   ቅድሜሆሙ ለማኅበር ጳውሊ ወጴጥሮስ ዘታውጉሉስ አብትር
   ኢፈተወኂ ከመይስተይ ዘኢያስከር
   ወይነ ቤተ ማትያስ ሃይማኖተ ይሁዳ ዘየነሥር
   እስመ ቀዲሙ ተብህለ ኢይጥዕሞ በምዕር
   ምጣር ለይሁዳ አድኅ ሲኦል ሠቃብር
2. መደንግጸ ሕዝባ ለሳሌም ሠረገላ ሙሴ
   ኖላዌ ኢያሱ ወአሮን አባግዐ ብንያም ዘተዐውቀ
   በጎበ ዕብራዊ ንፍታሌም ስሙዐ ርሑቅ ርሑቀ
   ጸራቅሊጦስ ኑጽድኃደ ራማ ዘለብሰ መብረቀ
   ዘናዝሬተ ዘገሊላ ዘበሰሎሜ ወዮሴፍ ነፋሳተ ብሂል ረቂቀ
   በዮሴፍ ዮሴፍሃ ዘብዙኃን አጥመቀ
   አድለቅለቀ አድለቅለቀ አድለቅለቀ አድለቅለቀ
   ዘኢ በጽሑ ሄኖክ ወመልከ ጼዲቅ መንፈቀ
   ምሥራቀ ወምዕራብ ምዕራብ ወምሥራቀ

3. ዕጣኑ ምገር (ዕዝል)

   ሰማዔ ትእዛዙ ለአብ ዝኮሬ ኩሉ ፍጥረት
   አብርሃም ወልድ ዘየሐትት
   እኩየ ወሠናየ በዘቀደመት አሪት
   ምዕራፈ አለ በዝኑ ነቢያት
   አናግደ ሳሌም ወጽአ ቀዲሙ እምነ ሀገሩ ስቅለት
   ወተፈልጠ እምነ አዝማዱ መቃብር ወሞት
   አብርሀ ለነ መቃርዮስ ብርሃነ ካህናት ቀደምት
   እስመ በእግን አንተ ለኩሉ ዘኢይጠፍዕ ማኅቶት
   ይተቄደስሂ ወይትአኩት
   ስምክ ሕያው ዘኢይመውት
   እስመ ለክ ይደሉ ስብሐት

ከሊቀ ወዜማት ሰሎሞን አደለ (ዘደ/ት/ት/ሚካኤል)

ዓይነ መሀይል ጠቢት ሠናይተ ራእይ
እንዚኂ ትተዋነይ ዘምስለ ዑረት መፍቀሪሃ
ፍጡነ ርጸት መንገለ ብርሃን ጽርሓ
እምአንጻር አምጣነ አልጸቀ ሩቶኤል አቡሃ
ከመ ኢይርግጸ ለፍቁራ ወከመዓዲ በኃይል ኢይተቆጣዕ ላዕሌሃ
ዑረትሰ ፈራህ ልበ እምድኅረ ገብአ ቅድሜሃ
ለፍቅርት ዓይነ ጠቢት ኢወአለ በፍሥሓ
ከመ በትፍሥሕት ኢየአል እንዘ ይተዋነይ ምስሌሃ
እስመ ኮነ ማዕቀፎ ሩቶኤል ወላዲሃ

ከመምህር ግደወርቅ ይሴ (ዘቤ/ብ/ኪዳነ ምሕረት)

ዋዜ. ሥጋ እም እቤረ ክብር መፍቀሬ ብሂል አዐቢ
መላእክተ ሰማይ ጌራነ
ላዕለ ዝሀር ሊቀ ቤተ ሙሴ መአዝዘ ኮነ
እስመ እም እግዚእ ተውህበ ዕርገተ ሰማይ ዘመነ
ሥጋ እምሂ እቤር ዘእስተኀዘነ
ሕገ ሙሴ ዕፄ ዝሀር መነነ

ወመ ሐሰስተ ኦቢያት ቀደምት ለመልከጼዴቅ ላዕካኑ
መና ወወይን ቅድሳኑ
ለፋኑኤል አመሰምዑ ትርጓሜ ፋኑኤል ቦኑ
ውስተ ደብረ ኢዮር ዘተሐጽኑ
ገዳመ ሱቁኤል ቦኑ ዋሕድና ወግበ ጻንኤል ኮኑ
እስመ ጽድቀ ዘከርያስሃ ዓለመ መነኑ
ሐነጽተ ጠ ቢባን ካህናት ወእሉ ሊቃውንተ ያሬድ ዝኑ
ማኅሌተ ሰሎሞን ቤት ዘዘበ ብርሃነ መስቀል ብርሃኑ
ይከውን እንከ ለለዘመኑ
አምጣነ ጠፈሩ ጽኑዕ በበአምጣኑ
ውኅሩይ ቅዱሴ ክዳኑ

ከመምህር አያሱ ገ/አልፋ (ዘደብረ ሊባኖስ)

መወደስ ባዕለ ጸጋ አብርሃም እምዘተዘምዱከ
እንከሰ ለትኅሥሥ ሐራሴ ስመ ሕይወት
አምጣነ መጥህሀት ወልድከ ዘውስተ ቤት
ኢያሐውር እምነ ኮኅዱ ለይስሐቅ ገራህት
በይነ ዘለመደ ተዋንዮ ተዋንዮ ፍቅር ምትረተ ምሰለ ወለተ አብ በግዕት
ያዕቆብሂ ዘዋዕቦ ለአእድከ ሐውልት

ይውእል በዕዚም ሰዋስወ ዘኢብርት
ወ እንዘ ይቀድሕ ዘይተ ማዞ ፈለገ ጸን ርሀቅት
ለዘየሐንጹ ማኅደረ ምሳሌ ድንግል መላእክት

ከመጽሐፉአዘጋጅ

መወድስ

1. በውእቱ ሱቃስ ነግደ ተጋድሎ
ይስሕቅ ኤርን ለስልምናሶር ጸታሁ
እስመ ኀህተ ሄኖክ ማይ እንበለ ይቀረብ ቅድሜሁ
ውስተ ሰይፍ ማዕደ ርምያ ፈነወ እዴሁ
ወይትፈአም በጉንሳ ኀበይምን ወጽግም እንዘኢይፌኢናሁ
ሉቃስሰ ድኅረፈአመ በሊዐምትረት ምሳሀ
ፈቀደ ለስኪብ እመንክር ምስካቢሁ
ሕማማትሰ እግብርት እለኅአሩ ምክሁ
ሰአልዎ ለሉቃስ ይሕጽቡ እገሪሁ

2 ወልደ አብ አንተ መምህረ ሱላሜ
ፍጡነ ገሥጽ ማየጸናስ ወለተከ
አምጣነ አፍአ ትውእል ምስለ ዮሐንስ ረድዕከ
ውስተ ቤት ቀለየ ገሊላ አንቢራ ኪያከ
ወእም ዮም ኢገሠጽካ ወለትከ ማይ ትወጽእ ላዕሌከ
እስኒ እምካልዓን አጽናዕከሙ ቅድሜከ
አግብርቲከ ድንጋጋት ኢዐቀቡ አጸደከ
አኮኑ አርመሙ እንዘ ይጸርሑ ብከ
መላእክት ሕጸናቲሁ ለአኃዝ ፍቁርከ

3 <u>ዕጣነ ሞገር (ዕዝል)</u>
እምከመ ሀሎ ጸዊም ጽጌ ምድረ ገነት ሥሙር
እምልላነ ጴጥሮስ ንህብ ዘበኢነሙር
ኢይትኃጣእ በምንትኒ ወንጌል መንግሥት መዓር
መሥጋ ማርያም ጥባሕ ክብር
እምከመ ተጠብሐ ሞተ በሊሐ መጥባሕት በምድር
ኢይሜወር እም አዕይንቲሁ ለዕርገት ንስር
ማርያም ፍቅርት ዘጸውሱስ መተርጉመ ዘቃል ምሥጢር
የህልው ዘልፈ በደብረ ትጉሃን ዘበኩር
ሥርጉተ ስብሐት ፅንሰንፕር ·
ከመ በሠናይ ይልሐቁ ማዕከለ እብትር
ውሉድኪ ሱላሜ ወፍቅር

የቢ መጻሕፍት

1. የኢትዮጵ ማኅበር - መጽሐፍ ቅዱስ /81/ - 1980 አ.አ
2. ትዝዝ አሳታሚ - መጻሕፍተ ትርጓሜያት - /መንፈሳ፣ ጸውሱስ - መልእክትና ቅዳሴ/
3. - ስንክሳር - ብራና
4. - ዜና አበው - ብራና
5. - ገድለ ሐዋርያት - ብራና
6. ጎሩይ ወ.ሥ.ብ. ጌታ - ዜና ሐዋርያት - 1923 ዓ.ም አ.አ
7. - ድርሳናትና ገድላት -ሕትመትና ብራና
8. - ግብረ ሕማማት
9. አባ ኅርኅርዮስ ሊቀጳጳስ - የቢክ ታሪክ በግዕዝ መድረክ - 1978 አ.አ
10. አባ ኅርኅርዮስ ሊቀጳጳስ - የኢት ቤክ ታሪክ - 1986 ዓ.ም አ.አ
11. ሉሊ መልአኩ - የቢክ ታሪክ - 1986 አ.አ
12. - ፍትሐ ነገሥት - አሥመራ
13. - ክብረ ነገሥት -
14. -
15. - New catholic Encyclopedia - vol I - XI
16. -
17. እነ ዶ/ር ሥርግው - የቢክ መዝገበ ቃላት I – III - ጀርመን
18 የኢ. መ.ቅ ማኅበር - የመ.ቅ መዝገበ ቃላት - 19 አ.አ



